ፍኖተ ነፃነት

ሁለተኛ ዓመት ቅጽ 2 ቁ. 42 | ዋጋው፡- 6 ብር | ፍኖተ ነፃነት ማክሰኞ ግንቦት 7 ቀን 2004 ዓ.ም.

የኢትዮጵያ ሕዝብ የሉዓላዊ ሥልጣኑ ባለቤት እንዲሆን እንታገላለን!

## ሚዛን ተፈሪ ግብርና ኮሌጅ በሙስና እየታመሠ ነው" የኮሌጅ ሠራተኞች

### "መሠረተ ቢስ ወሬ ነው" የኮሌጁ ኃላፊ

በደቡብ ክልላዊ መንግሥት ቤንቺ ማጂ ዞን የሚገኘው የሚዛን ተፈሪ ግብርና ኮሌጅ በሙስና እያታመሰ መሆኑ ተገለፀ፡፡ ይህ የተገለፀው የኮሌጁ ሠራተኞች ከ40 በላይ ገጽ ያለው የሰነድ ማስረጃዎችን በመያዝ በዝግጅት ክፍላችን በሰጡት ጥቆማ ነው፡፡ ሠራተኞቹ እንደሚሉት ‹‹የኮሌጁ ኃላፊዎች ከአንዳንድ የግብርና ሚኒስትር ሠራተኞችና ከዞኑ ኃላፊዎች ጋር በመመሳጠር ከፍተኛ የሆነ የመንግሥት ንብረት ከመዝረፋቸውም በላይ አስተዳደራዊ በደል እየፈፀሙ ናቸው፡፡›› በማለት ሲያማርሩ የኮሌጁ ኃላፊ አቶ ብዙአየሁ ገረመው በበኩላቸው ደግሞ ‹‹ መሠረተ ቢስ ወሬና አሉባልታ ነው፡፡›› ይላሉ፡፡

የኮሌጁ ሠራተኞች እንደሚሉት ‹‹ኮሌጁ ከተቋቋመበት ከ1994 ዓ.ም ጊዜ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ኮሌጁን የሚመሩት እነሱ ናቸው፡፡ ለአስር ዓመት ኮሌጁን በመምራታቸው ኮሌጁን እንደ ግል ካምፓኒያቸው ቆጥረውታል፡፡ ከአንዳንድ የግብርና ሚኒስቴርና ከአንዳንዱ የዞኑ መስተዳድር ባለሥልጣናት ጋር በጥቅም ተሳስረው ግልጽ ወንጀል እየፈፀሙ ናቸው፡፡ በኮሌጁ ግቢ ያሉት ቤቶች በቁጥር ይታወቃል፡፡ በየዓመቱ የሚገዛው ቆርቆሮ ሚዛን ተፈሪ ከተማን ማልበስ የሚችል ነው፡፡ እስከ ዛሬ ድረስ የተገዛው ብረታ ብረትና ሲሚንቶ ተመሳሳይ ነው፡፡ የተገዙ

ወደ ገፅ 13 ይዞራል....



## ኢፍትሐዊነትንና አድሎን በውርደት ከመቀበል መከራና ስቃይን በክብር ማስተናገዳችንን እንቀጥላለን

አቶ በቀለ ገርባ ከቃሊቲ ማረሚያ ቤት

5

## ኢቴቪ በወንጀል እንጂ በፍትሐብሄር ልከሰስ አይገባም አለ

### – የነ አንዱዓለም ክስ ፍርድ ለሌላ ጊዜ ተላለፈ

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ (አንድነት) ፓርቲ የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት እና ጋዜጠኛ አብዲ ከማል ላይ የመሠረተው የስም ማጥፋት ክስ ሰፊ ክርክር ተደረገበት፡፡

ኢቴቪ "አኬልዳማ" በሚለው ዘጋቢ ፊልም ስሜን አጥፍቷል፣ ጋዜጠኛውም ቢሆን እንዲሁ ሲል አንድነት ፓርቲ በመሰረተው ክስ ላይ ግንቦት 3 ቀን 2004 ዓ.ም በፌደራል የመጀመሪያ ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 9ኛ ፍትሐብሄር ችሎት በክሶቹ ጭብጨት ላይ ክርክር ተደርጓል፡፡

ኢቴቪ በበኩሉ ጉዳዩ በፍርድ ቤት እየታየ ያለ መሆኑን ጠቅሶ ልከሰስ እንኳ የሚገባ ከሆነ በወንጀል እንጂ በፍትሐብሔር መሆን ስለሌለበት ፍ/ቤቱ ክሱን ውድቅ ያድርግልኝ ሲል እንዲያደርግለት ጠይቋል፡፡ የኢቴቪ ጋዜጠኛ አብዲ ከማል ደግሞ የዘጋቢ ፊልሙ አዘጋጅ እኔ ስላልሆንኩ ልጠየቅ አይገባም ሲል ክሱን ተቃውሟል፡፡

የአንድነት ፓርቲ ጠበቃ አቶ ገበየሁ ይርዳው በበኩላቸው ለኢቴቪ በሠጡት መልስ በፓርቲው ላይ የፈፀማችሁት የስም ማጥፋት በወንጀልና በፍትሐብሔር የሚያስጠይቅ ቢሆንም እኛ የመሠረት ነው ክስ የፍትሐብሔር ነው፤ ጉዳዩ በፍ/ቤት እየታየ ነው የሚባለው ከተመሰረተው ክስ ጋር የሚያያይዘው ነገር እንደሌለ በመግለፅ መከራከሪያቸውን አቅርበዋል፡፡ ጋዜጠኛ አብዲን በተመለከተም ዘጋቢ ፊልሙ ላይ አዘጋጅ ያልተጠቀሰ በመሆኑና አቅራቢው እራሱ ስለሆነ

ወደ ገፅ 11 ይዞራል....

## አርበኞች የፕሬዝደንታቸውን ልመና አወገዙ 13

## እኛ ለወጣቱ ምን አስተላልፈን ነው የምንወቅሰው?




## ሰመጉ ለአንድነት አመራሮች ስልጠና ሰጠ

የቀድሞ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ጉባኤ (ኢሰመጉ)፣ የአሁኑ የሰብዓዊ መብት ጉባኤ (ሰመጉ) "የሰብዓዊ መብቶች መሠረታዊ ባህሪያት" በሚል ርዕስ ለአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት) የአዲስ አበባ ወረዳ አመራሮችና የቋሚ ኮሚቴ አባላት ግንቦት 5 ቀን 2004 ዓ.ም የአንድ ቀን ስልጠና ሰጠ፡፡ ስልጠናው በአንድነት ፓርቲ የህግና ሰብዓዊ መብት ቋሚ ኮሚቴ አስተባባሪነት የቀረበ ሲሆን በለቱ ሰመጉ ያሳተማቸው የምርጫ፣ የሥነ ምግባርና የህግ ሙፃህፍት በስጦታ ተሰጥቷል፡፡ በለቱ ስብሰባውን በንግግር የከፈቱት የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት) የህግና የሰብዓዊ መብት ቋሚ ኪሚቴ ሰብሳቢ አቶ ደምሴ መንግሥቱ ሲሆኑ የስልጠናውን ዋና ዋና አላማዎች በሦስት ከፍለው አሳይተዋል፡፡ አቶ ደምሴ መንግሥቱ ሦስት ናቸው ያሏቸው አላማዎች "መሠረታዊ የሰብዓዊ መብት ግንዛቤ ማስጨበጥ፣ አመራሩን ለአባላቱ የሚያስተላልፉት ነገር እንዲኖር ማድረግ እና የአመራርና የአባላት ሰብዓዊ መብቶች ሲጣሱ የማስከበር ሚና እንዲኖራቸው ነው" ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ስልጠናውን የሰብዓዊ መብት ጉባኤ (ሰመጉ) የሰብዓዊ መብት ከፍተኛ ኦፊሰር የሆኑት አቶ ዳን ይርጋ ናቸው፡፡ የለቱን ስልጠና የሰጡት አቶ ዳን የሰብዓዊ

ወደ ገፅ 12 ይዞራል....

## ሚያዝያ 30፤ ግንቦት 7 ነገም የምንናፍቀው የዴሞክራሲ ጮራዎች 4

## የአቶ መለስ ሦስት ትልልቅ ፍርሀቶች 6

## በአሜሪካ የሚገኘዉ ሲኖዶስ ለሙስሊሞች ተቃዉሞ ድጋፍ ሰጠ 11

## በአፈና ያልተረታው የኢትዮጵያውያን የለውጥ ጥያቄ 2

ዳሰሳ

# በአፈና ያልተረታው የኢትዮጵያውያን የለውጥ ጥያቄ



በዝግጅት ክፍሉ

የአፍሪካ መንግሥታት በ1990ዎቹ መንታ መንገድ ላይ ቆመው ነበር፡፡ ከዚህ ጊዜ በፊት አፍሪካን የሚወክሉ መንግሥታት አንድ የገንዘብ አማራጭ ለመያዝ ተገደው ነበር፡፡ በወቅቱ የምዕራባውያን ሀገራት፣ አበዳሪ እና የችሮታ ተቋማት አፍሪካ በእነርሱ ፖሊሲ አምሳል እንድት ቀረፅ ጠፍንገው ይዘዋት ነበር፡፡ በአብዛኛው የአፍሪካ መንግሥትታት ዘንድ ይጠላ የነበረውም የመዋቅር ለውጥ መንግሥታቱን ወደ ፖሊሲ ቀራፂነት ሳይሆን በአስፈፃሚነት ደረጃ ብቻ ያስቀረ በመሆኑ ከፍተኛ ቅሬታ ይነሳበት ነበር፡፡ ነገር ግን በዚህ ሁሉ መሃል የሚያቀርቡት የዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር ቅድመ ሁኔታዎች አፍሪካን በዴሞክራሲ የተወሰነ ደረጃ ከፍ አድርጓት የነበረ ቢሆንም መንግሥታቱ ይህ ባህሪያቸው ያልሆነን ነገር ለመቀበል ፈቃደኞች አልነበሩም፡፡

የ1990ዎቹ ኢጋማሽ የአንድ ልዕለ ሀይል የበላይነት የነበረውን የአለም ሁኔታ ህዝበ ብዙዋ ቻይና መሸርሸር ጀመረች፡፡ ቻይና ባሳየችው ከፍተኛ የእድገት ለውጥ ለምትፈልገው የጥሬ ዕቃ ምንጭነት እንዲሁም ለሸቀጦችዋ ማራገፊያ አፍሪካን በፅኑ ትፈልግ ጀመር፡፡ ኢህአዴግ ወኔ የሰጠው የቻይና ብድር ለዴሞክራሲያዊነት ቁብ የሌለው መሆኑ ነበር፡፡

በፖሊሲ ደረጃ መንግሥታት የውጭ ግንኙነታቸውን የሚያስቀድሙ ከሆነ ሀገራዊ አጀንዳዎችን ለመመልከት እንደሚቸገሩ ይታመናል፡፡ ኢህአዴግም ያለፉትን የኢትዮጵያ መንግሥታት በዚህ ወደ ውጭ የማተኮርና የመከበብ ስነ ልቡና ሲከሳቸው በተደጋጋሚ ይሰማል፡፡ የኢህአዴግ መንግሥት መከራከሪያ የሆነው «የቤት ስራችንን ሳንጨረስ ወደ ውጭ ትኩረት ማድረግ አልነበረብንም» የሚል ነው፡፡ ብቸኛው የተቃዋሚ ፓርቲ የፓርላማ ተወካይ የሆኑት አቶ ግርማ ሰይፉ ኢህአዴግ የቀድሞዎቹን ከሚወቅስበት ያልራቀ ፖሊሲ እንደሚያራምድ ያምናሉ ፡፡ "ኢህአዴግም ወደ ውጭ የሚያይ ፖሊሲ ያለው ነው፤ ለምሳሌ ያክል ‹ገፅታ ግንባታ› የሚሉት ለውጪው ፍጆታ እንጂ ለህዝቡ ጥቅም ያለመ አይደለም፡፡" የሚሉት አቶ ግርማ "የገፅታ ግንባታ የህዝቡ ፊት ላይ ነው መታየት ያለበት" ይላሉ፡፡ የግብፅና የኢትዮጵያን ህዝብ ገፅታም በማወዳደር «አሁን የኢትዮጵያ ህዝብ ለተቃውሞ ሰልፍ ቢወጣ እንደ ግብፅ ህዝብ ነጭ ቲሸርት ለብሶ የሚወጣ ይመስልሀል?» በማለት ይጠይቃሉ፡፡

የምዕራባውያንን የዴሞክራሲ አቀንቃኝነትም ቢሆን ለተከበሩ አቶ ግርማ የሚዋጥ አይደለም፡፡ "ህዝቡ ሊገነዘብ የሚገባው በጥቁርና በነጭ በህገ መንግሥቱ ላይ የሰፈሩ መብቶችን ማስከበር ያለበት ራሱ መሆኑን ነው፡፡ ህገ መንግሥት ላይ የሰፈሩት መብቶች ሲጣሱ ልክ ጡት እንደፈለገ ህፃን ቦታ ሳይመርጥ መጮኸ ነው ያለበት» ይላሉ፡፡

### ስብዕናን በጊዜያዊ ጥቅም መግዛት

ርዕዮተ ዓለምን (አይዲዮሎጂን) በሚመለከት በሚደረግ ውይይትና ክርክር የሐሳብ የበላይነት ከማንፀባረቅ ይልቅ ስብዕናን በጊዜያዊ ጥቅም መግዛት አንዱ እና ዋነኛው የኢህአዴግ መገለጫ ባህርይ ነው፡፡ በተለይ ስልጣን ከያዘ ጀምሮ የሚያራምደውን የርዕዮተ ዓለም ፍልስፍና ፊት ለፊት ተወያይቶ ከማሳመንና እንዲቀበሉት ከማድረግ መደለያዎችን ማቅረብ መምረጡ ዛሬም ድረስ የሚታይ እውነታ ነው፡፡

ቤት ሰራተኛ ያልሆኑ፣ ስራፈት እና ስራአጥ ሴቶችንና ወጣቶችን በቡና ጠጡና በጥቃቅንና አነስተኛ በማደራጀት ስም የስርዓቱ መሳሪያ ለማድረግ እንደሚሰሩ ይነገራል፡፡ አንድ ስሙ እንዲገለፅ ያልፈቀደ ሰዉ ከስራ ቅጥርና ምድባ ጥቅም አኳያ ደግሞ መጀመሪያ የድርጅቱ ከፍተኛ አመራሮች እስከ ቀበሌ አመራር ያሉ በየመዋቅራቸው መጀመሪያ በጊዜያዊ ጥቅም በመደለል ባሉት ክፍት የስራ ቦታዎች ቅጥርና ምደባ እንደሚደረግ ይናገራሉ፡፡

በአንድ ወቅት አዲስ ነገር ጋዜጣ አንዲት የሐዋሳ ዩኒቨርስቲ ተማሪ የትምህርት ቆይታዋን ጨርሳ ትደሰታለች በተባለ ሰዓት ማልቀሷን አስነብቧል፡፡ በወቅቱ የለቅሶዋ ምክንያት የነበረዉ በዩኒቨርስቲ ውስጥ የኢህአዴግ አባልነት ምልመላ በይፋ መካሄዱን ተከትሎ እሷ ፎርሙን ሳትሞላ ስላመለጣትና ያለበለዚያ ብትመረቅም ወደ ሥራ ዓለም (በተለይ የመንግሥት) እንደማትሰማራ በግልፅ ስለነገሯት ነበር፡፡

ባለሃብቶችን በተመለከተ ደግሞ ምቹ የስራ ቦታ፣ የንግድ ዝውውር፣ አነስተኛ የቀረጥ ክፍያ አሊያም በነፃ የሚጠቀሙበት መንገድ ይመቻችላቸዋል፡፡ በተጨማሪም የተቀላጠፈ የባንክ ብድር አገልግሎት እንዲመቻችላቸው የሚደረግ ሲሆን ከኢህአዴግ የንግድ ድርጅት ወይም ከአመራሮቹ ጋር ስውር የሽርክና መረብ እንዲፈፅሙ እና በህገወጥ ንግድ እንዲበለፅጉ ይደረጋል፡፡

ጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ እንቅስቃሴዎችም ቢሆኑ ወጣቶቹ ብድሩን ለማግኘት የግድ የኢህአዴግ አባል መሆን አለባቸው ይላል፡፡ የሚገርመው የሚበደሩት ደግሞ የኢህአዴግ የንግድ ድርጅቶች መሆናቸው የሚነገረው ከአዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋም (አዲስ አበባ) ከደደቢት ብድርና ቁጠባ ተቋም (ትግራይ)፣ ኦሮምያ ብድርና ቁጠባ ተቋም (ኦሮሚያ)፣ አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም (አማራ)፣ ኦሞ ብድርና ቁጠባ ተቋም (ደቡብ)፣ ከሚባሉት በከፍተኛ ወለድ እንዲወሰድ እንደሚደረግ አንዳንድ በስራው ላይ የተሰማሩ ወጣቶች ይናገራሉ፡፡ ይሄም ወጣቱን የመደለያ ልዩ ጥቅም እንደሆነ ይነገራል፡፡

### የኢህአዴግ ቅጥ ያጣ ቁጥጥር

ኢህአዴግ የህዝብ ቋንቋ እየተናገረ በጠመንጃ ወደ ሥልጣን የመጣ ሲሆን ሥልጣኑን ከተቆጣጠረ በኋላ አምባገነናዊ ሥርዓትን በመገንባት ላይ ነው፡፡" የሚሉ ዜጎች ቁጥራቸው በርካታ ነው፡፡ የአንድ አምባገነናዊ ሥርዓት መገለጫው ምንድነው? ሲባል ደግሞ "የቁጥጥርና የአፈና መዋቅሩ ዋና መለያው ነው" ይላሉ፡፡ ኢህአዴግ በህዝብ አለመታመኑን ከተገነዘበ በኋላ እንደ ዋንኛ ሥራ የያዘው የፕሮፓጋንዳ ሥራዎችን፣ ግዙፍ የሆኑ የስለላ መዋቅሮችን እና የተደራጀ የአፈና ሥርዓትን በመዘርጋት ተግቷል፡፡ የኢህአዴግን ድርጅታዊ መዋቅርን እንደመደበኛ የስለላ መዋቅር ከመጠቀሙም በላይ የመንግስትን የሥራ መዋቅሮች ከህዝብ አገልግሎት ሰጪነት ይልቅ የስለላና የአፈና መዋቅር አድርጎ ይጠቀምባቸዋል፡፡

በሌላ በኩል የተለያየና ቀጥተኛ የሆነ የስለላና የአፈና መዋቅሮችን ይጠቀማል፡፡ የፖሊስ መዋቅርን፣ የደህንነት መዋቅርን፣ የመንግስት አስተዳደራዊ መዋቅርን፣ ካድሬዎችን፣ ኮሚኒቲ ፖሊስን፣ አነስተኛና ጥቃቅን ማህበራትን፣ የትምህርት ተቋማትን፣ የአንድ ለአምስት የስለላና የቁጥጥር መዋቅርን ወዘተ በቀጥታ ለሥልጣን ማራዘሚያና ለወንጀል ተግባር ይገለገልባቸዋል፡፡

### አንድ ለአምስት መዋቅር

ኢህአዴግ ይህንን መዋቅር ለልማት ነው የምጠቀምበት እያለ ቢሆንም በተግባር ግን ለስለላና ለቁጥጥር እንደሚጠቀምበት የተደራጁት ግለሰቦች በግልጽ ይናገራሉ፡፡ ስማቸው እንዳይጠቀስ ያልፈለጉ በአዲስ አበባ ከተማ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ነዋሪ የሆኑና በአንድ ለአምስት አደረጃጀት «የተጠረነፉ» አንድ ጐልማሳ እንደሚሉት "ሲያደራጁን ሥራ ይሰጣችኋል፡፡ አበልም ታገኛላችሁ ብለውን ነበር፡፡ በቋሚነት በሳምንት አንድ ቀን ከ2-3 ሰዓት ስብሰባ እናደርጋለን፡፡ በየቀኑ ደግሞ ለጠርናፊው ውሎአችንና ያጋጠመንን ነገር በሪፖርት መልክ እንድንናገር እንገደዳለን፡፡ የነገውን ውሎአችንንም በእቅድ እንድናሳውቅ እንጠየቃለን፡፡ የት ቦታ ከእነማን ጋር ምን ለመሥራት እንደፈለግን ሳይቀር እናሳውቃለን፡፡ ጠርናፊያችን የሚፈልገው ነገር ካለም ‹ይህንን... ይህንን ጉዳይ ተከታትለህ እንድትመጣ› ብሎ ያዘናል፡፡" ይላሉ፡፡

### የትምህርት ተቋማትን ለአፈና

ተማሪዎች ከመደበኛ ትምህርታቸው ውጪ የኢህአዴግን ታላቅነት፣ የኢህአዴግን ዘላለማዊነት፣ የኢህአዴግን ፍትሐዊነት፣ የኢህአዴግን አስፈላጊነት እንዲጠመቁ ማድረግ ዋንኛው የትምህርት ተቋማት ፖለቲካዊ ተልዕኮ እየሆነ ይመስላል፡፡ በተቃራኒው «የብሔር ብሔረሰቦችን ልዩነትና የልዩነቱን አስፈላጊነት አጥብቆ ይሰበክበታል» የሚሉ ትችቶችም ይደመጣሉ፡፡ በትምህርት ተቋማት ከኢህአዴግ አራቱ ድርጅቶች (ህወሓት፣ ብአዴን፣ ኦህዴድና ደኢህዴን) አባል መሆን ግዴታ እየሆነ ነው፡፡

### ፖሊስ ለስለላ ተግባር

ፖሊስ በህግና በሞያዊ ስነምግባር ወንጀልን የመከላከልና ወንጀል ተሰርቶ ሲገኝ ምርመራ ሠርቶ ተጠርጣሪን ለህግ የማቅረብ ኃላፊነት እንዳለበት ይታወቃል፡፡ በአሁኑ ጊዜ ግን ፖሊስ እያገለገለ ያለው አገርንና ህዝብን ሳይሆን ኢህአዴግን ነው ማለት ይቻላል፡፡ ይህን ሀሳብ የሚደግፉ ወገኖች እንደሚሉት ፖሊስ ተግቶ እየሰራ ያለው የኢህአዴግን ሥልጣን በመጠበቅ ላይ ነው፡፡ ፖሊስ ኢህአዴግን ያወገዘና የጠላን ብቻ ሳይሆን ኢህአዴግን በሐሜት ደረጃ በክፉ ያነሳ እንኳን እንደ የአገር ጠላት አሊያም እንደ ሽብርተኛ እየፈረጀና የፈጠራ ታርጋ እየሰጠ ያስራል፡፡ የሐሰት ምስክሮችን እየመለመለ ያሰለጥናል፡፡ በፈጠራ ወንጀል በተከሰሱ ዜጎች ላይ እያስመሰከረ ያስፈርዳል የሚሉ ትችቶች ይቀርቡበታል፡፡ እያንዳንዱን ዜጋ በየመኖሪያ ቤቱ በየሥራ ቦታው በየመዝናኛ ቦታው በፖሊስ መዋቅርም እንደሚሰለል ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ወገኖች ያስረዳሉ ፡፡ ፖሊስ የአቶ መለስን ስልጣን ለማስጠበቅ የህዝቡን የዜግነት፣ የሰብአዊ እና

ዶ/ር መራራ ጉዲና በአንድ ወቅት "ጅብ ለሊት ሌሊት የሚሰራውን ስለሚያውቅ ቀን ቀን ሰው ይሸሻል፡፡" እንዳሉት ኢህአዴግ የሚሠራውን ስለሚያውቅ በዜጐች ላይ እምነት የለውም፡፡ ህዝብን እንደሸሸ ህዝብን እንዳሳደደ ህዝብን እንደወንጀለ ከጊዜ ወደ ጊዜ በወንጀልና በህዝብ ደም እየጨቀየ ይኖራል፡፡ ኢህአዴግ የሚሠራው ወንጀል ሁሉ ለራሱ ህጋዊ ነው፡፡ ዜጐች የሚሠሩትም ህጋዊ ተግባር ደግሞ ለኢህአዴግ እስካልተመቸው ድረስ ወንጀል ነው፡፡ሁሉም በእጁ ሁሉም በደጁ ነው፡፡ ኢህአዴግ በባልና ሚስት መካከልም ሳይቀር መገኘት አለብኝ ብሎ ወደ ማመንም እየደረሰ ይመስላል፡፡ ባል ሚስትን ሚስት ባለቤቷን ወላጆች ልጆቻቸውን ልጆች ወላጆቻቸውን እንዲሰልሉ ያደርግ ወደ ነበረው የሶቪየት ህብረት ጥብቅ የስለላ መዋቅር እያደገ ይገኛል ፡፡ አቶ ገብሩ አስራት በአንድ ህዝባዊ ስብሰባ ላይ እንደተናገሩት "ገደብ የሌለው ቁጥጥርና የስለላ መዋቅር መዘርጋት የአምባገነናዊ ሥርዓት መገለጫ ነው" ፡፡ ሶቪየት ህብረት ሁሉም ሰላዮች ሲሆኑ የሚሰልሉት አጥተው ተቸግረው ነበር ይባላል፡፡ ዛሬ ኢህአዴግ በአገራችን እየገነባ ያለው የስለላ መረብ ከኢትዮጵያኖች አልፎ ፈረንጆችንም ያሳትፋል፡፡

### ከውጥረት ወደ አብዮት

አምባገነን መንግስታት በሚዘረጓቸው አፋኝ መዋቅሮች ህዝብን ፀጥለጥ አድርገው ለመግዛት የተቻላቸውን ሁሉ ያደርጋሉ፡፡ የአቶ መለስ መንግስትም ይህንኑ መንገድ በመተግበር የስልጣን ዘመኑን በማስረዘም ላይ ይገኛል፡፡ ኢህአዴግ ደርግን ተክቶ መንግስት ከመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ ከመንበሩ ያልተለዩት አቶ መለስ ከ21 አመት አምባገነናዊ ጉዞ በኋላም ለዴሞክራሲያዊ የስልጣን ሽግግር ቁብ ያላቸው አይመስልም፡፡ "ያረጀ ስርአታቸውን" በዴሞክራሲያዊ ወግ እጣፈንታውን ከመለየት ይቅል፣ በስርዓቱ ላይ "መተካካት" በሚል ስልት "ጥገናዊ ለውጥ" ለማምጣት መትጋትን መርጠዋል፡፡ ሆኖም ለአመታት ሲብላላ የመጣውን የለውጥ ጥያቄ ለመመለስ አልቻሉም፡፡

በአንድ ወገን ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና፣ ኢኮኖሚያዊ ለውጥ እንዲመጣ የሚሻውን የለውጥ ኃይል፤ በሌላ በኩል ደግሞ የአቶ መለስን አገዛዝ ለማስቀጠል ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የበላይነቱን በበላይነት በጠቀለለው አገዛዝ መሀከል ግዙፍ የነሳ ውጥረት በማየል ላይ ይገኛል፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ስርዓቱ እየወሰዳቸው የሚገኙ የፖሊሲ እርምጃዎች፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጣልቃ ገብነቶች በህዝቡ ውስጥ ተጨማሪ ቅሬታ ተፈጥሯል፡፡ ህዝቡ እነዚህን ቅሬታዎች አንግቦ ሀሳብ የሚያንሸራሽርበት እና /ወይም በይፋ በቅሬታዎቹ ላይ ተቃውሞውን የሚገልፅበት እድል ዝግ መሆኑ ፖለቲካዊ ውጥረቱን አሳሳቢ ደረጃ ላይ አድርሶታል፡፡

"ዴሞክራሲያዊ የስልጣን ሽግግር በሌለበት እንዲሁም በህዝቡ ውስጥ ቅሬታዎች ሲበራከቱ፣ ህዝብ በመንግስት ላይ እምነት እንዲያጣ ያደርገዋል" ይላሉ አንድ ስማቸው እንዲገለፅ የማይፈልጉ የፖለቲካል ሳይንስ ባለሙያ፡፡ እንደ ባለሙያው ትንተና በመንግስት ላይ እምነት ያጣ ህዝብ በስርዓቱ ላይ ያምጻል፡፡ ህዝባዊ አመፃ ደግሞ አብዮታዊ የስልጣን ሽግግር ያስከትላል፡፡ ያልተጠበቁ ሀገራዊ ቀውሶችን ሊጋብዝ የሚችል አብዮታዊ የስልጣን ሽግግር እንዲከሰት ቀዳማይ ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ ሁኔታዎች ብዙም ትኩረት የማይሰጣቸው አይነት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

ቶማስ ደብሊው ዋከር «The land of sandina 1981» መፅሐፋቸው የሳንዲኒስታ አብዮት (the sondinista revolution) በመባል ስለሚታወቀው የኒካራጓ አብዮት "የኒካራጓ ህዝብ በአምባገነኑ አናስታሲኦ ሶሞዮ (Anostasio somoyo) ስርዓት ላይ የከረመ ቅሬታ ቢኖረውም አብዮቱ እንዲጀመር ያደረገው ቀዳማይ ምክንያት የጋዜጠኛ ፔድሮ ጆአኩኢን (redra jouguin) በመንግስት መገደል ነው" በማለት አብራርተዋል፡፡ ይህ እውቅ ጋዜጠኛ በመንግስት በተቀነባበረ መንገድ መገደሉ በኒካራጓ ህዝብ ውስጥ ሲብላላ የነበረው ቅሬታ እንዲገነፍል አድርጎታል፡፡ በቅርቡ የተከሰተውን የአረቡ አለም እንቅስቃሴም የሚያሳየው ይህንኑ እውነት ነው፡፡ የፊኒሽ የአለም አቀፍ ጉዳዮች ኢንስቲቲዩት ተመራማሪዎች «The ARAB uprising causes, product & implication» በሚል ባወጡት ጥናት እንዲመለከቱት በብዛኞቹ የአረብ ሀገራት በተመሳሳይ ሁኔታ የነበረው ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እጥረቶች (deficit) በአንድ ያልተጠበቀ አጋጣሚ ወደ አብዮት ተቀይሯል፡፡ ቱኒዝያዊው መሀመድ ቦአዚዝ ራሱን እንደ ጧፍ በማንደዱ የተፈጠረው ህዝባዊ መአበል መሪዎቹን እንዲወገዱ ቀዳጣይ ምክንያት ሆኗል፡፡ እነዚህ እውነቶች እንደሚያስረዱት በህዝቡ ላይ የሚፈጠሩ የሚብላሉ ቅሬታዎች በተገቢው መንገድ አፋጣኝና አግባባዊ መፍትሄ ካላገኙ ወደ አብዮት እንዳያመሩ ማድረግ የማይችል ምንም አይነት ሀይል አለመኖሩን ነው፡፡ በኢትዮጵያ በህዝቡ ውስጥ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣው በመንግስት ላይ እምነት የማጣት ስሜት እንዲሁም በስርዓቱ ላይ የተባባሰው ቅሬታ ለአቶ መለስ ስርዓት ግልፅ አደጋ የደገሰ ይመስላል፡፡ የፖለቲካ ተንታኞች ህዝብ በአቶ መለስ ስርዓት ላይ እምነት እንዲያጣ እንዲሁም በቅሬታ የተብላላ ተቃውሞ እንዲያዳብር ያደረጉት እውነታዎች በ3 ነጥቦች ተጠቃለው እንደሚቀርቡ ያምናሉ፡፡ የመጀመሪያው ፖለቲካዊ ምክንያትን ሊባል ይችላል፡፡ የአቶ መለስ መንግስት የፖለቲካ ሜዳውን በልኩ ከማጥበቡም በላይ ከስርዓቱ ተፃራሪ አቋም ያላቸውን አካላት ማሸማቀቅ ብሎም ማሰርን ህጋዊ ሽፋን መስጠቱ፣ በተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ ቅሬታን ፈጥሯል፡፡ ይህ ሁኔታ ፖለቲካዊ ለውጥ ለማምጣት የሚታገሉ አካላት አታካች ሰላማዊ ትግል እንዲያደርጉ የሚያስገድድ ነው፡፡ ሆኖም በሰላማዊ መንገድ ፖለቲካዊ ለውጥ ላይመጣ እንደሚችል በማመን ለአብዮት ምክንያት ሊሆን በሚችል ተቃውሞ ውስጥ እንዲያምኑ አድርጓል፡፡

ሁለተኛ ኢኮኖሚያዊ ምክንያት ሲሆን፣ በሁሉም የማህበረሰብ ክፍል ውስጥ ቅሬታን የፈጠረ ነው፡፡ የኑሮ ውድነት ከጊዜ ወደ ጊዜ መባባሱ፣ መንግስት የሚገልፀው የኢኮኖሚ እድገት በማህበረሰቡ ውስጥ የሚታይ ለውጥ አለማምጣቱ፣ በባለፀጋና በድሃው ህዝብ መካከል ያለው ክፍተት እየተባባሰ መሄዱ የገዢው ፓርቲ የንግድ

ወደ ገፅ 13 ይዞራል....

# የዓለም የኢኮኖሚ ፎረም በኢትዮጵያ!

ጎይቶም ሸዊት

ሚያዝያ 16፣2004 በወጣችው ፍኖተ ነጻነት ጋዜጣ ላይ ከአሥራ አምስት ቀናት በኋላ (ማለትም ግንቦት መጀመሪያ ላይ) በኢትዮጵያ የዓለም የኢኮኖሚ ፎረም የመካሄዱን ዜና ሳነብ በእጅጉ ተገረምኩኝ፡፡ የዓለም ታላላቅ ኩባንያዎች ተወካዮችን እና ዓለም አቀፋዊ ታዋቂነት ያላቸው ኢኮኖሚስቶች ጨምሮ ወደ 700 ተሳታፊዎች በስብሰባው ላይ እንደሚገኙ ተገልፆአል፡፡ ውይይቱ ለሦስት ተከታታይ ቀናት እንደሚካሄድም ተመልክቶአል፡፡

ፈረንጆቹ ይህን ታላቅ ጉባኤ በኢትዮጵያ ለማድረግ ሲወስኑ፣ ምን መልዕክት ለማስተላለፍ ፈልገው ነው? አንደኛው መልዕክት፣ ፈረንጆቹ የአቶ መለስን አምባገነን መንግሥት እንደሚደግፉ በኢህአዴግ የብረት ጫማ ለሚኮደኮደው ደሀው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለመግለጽ ነው ብዬ እገምታለሁ! ሕፃናትን ጭምር በጠራራ ፀሐይ ያስረሸነን መንግሥት ፈረንጆቹ እንዴት ሊደግፉት በቁ? በቅርቡ እንኳን በአማራዎች ላይ የዘር ማጥራት (ethnic cleansing) እና የዘር ማጥፋት (genocide) ለማካሄድ የሞከረን መንግሥት ማበረታታት ምን የሚሉት ፖለቲካ ነው? በበኩሌ ይህ ጉባኤ የሚያመለክተው ኢትዮጵያን ለማዳከምና ብሎም ለማጥፋት የተጠነሰሰው ሴራ በሻዕቢያ እና በወያኔ ብቻ አለመሆኑን ነው፡፡ ሴራውን በመሸረብና ከበስተጀርባ ሆኖ በመምራት ረገድ የፈረንጆቹና የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች እጅ እንዳለበት ለመገመት አስቸጋሪ አይደለም፡፡

የአቶ መለስ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ የሐሰት ፕሮፓጋንዳ የፈረንጆች ቡራኪ እንደተሰጠው እገምታለሁ፡፡ እዚህ አዲስ አበባ እንኳን በረሀብ እየተሰቃየን ኢኮኖሚው በሁለት አሓዝ አድጎአል የሚለውን የሐሰት ኢኮኖሚያዊ ፕሮፓጋንዳ ፈረንጆቹ ተቀብለውታል ማለት ነው፡፡ መሬት ላይ የምናየው ደረቅ ሐቅ ግን ከዚህ የሐሰት ፕሮፓጋንዳ ጋር በሰፊው የሚጣረስ ነው፡፡ በአጭሩ እንደ ኢትዮጵያ የገንዘብ የመንግሥት በጀት (ፊስካል) እና የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲዎች የተበላሹበት ሀገር በዓለም ተፈልጐ አይገኝም፡፡ በዋጋ ንረት ከዓለም አንደኛ ሆነናል!

በድህነት አሁንም ከዓለም አንደኛ ነን፤ በሥራ አጥነት በዓለም ተወዳዳሪ የለንም፤ በሙስና ናይጀሪያ እንኳን አትስተካከለንም፤ በአምባገነንነት ከአቶ መለስ ኮ/ል ጋዳፊ ይሻሉ ነበር! እሳቸው እኮ ሕዝቡን አጥግበው አብልተዋል! ለእያንዳንዱ ሊቢያዊ የድንጋይ ቤት አሠርተው ሰጥተዋል! ወጣት ሴቶች ለምግብ ሲሉ አካላቸውን የሚሸጡባት ሀገር፣ ወጣቶች የሞት አደጋ እንኳን ሳያስፈራቸው አቶ መለስ በኢትዮጵያ ከፈጠሩት ገሀነም ለመሸሽ የሚወዷትን ሀገራቸው ጥለው የሚሰደዱባት፤ ጋዜጠኞች ሃሳባችሁን ለምን ነፃ ሆናችሁ ትገልፃላችሁ ተብለው እስር ቤት የሚወረወሩባት ሀገር ምኗ አስደሰታቸው ነው ፈረንጆቹ በአሁኑ ጊዜ ታላቅ ጉባኤያቸውን በኢትዮጵያ ምድር ለማካሄድ የወሰኑት?

በሌላ በኩል የአቶ መለስ አምባገነን መንግሥት ለፈረንጆቹ ብዙ ውለታ እንደዋለላቸው መርሳት የለብንም፡፡ ዋና ጠላታቸው የሆነውን ዓለም አቀፍ ሽብርተኝነትን ለመዋጋት አቶ መለስ የኢትዮጵያን ክቡር ደም አርሰውላቸዋል! ሬሳቸውም በአደባባይ እንዲጐተት አድርገውላቸዋል! ኢትዮጵያውያንን እያፈናቀሉ በሚሊዮን ሄክታር የሚለካ መሬት ሰጥተዋቸዋል፡፡ ፈረንጆች ዋሻ ውስጥ ይኖሩ በነበረበት ጊዜ ጥንታዊ ሥልጣኔ የነበራትን ኢትዮጵያ አደክመውላቸዋል፡፡ ትላልቅ ፋብሪካዎችን በርካሽ ሸጠውላቸዋል፡፡ የብር ምንዛሪን በመቀነስ ፈረንጆቹ ኢትዮጵያ ውስጥ ተንደላቅቀው እንዲዝናኑ አድርገዋል፡፡ የወርቅ ማዕድናትን በርካሽ ሸጠውላቸዋል፡፡ ለነዳጅ ሀብት ፍለጋ በሩን በሰፊው ከፍተውላቸዋል፡፡ የአድዋ ድልን አርክሰውላቸዋል፡፡ ሙሰኞች ከኢትዮጵያ ሕዝብ የዘረፉትን በቢሊዮን ዶላር የሚቆጠር ገንዘብ ከሀገር አውጥተው ፈረንጆቹ ዘንድ አስቀምጠዋል፡፡ ታዲያ፣ ፈረንጆቹ አቶ መለስን ቢደግፉ ይፈረድባቸዋልን?

ሐቀኛ ተቃዋሚዎች ይህን ጉድ ዝም ብለው ማየት የለባቸውም፡፡ በሰላማዊና ሕገ መንግሥታዊ መንገድ ጉባኤውን መቃወም ይጠበቅባቸዋል፡፡ የአዲስ አበባ ከንቲባ ‹ተብዬው› እንደለመዱት ሰላማዊ ተቃውሞውን እንዳይከለክሉ የሚደረገው ሰላማዊ ሰልፍ ወይም ሰላማዊ ሕዝባዊ ስብሰባ ጉባኤው ከመጀመሩ ጥቂት ቀናት ቀደም ብሎ ቢካሄድ ጥሩ ይመስለኛል፡፡ ከዚህ ቀደም አንድነት ፓርቲ በየሩሳሌም ሆቴል ሕዝባዊ ስብሰባ እንዳያደርግ የተከለከለበት ሰበብ በዚያኑ ቀን የአፍሪካ መሪዎች ስብሰባ አለ በሚል ሰበብ ነበርና፣ ከንቲባ ተብዬው ይህ ሰንካላ ሰበብ እንደገና መሰጠት የለበትም፡፡ በነገራችን ላይ፣ በአፍሪካ ሕብረት አዳራሽና በየሩሳሌም ሆቴል መካከል ያለውን ርቀት ገምታችሁ ብትነግሩኝ ባለውለታዬ ናችሁ፡፡ ሌላው ነገር ጉባኤው መካሄድ ካልቀረ ተሳታፊዎቹ ከአቶ መለስ መንግሥት ሊቀስሟቸው የሚችሏቸው ኢኮኖሚያዊ ተሞክሮዎች መኖራቸውን መጠቆም የሚገባ ይመስለኛል፡፡ ገንዘብ ማተም የሚችል መንግሥት የገንዘብ እጥረት ሊደርስበት እንደማይችል ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መማር ይቻላል፡፡ የሐሰት ኢኮኖሚያዊ መረጃዎች መፈብረክ ደግሞ ከኢትዮጵያ የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር መቅሰም ይቻላል!

# ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት የኢህአዴግ ሳንሱር ቢሮ?!

በለጠ ጐሹ ወ/ሚካኤል

ኢህአዴግ የሀሳብ መካን ሆኗል፡፡ ከተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶችና ከደፋር ምሁራን የሚሰነዘርበትን ትችት መመከት ስላቃተው፣ የኃይል እርምጃዎችን እየወሰደ ነው፡፡ እነ እስክንድር ነጋን እስር ቤት የወረወራቸው የሚያቀርቧቸውን ጠንካራ ሃሳቦችና አስተያየቶች መመከት ስላቃተው ነው፡፡

ኢህአዴግ የሻዕቢያ ሽፋን ነው፡፡ የሻዕቢያ ዓላማ ደግሞ ኤርትራን ለማጠናከር ኢትዮጵያን አዳክሞ ማጥፋት ነው፡፡ ሕዝቡ ስለነቃበት ኢህአዴግ የሥልጣን ዕድሜውን አራዝሞ ዓቢይ ዓላማውን ለማሳካት የማይፈፅመው ወንጀል የለም፡፡ ያለአንዳች ማስረጃ ንፁሐን ዜጐችን ያሥራል፤ ይደበድባል፤ ይገድላል፡፡ የዘር ማጥራት እና ማጥፋት (ethnic cleaning and genocide) ወንጀሎችንም በይፋ እየፈፀመ ነው፡፡ ከሰሞኑ ደግሞ ቀጣዩን ምርጫ በማስመልከት አንዳንድ የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ጠንካራ አባላትን ወንጀል ፈብርኮ ለማሰር ማቀዱን ታማኝ ምንጮች አድርሰዉናል፡፡

ኢህአዴግ የጸረ ኢትዮጵያ ኃይሎች ሽፋን እንደመሆኑ፣ በውስጡ ተደብቀው የሚንቀሳቀሱትን ወሳኝ ኃይሎች በቀላሉ ለይቶ ለማወቅ ያዳግት ይሆናል፤ ግን በመጠኑም ቢሆን ለተመራመረ ሰው በውስጡ የተወሸቀውን የሥልጣን አስኳል ለይቶ ለማውጣት እስከዚህ አስቸጋሪ አይደለም፡፡ እንደሚታወቀው፣ ደርግን አስወግደው ሥልጣን የያዙት ሻዕቢያዎች እና ወያኔዎች ናቸው፡፡ ሻዕቢያዎቹ በወታደራዊ ኃይል የራሳቸውን ነፃና ሉዓላዊ ሀገር የመሰረቱ ቢሆንም፣ ኢትዮጵያ ውስጥ አሁንም በሥልጣን ላይ ናቸው፡፡ ሻዕቢያዎቹ የሚንቀሳቀሱት የወያኔዎቹ ድርጅት በሆነው በህወሓት ጥላ ስር ነው፡፡ የሚገርመው ነገር፣ በህወሓት ውስጥ የበላይነቱን የያዙት ሻዕቢያዎቹ መሆናቸው ነው፡፡ ይህን አግባብ ያልሆነ ሁኔታ ለመቀየር በ1993 እነ አቶ ስየ አብርሃ እንቅስቃሴ አድርገው ነበር፤ ግን በሻዕቢያዎቹ ተበልጠውና ተቀድመው እነሱ ከሥልጣን ሲባረሩ ሻዕቢያዎቹ ሥልጣን እንደያዙ ቀጥለዋል፡፡

በአሁኑ ጊዜ ህወሓት ስሙ ብቻ ነው የቀረው ማለት ይቻላል፡፡ በህወሓት ውስጥ የወያኔዎቹ (የትግሬዎቹ) ሥልጣን እየተመናመነ መጥቶ፣ ወደ መጥፋቱ እየደረሰ ነው፡፡ ይሁንና ዋናው ተዋጊ ሠራዊት በትግሬ ታጋዮች የተገነባ ነው፡፡ በአጠቃላይ የመከላከያ፣ የደህንነት እና የፖሊስ አዛዦችና ኃላፊዎችም ትግሬዎች እንደሆኑ ይገመታል፡፡ እርግጥ፣ ይህ መጣራት ያለበት ወሳኝ መረጃ ነው፡፡ እነዚህን ቁልፍ የሥልጣን ተቋሞች የሚመሩት ትግሬዎች ከሆኑ ሻዕቢያዎቹ በትግሬዎቹ ላይ እንዴት እስካሁን የበላይነቱን ይዘው ሊቀጥሉ ቻሉ? ብለው የሚጠይቁ ብዙ ሰዎች አሉ፡፡

ለማንኛውም በአሁኑ ጊዜ የኢህአዴግ መንግሥት የስልጣን ዘመን ማብቂያ ላይ የደረሰ ይመስላል፡፡ ሃያ አንድ ዓመት እጅግ ረጅም ጊዜ ነው፡፡ በኢትዮጵያ እና በህዝቧ ላይ ይህን ያህል ግፍ በደል እና ወንጀል የፈፀመ መንግሥት እንኳንስ ሃያ አንድ ዓመታት አንድም ዓመት በሥልጣን ላይ ሊቆይ ባልተገባ ነበር፤ ግን ሕዝቡ ከብዙ አቅጣጫዎች ተፅዕኖ የሚደረግበት ስለሆነ በቻይነት እስካሁን ይህን ግፈኛ መንግሥት ተሸክሞ ቆይቷል፡፡ እዚህ ላይ አንድ በደንብ አስረግጠን መግለጽ ያለብን ነገር ያለ ይመስለኛል፤ ይኸውም የኢህአዴግ መንግሥት በኃያላን ምዕራባውያን መንግሥታት ከፍተኛ ድጋፍ የሚደረግለት መሆኑ ነው፡፡

አሁን ካለው ተጨባጭ የፖለቲካ ሁኔታ አኳያ ሲታይ ለኢትዮጵያ የሚበጀው ትግሬዎቹ በሻዕቢያዎቹ (በኤርትራውያኖቹ) ላይ የሥልጣን የበላይነት ቢቀዳጁ ነው፡፡ ኢትዮጵያን ወደብ አልባ አድርገው በጐሣ የከፋፈሏት ሻዕቢያዎቹ ናቸው፡፡ ከላይ እንደተጠቆመው የእነሱ የመጨረሻ ዓላማ ኢትዮጵያ ለኤርትራ ተፎካካሪ እንዳትሆን ከዓለም ካርታ ማስፋቅ ነው፡፡ ይህን ድብቅ ሴራ የሚጠራጠሩ ሰዎች በእኔ አመለካከት የዋሆች ናቸው እላለሁ፡፡

እርግጥ ትግሬዎች መጀመሪያ ላይ በሻዕቢያዎቹ ተታለዋል፡፡ ኤርትራንና ትግራይን አንድ አድርገን ትግረኛ ተናጋሪ ሉዓላዊ ሀገር እንመሠርታለን ብለው አስበው ነበር፡፡ እንዲሁም ነፃ የትግራይ ሪፖብሊክም ለማቋቋም የሚችሉ መስሏቸው ነበር፤ ግን ይህ ሁሉ የማይዘገን የሰማይ ጉም ሆኖ ቀርቷል፡፡ እናም ትግሬዎቹ ከኢትዮጵያ ሌላ ሀገር እንደማይኖራቸው የተገነዘቡ ይመስለኛል፡፡ በመሆኑም ኢትዮጵያን ከምድረ ገፅ ለማጥፋት ከሚፍጨረጨሩት ሻዕቢያዎች ጋር ፍጥጫ ውስጥ ከገቡ ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ ከላይ እንደተጠቆመው፣ ሻዕቢያዎቹን ከሥልጣን ለማባረር እነ አቶ ስየ አብርሃ ያደረጉት ሙከራ ሳይሣካ ቀርቶአል፤ ግን ንቅናቄው እስካሁንም አለ፡፡

ሻዕቢያዎቹ፣ አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግሬዎቹን እንደሚደግፍ ስለሚያውቁ ልማትን ጨምሮ በተለያዩ ማደናገሪያዎች የሕዝቡን የትኩረት አቅጣጫ ለማስቀየስ እየሞከሩ ቢሆንም፣ አልተሳካላቸውም፡፡ ከተለያዩ አቅጣጫዎች ሕዝቡ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶቹን ለማስከበር እየተንቀሳቀሰ ነው፡፡ የመምህራኑና የሙስሊሙ ህብረተሰብ ጥያቄዎች እስካሁን አልተመለሱም፡፡ ሐቀኛ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ከሕዝቡ ጋር እንዳይገናኙ እንደተከለከሉ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ የፖለቲካ ምህዳሩ እየጠበበ ነው የመጣው፡፡ ሕዝቡ ሰላማዊ ሰልፎችና ሰብሰባዎች እንዳያደርግ ተከልክሏል፡፡ የግል ጋዜጦች ላይ የሚደረገው ጫና እየጨመረ መጥቶ አሁን ኢህአዴግ እነዚህን የሕዝብ ድምፆች ለመዝጋት እየተንቀሳቀሰ ነው፡፡

ኢህአዴግ ለብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት በሕግ ያስጠይቀኛል ብሎ የሚገምተውን ጽሁፍ ሁሉ እንዳያትም ስልጣን ሰጥቶታል፡፡ “ስታንደርድ ውል” በሚል ሽፋን ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት አሳታሚዎች በሚያቀርቡለት ጽሁፎች ላይ ሁሉ “የቅድሚያ ምርመራ” (ሳንሱር) እንዲያደርግ ኢህአዴግ ሥልጣን ሰጥቶታል፡፡ እግዚአብሔር ያሳያችሁ በህግ የሚጠየቁ አሳታሚዎቹና አዘጋጆቹ እያሉ አታሚው ምን አግብቶት ነው ጽሁፎችን የሚመረምረው? አንድ መኪና አደጋ ቢያደርስ የሚጠየቀው ሾፌሩ ነው ወይስ መኪናው? ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት እኮ የህትመት መኪና ነው በቃ!

የህገ መንግሥቱ አንቀጽ 29 (ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3) እንደሚከተለው ይደነግጋል፤ “ማንኛውም ሰው ያለማንም ጣልቃገብነት ሀሳቡን የመግለፅ ነጻነት አለው፡፡ ይህ ነፃነት በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጪ ወሰን ሳይደረግበት በቃልም ሆነ በጽሁፍ ወይም በህትመት በስነ ጥበብ መልክ ወይም በመረጠው ማንኛውም የማሰራጫ ዘዴ ማንኛውንም ዓይነት መረጃ ሀሳብ የመሰብሰብ የመቀበልና የማሰራጨት ነፃነቶችን ያካትታል፡፡ የፕሬስና የሌሎች መገናኛ ብዙሃን እንዲሁም የሥነ ጥበብ ፈጠራ ነፃነት ተረጋግጦአል፡፡ የቅድሚያ ምርመራ በማንኛውም መልኩ የተከለከለ ነዉ፡፡ በመሆኑም ኢህአዴግ በእጅ አዙር ለብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት የሰጠው ተገቢ ያልሆነ የቅድሚያ ምርመራ ሥልጣን ሕገ መንግሥቱን የሚጥስ ነው፡፡ የመንግሥት ኮሚዩኒኬሽን ጽ/ቤት ምክትል ኃላፊ የሆኑት አቶ ሽመልስ ከማል ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ራሱን ከወንጀል ተጠያቂነት ለማዳን ያደረገው ነው” ብለው ተናግረዋል፡፡ ይህ ዓይን ያወጣ ሽፍጥ ወደ ፊት ዋጋ እንደሚያስከፍል የተገነዘቡት አይመስለኝም፡፡

ለነገሩ ኢህአዴግ ዴሞክራሲን የተጠቀመበት ኤርትራን ለማስገንጠል፣ ኢትዮጵያን ወደብ አልባ ለማድረግና በብሄረሰቦች ነፃነት ሽፋን ሀገሪቱን በጐሣ ለመከፋፈል ብቻ ነው፡፡

ይህ ደግሞ በህወሓት ውስጥ አሸምቀው ሥልጣን የተቆናጠጡት ሻዕቢያዎች ዓላማ ነው፡፡ ሻዕቢያዎቹ ዓላማውን ካሳኩ በኋላ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ዴሞክራሲ የሚፈቅዱበት ምክንያት የለም፡፡ ሰላማዊ ሰልፎችና ስብሰባዎች ተከልክለዋል፡፡ የሥራ ማቆም አድማ ማድረግ አይቻልም፡፡ ትንሽ ጭልጭል ትል የነበረችው የጽሑፍ ነፃነት አሁን ድርግም ልትል ነው፡፡ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ተከትለው የግል ማተሚያ ቤቶችም ተመሳሳይ መመሪያ እንደሚያወጡ ይጠበቃል፤ ምክንያቱም ለራሳቸው ይፈራሉና፡፡ የፖለቲካ ምህዳሩ ጠብቦ ጠብቦ አሁን ጨርሶ እየተዘጋ ነው፡፡ የዚህ ዓላማ ጥቂት ሃሳባቸውን በነፃነት የሚገልጹ የግል ጋዜጦችን ከጨዋታ ውጪ ለማድረግ እንደሆነ ግልፅ ነው፡፡ ከእንግዲህ የሚቀረው ሐቀኛ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን መዝጋት ነው፡፡ ከዚያስ? ከዚያ በኋላ ለሚደርሰው ማንኛውም ዓይነት የፖለቲካም ሆነ የኢኮኖሚ ሁከትና ችግር ተጠያቂው መቶ በመቶ ኢህአዴግ እና ኢህአዴግ ብቻ ነው፡፡

ግን ትግሬዎቹ ከሕዝቡ ጐን ተሰልፈው የሻዕቢያዎቹን ሴራ ማክሸፍ ይችላሉ፡፡ በህወሓት እና በኢህአዴግ ውስጥ ተሰግሥገው ኢትዮጵያን ለማጥፋት የሚፈጨረጨሩት ሻዕቢያዎች (ኤርትራውያኖች) በቁጥር ከትግሬዎቹ ያነሱ ናቸው፡፡ ከዚያም በላይ በመከላከያ በደህንነት እና በፖሊስ ውስጥ ያሉት አዛዦችና ኃላፊዎች አብዛኛቹ ትግሬዎች ናቸው፡፡ እባካችሁ እናንተ ትግሬዎች ኢትዮጵያን ከሻዕቢያ ጥፋት አድኗት፡፡ ይህን ለማድረግ አንዲት ጥይት እንኳን መተኮስ አያስፈልጋችሁም፡፡ ማድረግ ያለባችሁ፣ “የፃፍነውን ሕገ መንግሥት እናክብር” ብላችሁ ድምፃችሁን ማሰማት ብቻ ነው፡፡

የዘጠና ዓመቱ አንጋፋ ማተሚያ ድርጅት ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት በስተመጨረሻው ለእንዲህ ዓይነቱ አሳፋሪ ድርጊት ተባባሪ እንዳይሆን መጠንቀቅ አለበት፡፡ ክብሩን መጠበቅ አለበት፡፡

የተቀናጀ ሰላማዊ ትግል ያሸንፋል!!

ፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ሐምሌ 2003 ዓ.ም ተመሰረተ፡ ፡ፍኖተ ነፃነት በአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት) ስር የሚታተም በፖለቲካዊ፣ በማህበራዊ፣ወቅታዊ ጉዳዮችና በመዝናኛ ላይ የሚያተኩር ጋዜጣ ነዉ፡፡

ጋዜጣችን ሚዛናዊና ነፃ ጋዜጣ ሆኖ ማገልገል መርሁ ነዉ፡፡ ማንኛዉም ሀሳብና አመለካከት የሚስተናገድበትና የሚንሸራሸርበት እንዲሆን እንሻለን፡ ፡ ሰፊ የሚዲያ ሽፋን አለዉ የሚባለዉ ኢህአዴግም በዚህ ሚዲያ አቋሙንና ፖሊሲዉን ለማግለፅ ቢፈልግ መድረኩ ክፍት ነዉ፡፡

ዋና አዘጋጅ፡-
ሰለሞን ስዩም

አድራሻ፡-
የካ ክ/ከተማ ወረዳ 1
የቤት ቁ.028
ስልክ ሞባይል፡- 09 26 81 46 81

አዘጋጆች፡-
ብዙአየሁ ወንድሙ
ስልክ ሞባይል፡- 09 22 11 17 62
ብስራት ወ/ሚካኤል
ስልክ ሞባይል 09 23 11 93 74

አርታኢ፡-
አንዳርጌ መስፍን
ስልክ ሞባይል 09 13 05 69 42

አምደኞች፡-ዶ/ር ኃይሉ አርአያ
ኢ/ር ዘለቀ ረዲ
ቀለሙ ሁነኛዉ
በለጠ ጎሹ
አንዷለም አራጌ
ግርማ ሞገስ
ደረጀ መላኩ
ወንድሙ ኢብሳ

ኮምፒዩተር ጽሁፍ፡-
ብርቱካን መንገሻ
ህትመት ክትትል፡-
ወንድወሰን ክንፈ

አከፋፋይ፡-
ነብዩ ሞገስ

አሳታሚዉ፡-አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት)
አድራሻ፡-አራዳ ክ/ ከተማ ወረዳ 07 የቤት ቁ. አዲስ

አታሚ፡- ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት
አራዳ ክ/ ከተማ ቀበሌ 07 የቤት ቁ.984
የዝግጅት ክፍሉ ስልክ፡-01 11249659
ፖ.ሳ. ቁ. 4222
ኢሜይል fnotenetsanet@yahoo.com
ujdparty@gmail.com
andinet@ andinet.org
ፋክስ ቁጥር ፡-+251-111226288

## ርዕስ አንቀፅ

# ሚያዝያ 30፤ ግንቦት 7 ነገም የምንናፍቀው የዴሞክራሲ ጮራዎች

ሰባት አመታትን ወደኋላ ተጉዘን ሚያዝያ ሠላሳ እና ግንቦት ሰባትን እንዘክር፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ ዴሞክራሲን እንደሚሻ፣ መልካም አስተዳደር እንደሚያስፈልገው እና ከእንግዲህ አምባገነናዊ አገዛዝን እንደማይፈልግ በጨዋ ደንብ መልዕክት ያስተላለፈበት ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ የኢህአዴግን ጨቋኝ ስርዓት "እምቢ" ያለበት የፍርሃትን ካባ ከላዩ ላይ ገፎ በነፃነት ብርሃን ተስፋን የሰነቀበት፡፡ ከምርጫ 97 በኋላ በህዝቡ ላይ የደረሰው አረመኔያዊ ግፍን የቀላቀለ እርምጃ ያሳደረው የፍርሃት ድባብ ምን የወፈረ ምን የደደረ ቢመስልም ግንቦት ሰባት የፈነጠቀችውን የነፃነት ጉህ ለመሸፈን አልቻለም፡ ፡ የመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ሰላማዊና ስልጡን የነፃነት ጥያቄ ተወደደም ተጠላ፣ የነፃነት ቀን እስከ ሚደርስበት ቀን ድረስ ግንቦት ሰባት ሁለት አይነት መልዕክት ታስተላልፋለች፡፡ አንደኛው መልዕክት በቀጥታ ለአምባገነኑ የኢህአዴግ መንግስት "አፈናው፣ ግፉ፣ ሙስናው ያብቃ" የሚል ሲሆን፤ ይቺ ቀን እውነተኛውን የስብዕና ነፃነት የተለማመድንባት ነበረች፡፡ ሁለተኛው መልዕክት ደግሞ ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ "አጐንብሶ፣ ተጨቁኖ፣ እየተበዘበዙ መኖር ያብቃ" የሚል ነው፡፡ ሚያዝያ 30/1997 በሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝብ ለቅንጅት ያለውን ፅኑ ድጋፍ መስቀል አደባባይ ተገኝቶ የገለፀበትና ዓለምን ያስደመመበት ዕለት ነው፡፡ ግንቦት 7/1997 ዓ.ም ደግሞ ቅዳሜ ለእሁድ አጥቢያ ወደ የምርጫ ጣቢያው የተመመው ህዝብ ኢህአዴግ "ስልጣን በቃህ!" ያለበትና ለዴሞክራሲያዊ ምርጫ የጠነከረ ወገናዊነቱን የገለፀበት በመሆኑ ለዘላለም በኢትዮጵያውያን ዘንድ ልዩ የነፃነት ቀን ሆኖ ይታሰባል፤ ኢትዮጵያውያን በነፃ ምርጫ መንግሥታቸውን ለመምረጥ የደረሱ፤ ስልጡን ህዝብ መሆናቸውንም የሚገልፅ ነበር፡፡ ምንም እንኳን ገዢው ፓርቲ ያነገበውን ነፍጥ ተማምኖ የህዝብን ድምፅ ቢያፍንም ሥርዓቱ ፍፁም አምባገነን መሆኑን ለአለም ህዝብ ማሳወቅ ተችሏል፡፡ ኢህአዴግ በ1997 ዓ.ም ምርጫ ተሸናፊነቱን በፀጋ ተቀብሎ ህዝብ ለመረጠው ፓርቲ ስልጣን ማስረከብ ሲገባው አሻፈረኝ ማለቱና እስከ ዛሬም በስልጣኑ ላይ መቆየቱ ገዢው ፓርቲ የለየለት አምባገነን መሆኑን እንደሚያሳይ ፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ታምናለች፡፡ እንደ ቀበሮ ባህታዊ የዴሞክራሲ ለምድ የለበሰው ኢህአዴግ በግንቦት ሰባቱ ምርጫ ማንነቱ ገሀድ ወጥቷል፡፡ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ለኢህአዴግ አምባገነናዊ ስርዓት ያለውን ጥላቻ ያለ አንዳች ሀይል አስገዳጅነት በድምፅ መስጫ ካርዱ ገልፃ6ል፡፡ በዚህም የኢህአዴግ ጎራ በከፍተኛ ድንጋጤ የራደበትና በታሪኩ ለአሳፋሪ ሽንፈት የተዳረገበት ወቅት እንደነበር የማያስታውሰው ኢትዮጵያዊ አይኖርም፡፡

ህወሓት /ኢህአዴግ የደርግን አምባገነናዊ መንግስት ለመጣል ለ17 ዓመታት ነፍጥ አንግቦ የተዋጋው ዴሞክራሲያዊ ስርዓትን ለማስፈን እንዳልሆነ ከምንም በላይ ከ97 ዓ.ም ምርጫ ይበልጥ ጉልህ ምስክር የለም፡፡ ሥርዓቱ የለየለት አምባገነን በመሆኑ የሕዝብን ድምፅ ረግጦና ከምርጫው ውጤት ውዝግብ ማግስት አያሌ ዜጎችን በጥይት አረር ገድሎ ዛሬም ቤተመንግስቱን የሙጥኝ እንዳለ ነው፡፡ አሁንም ቢሆን ከግንቦት 7 ቀን የምርጫ ሂደት ኢህአዴግ መማር አልቻለም፡፡ "ከድጡ ወደ ማጡ" እንዲሉ የዴሞክራሲውን ጭላንጭል በፅልመት መጋረጃ ከመከለል አልፎ ራሱን በአውራ ፓርቲነት ሰይሟል፡፡

የሥርዓቱ መሪዎች አስተዋይ ቢሆኑ ኖሮ "ህዝብ ለምን ድምፁን ነፈገን? ሕፀፆቻችን ምን ምን ነበሩ?" እያሉ ራሳቸውን (ውስጣቸውን) መፈተሽ ይገባቸው ነበር፡፡ የሕዝብን ድምፅ ረግጠው በጠመንጃቸው ጉልበት ሥልጣን ላይ እንደወጡ ልቦናቸው እያወቀ ከዕለት ዕለት ክንዳቸውን በጉልበትና በሃይል አፈርጥመዋል፡፡ በሚቀጥሉት ዓመታትም በሥልጣን ላይ ለመቆየት ሲሉ በሙስና በመዘፈቅ አገሪቱን ልትወጣው ወደ ማትችለው ማጥ ውስጥ ይዘዋት እየሰመጡ ነው፡፡ ስለሆነም የኢትዮጵያ ሕዝብ በፍርሃት ተሸብቦ እነሱን ተከትሎ አረንቋ ውስጥ መስመጥ እንደሌለበት ከግንቦት መማር ይገባዋል፡፡ በመሆኑም በቅርቡ በሚደረገው የአዲስ አበባ ምክር ቤት ምርጫ እንደ 97 ዓ.ም በካርዱ ትምህርት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ ግፉ ማክተም አለበት፤ ጭቆናው ልክና ቅጥ ሊኖረው ይገባል፡ ፡ ይህ አምባገነን መንግሥት በሕዝብ ድምፅ ሊወገድ ይገባዋል፡፡ ሁልጊዜ ዋይታ፣ ሁልጊዜ ሰቆቃ፣ ሁልጊዜ ከመኖሪያ ቀየ መፈናቀል መቆም አለበት፡፡ በመጨረሻም እሮሮችንና ብሶታችን ያከትም ዘንድ የዚች አገር ዜጎች አንድ ሆነን እንታገል፡፡ አንድነት ኃይል ነውና ለአንድነት ክብርና ዋጋ እንስጥ፡ ፡ ግንቦት ሰባት የኢትዮጵያ ህዝብ ዴሞክራሲን እንደሚሻ፣ መልካም አስተዳደር እንደሚያስፈልገው እና የኢትዮጵያ ህዝብ አምባገነናዊ አገዛዝ እንዳንገፈገፈው ጮክ ብላ ዛሬም ነገም ትናገራለች፡፡

# ነፃ አስተያየት

## ዶ/ር ነጋሶን ምን ነካቸው?

ሚያዝያ 2 ቀን 2004 ዓ.ም 2ኛ ዓመት ቅጽ ቁጥር 38 በወጣው ፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ከገዳ እስከ ኦሕዴዲ ገዳዳ በሚለው ሰፊና በጣም ምስጢርን ፈልፍሎ የገዥዎቻችንን ማንነት ለሕዝብ ባስተዋወቀው ጽሁፍ እንዲታረም የሚንጠይቀው 1 ቶሎሣ ጉደታ ሳይሆን ቶለሣ ገደፋ ጉበና ተብሎ እንዲታረም እንጠይቃለን፡፡

ዶ/ር ነጋሶ ስለኩማ ደመቅሳ ያነሱትም የተምታታ ነው የሚመስለኝ፡፡ እኛ መረጃውን ያገኘነው በአየር ጤና አካባቢ አሁንም ነዋሪ ከሆኑት ከቄስ ተ/ማሪያም ባለቤት ከአቶ ኩማና ግርማ እናት ሲሆን ዶ/ሩ ከምን ተነስተው ነው ተነስተው ሊከራከሩ የፈለጉት? እሳቸው ጀርመናዊት ሚስታቸውን ሲያገቡ የነገር አባት ስለሆናቸው ወይንስ ወደ ኦፒዲዮም ሲገቡ መዝጋቢ ስለሆነ? ከሆነ መረዳዳት በሌላ ይቻላል፡፡ ለማንኛውም እውነታው የሚከተለው ነው፡፡

የኩማ አባት ከትግራይ ተነስተው በጐንደር ወደ ጐጃም በመምጣቱ ከቀሰሱ በኋላ ወደ ደምቢ ዶሎ በመሄድ በኢሉባቡር የሚገኙት አቶ ቶኩን ቤተክርሲቲያን አቋቁመው የሚቀርበላቸው ስላጡ ደምቢ ዶሎ ከሚገኙት አማቻቸው ዘንድ ቄስ ተ/ማሪያም ወደ ኢሉባቦር እንደተላኩ ባለቤታቸው የኩማ እናት እያረጋገጡልን በካሴት የተቀዳ በእጃችን እያለ ዶ/ሩ ኩማን ኦሮሞ ሊያደርጓቸው መሞከራቸው አስገርሞናል፡ ፡

ነፃ ሐሳብ

# ኢፍትሐዊነትንና አድሎን በውርደት ከመቀበል መከራና ስቃይን በክብር ማስተናገዳችንን እንቀጥላለን

አቶ በቀለ ገርባ ከቃሊቲ ማረሚያ ቤት



አቶ በቀለ ገርባ

ነሐሴ 21/2003 ዓ/ም ከምሠራበት ቦታ በስልክ ተጠርቼ በተለምዶ ማዕከላዊ ተብሎ ከሚጠራው የፌዴራል ወንጀል ምርመራ ዘርፍ ተወስጄ ከአንዲት ትንሽ ጨለማ ክፍል ውስጥ ከተወረወርኩ በኋላ በማግስቱ አራዳ ወረዳ ፍ/ቤት ቀርቤ የሃያ ስምንት ቀን የምርመራ የጊዜ ቀጠሮ ተጠይቆብኝ ተፈቅዶላቸው ያም ሲያልቅ እንደገና ሌላ ቀጠሮ ተጠይቆ ተፈቅዶላቸው፣ የማይመለከቱኝን ጥያቄዎች ስጠየቅና ስመልስ ቆይቼ ጥቅምት 3/2004 በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት 3ኛ ወንጀል ችሎት ቀርቤ የክስ ወረቀት ደርሶኝ ወደ ቃሊቲ ማረሚያ ቤት ተልኬ እነሆ እስከዛሬ ድረስ ዞን አንድ ቅጣት ቤት ተብላ በምትጠራው ቤት እገኛለሁ፡፡

የቀረበብኝ ክስ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 241 የተመለከተውን በመተላለፍ የአገሪቱን የፖለቲካና የግዛት አንድነት በመንካት ወንጀል ሲሆን ዝርዝሩ፡- "የኦሮሞ ነፃነት ግንባር /ኦ.ነ.ግ/ አባል በመሆን ሶሎሎ ጐልቦ ሥልጠና ወስደሃል፤ በጥር ወር 2002 ዓ/ም በአምቦ ከተማ ኦ.ነ.ግ በቅርብ ወደ አገር ውስጥ አሸንፎ ይገባል፤ ከጐኑ ቆመን በሥልጣን ላይ ያለውን መንግስት መጣል አለብን ብለህ መመሪያ ሰጥተሀል፤ በሐምሌ 2003 ዓ/ም ተማሪዎችንና ህዝቡን ለአመጽና ለብጥብጥ እንዲነሳሱ ቅስቃሳ አካሂደሀል፤ እንዲሁም በ2004 ዓ/ም በመላው ኦሮሚያ አመጽና ብጥብጥ በማስነሳት በሥልጣን ላይ ያለውን መንግሥት መጣል አለብን በማለት ትዕዛዝ አስተላልፈሀል፤ በዚሁ ወር የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህርነትህን ሽፋን በማድረግ ቢሮህ ተገኝተው የመመረቂያ ጽሁፍ ሊሰጡህ የመጡትን ተማሪዎች በሥልጣን ላይ ያለውን መንግስት በሃይል ከሥልጣን እናውርድ በማለት መመሪያ ሰጥተሀል" የሚል ነው፡፡

እነዚህ የቀረቡብኝ ክሶች ፈጽሞ የሀሰት ውንጀላዎች መሆናቸውን ለማስረዳት በመጀመሪያ ደረጃ ትጥቅ ትግልና ሰላማዊ ትግልን አስመልክቶ ያለኝን አቋምና እምነት ባጭሩ ከገለጽኩ በኋላ በቀረቡብኝ ምስክሮችና የሠነድ ማስረጃ ላይ ያሉትን እውነታዎች አቅርቤ በአጭሩ የማጠቃለያ ሀሳብ እደመድማለሁ፡፡

1.የትጥቅ ትግል በአንድ ወገን ድል አድራጊነት የሚጠናቀቅ እንደመሆኑ አሸናፊውን ወገን ክብርና የበላይነትን ሲያጐናጽፍ ተሸናፊውን ወገን ደግሞ የውርደትና የበታችነት ስሜት ይፈጥርበታል፡፡ በዚሁ የተነሳ ተሸናፊው ወገን ቂም አርግዞ ጊዜውን ጠብቆ አድፍጦ የሚያደባበት ስለሆነ እውነተኛ ያልሆነ አሉታዊ ሠላም የሰፈነበት ነው፡፡ ፖለቲካውም የምሬት፣ የጥላቻ የበቀልና የጠላትነት ስለሚሆን እስራት፣ ስደት፣ ከሥራ መፈናቀልና ሌሎች ምስቅልቅሎችን ያስከትላል፡፡ ይህን የትግል ዘዴ በታሪካችን ደጋግመን ሞክረነዋል፡፡ መዘዙንም ቀምሰነዋል፤ ለኋላ ቀርነታችን አንደኛው ምክንያት ሆኗልና፡፡ በአንፃሩ ግን ሠላማዊ ትግል አሸናፊና ተሸናፊ ስለሌለው መቋጫው እርቅ ወንድማማችነትና ዘላቂ ሰላም ነው፡፡ አውንታዊ ሠላም ፖለቲካውም ልዩነትና ብዙሀንነት ስለሚያስተናግድ የሚማረር ወገን አይኖርም፡፡ ስለዚህ ተመራጭ ብቻ ሳይሆን ብቸኛ የትግል ዘዴ መሆን አለበት የሚል እምነት ስላለኝ ህጋዊ በሆነ የፖለቲካ ድርጅት ውስጥ በመሳተፍ የድርሻዬን በማበርከት ላይ እገኛለሁ፡፡

2.የትጥቅ ትግል አሸናፊው ቡድን የአልበገር ባይነት ስሜት እንዲሰማውና እብሪተኛና ጨካኝ እንዲሆን ከማድረጉም በላይ ድሉን ለማግኘት ለከፈለው መስዋዕትነት ካሳ ፈላጊ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ በዚህ ምክንያት ሥልጣንንና የሀብት ምንጮችን ጨምድዶ በመያዝ በትግሉ ያልተሳተፉትን በማግለል ፍትሀዊ ክፍፍልን አዛብቶ የዜጐችን የእኩልነት መብት ወደ መርገጥ ያመራል፡፡ ውሎ ሲያድርም ይህን ስህተቱን ማረም ስለሚሳነው የሃሳብ ልዩነትን የማይቀበል አምባገነን ይሆናል፡፡ በዚህ ምክንያት መብታቸውን የሚጠይቁ ዜጐችን በጠላትነት ፈርጆ ሊያጠፋቸው ሕጋዊ የሚመስል ህገወጥ ድርጊቶችን በስውርና በግልጽ በመፈጸም ለሌላ ትጥቅ ትግል በር ይከፍታል፡፡ ይህን የትጥቅ ትግል ዑደት አንድ ቦታ ላይ ሰብሮ በማቆም አገሪቱን ከትርምስና የመገዳደል ባህል መታደግ የሚቻለው ራሳቸውን ለአደጋ አጋልጠው ሳይገድሉ እየሞቱ እየታሠሩና ከሥራ እየተፈናቀሉ በሠላማዊ መንገድ ብቻ በሚታገሉ ኃይሎች አማካኝነት ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ መርጬ እየተጓዝኩበት ያለሁትም ይህን ነው፡፡

3.የትጥቅ ትግል ሰብዓዊና ቁሳዊ ሀብትን ከማውደሙም በላይ ጊዜያዊም ቢሆን ሥርዓተ አልበኝነትን ያስከትላል፡፡ በጣም ውስን በሆነች የሀገር ሀብት አንዱ የገነባውን ሌላው እያፈረሰ የሚሄድ ከሆነ መጨረሻችን የት ሊሆን እንደሚችል መገመት አያስቸግርም፡፡ የትጥቅ ትግል ለዜጎች ስንዴና ዘይት እንኳን ማቅረብ የማይቻል እንደኛ ያለ አገር ቀርቶ የሚዋጉበት በጦር መሳሪያ ለሚያመርቱ አገሮች እንኳን አዋጭ ስላልሆነ ዘለው አይገቡበትም፡፡ ብጥብጥና ሁከት በሚነሳባቸው አገሮች ዋነኞቹ ተጐጂዎች ተራ ዜጎች እንጂ እንደከሳሾቼ ያሉ ባለሥልጣናት ወይም የመንግሥት መሪዎች አይደሉም፡፡

በኛ አገርም ይህ ሁኔታ ቢከሰት ግንባር ቀደም ሰለባ መሆን ከሚችሉት ውስጥ እኔና ቤተሰቤ እንገኛለን፡፡ ምክንያቱም የምጓዘው በተራ ትራንስፖርት፤ የምኖረው በተራ መንደር በተራ ቤት፣ ልጆቼ የሚማሩት በተራ ትምህርት ቤት ሲሆን ከሳሾቼ ግን ይህ ሁሉ የማይመለከታቸውና የማያስጋቸው በመሆኑ ከነሱ የበለጠ ሠላም ለኔ ትልቅ ዋጋ አለው፡፡ ስለዚህ ነው ምንም ዓይነት ዜግነት፣ ቀለም ወይም ዘር ይኑርው ሰብአዊና ቁሳዊ ውድመትን የሚያስከትል ጦርነትም ሆነ ብጥብጥ ከሚራምድ አካል ጋር የማልተባበረው

4.በትጥቅ ትግል ወደ ሥልጣን የሚመጡ መንግስታት ከውይይትና ድርድር ይልቅ በኃይል መፍትሔ ስለሚያምኑ ዴሞክራሲያዊ አካሄድን ከማቀጨጭ አልፎ እስከነአካቴው ይፃረራሉ፡፡ ለይስሙላ በሚገኙባቸው የድርድር መድረኮችም ሌላም ወገን እንዲቀበል የሚፈልጉትን ለመንገር እንጂ ሰጥቶ ለመቀበል ስላልሆነ በድርድሩ ማግስት ወደ ቀድሞ የኃይል ተግባራቸው ይመለሳሉ፡፡ ህዝቡ የጦር ሜዳ ገድሎቻቸውን አይቶና ሰምቶ አይበገሬነታቸውን ተረድቶ በፍርሃት እንዲገዛላቸው ሚዲያውን በጦርነት ወሬ ያደምቃሉ፡፡

በሰላማዊ ትግል አግባብ ስልጣን የሚይዙት ግን የስልጣናቸው ምንጭ የሆነው ሕዝብ ጥቅሙና መብቱ ካልተጠበቀለት ነገ ደግሞ ለሌላ መስጠት እንደሚችል ስለሚገነዘቡ ዜጐቻቸውን ያከብራሉ፤ ከመፍራት ይልቅ መከበርን ይሻሉ ከመናገር ይልቅ ማዳመጥን ያስቀድማሉ፡፡ እውነተኛ ዴሞክራሲን በማስፈን ሕዝባቸውን ወደ ዘላቂ ሰላምና እድገት ይመራሉ፡፡ እንደዚህ ዓይነት ሰላማዊ ትግል ነው እንዲካሄድ የምሻውና ዋጋ እየከፈልኩበት ያለው፡፡

5.በእምነት ዝንባሌዬ ነፍስ የፈጣሪዋ ብቻ ስለሆነች የሰውን ልጅ ነፍስ ማጥፋት ከወንጀል አልፎ ኃጢአት መሆኑንና ይህን ክቡር ነገር በኃይል ከሰው የሚነጥቁ ሁሉ በተመሳሳይ መንገድ እንደሚነጠቁ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ "ሠይፍ የሚመዙ በሠይፍ ይጠፋሉ" የሚለውን መለኮታዊ ቃል አምናለሁ፡፡ ስለዚህ የኃይል ተግባርን እንደአማራጭ ወስጄ አላውቅም፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ፈጣሪ እውነት ነው፤ በፈጣሪ የሚያምን ሁሉ እውነትን ያመነ ማለት ይገባዋል፡፡ "እውነትን ሲሻና ለፍትህ ሲከራከር በፍቅር ብቻ ማድረግ አለበት" የሚለውን የጋንዲ "ሳትያግራሀ" ፍልስፍና እቀበላለሁ፡፡ "ሳትያግራሀ" "የእውነት ኃይል፤ የፍቅር ኃይል" ማለት ሲሆን ጥቃት ለሚሰነዝር ሰው አፀፋ ሳይመልሱ በፍቅር ቀርቦ በውስጥ ያለውን መልካም ነገር በማንቀሳቀስ በህሊና ወቀስ ከክፉ ሥራው እንዲመለስ ማድረግ ይቻላል፡፡ የሚል ፍልስፍና ነው፡፡ ይህ የሰላማዊ ትግል የመጨረሻ ተሞክሮ በሰላማዊ ታጋዩ ወይም ሳትያግራሂው ላይ ከፍ ያለ ሥቃይን የማያስከትል እንደመሆነ በአስተሳሰቦች በሞራላዊነታቸውና በትዕግሥታቸው የላቀ ደረጃ ላይ የደረሱ ሰዎች ብቻ የሚተገበሩት ነው፡፡ ከሳትያግራሀ የሰላማዊ ትግል ስልቶች አንዱና ዋነኛው ከክፉ ሥራ ጋር ያለመተባበር ነው፡፡ እኔም አንድን ዓላማ ለማሳካት ኃይልን ከመጠቀም የበለጠ ክፉ ነገር አለ ብዬ ስለማስብ ከእንዲህ አይነት ተግባር ጋር ተባብሬ አላውቅም፡፡ እንግዲህ ትጥቅ ትግል ውስጥ ያልተሳተፍኩት እላይ በጠቀስኳቸው ምክንያቶች እንጂ በማንምና በምንም ፍራቻ አሊያም አጋጣሚ አጥቼ አልነበረም፡፡ ከሳሾቼ እንደሚሉት ልጆች ሳላፈራና በትምህርት ሳልገፋ በአፍላ የወጣትነት ጊዜዬ ያላሰብኩትን ድንገት በሃምሳኛ ዓመት እድሜዬ ላይ በተራ የኦ.ነ.ግ ተዋጊነትና ካድሬነት ለመሠልጠን ኬንያና ሰሎሎ አልሄድኩም፡፡

ነፍስ ካወቅሁ ጊዜ ጀምሮ የሰው ልጆች መብት እንዲከበር ጽኑ ፍላጎና አቋም የነበረኝ ቢሆንም ሁሉም ሰው ፓለቲከኛ መሆን አለበት የሚል እምነት ስላልነበረኝ እስከ 2002 ዓ/ም ድረስ የማንኛውም ፖለቲካ ፓርቲ አባል ሆኜ አላውቅም፡፡ ተሰጥኦውና ዝናባሌው ያላቸው ጥቂቶች የፖለቲካ ማህበር መስርተው ለስልጣን ተወዳድረው ህዝባቸው በፍትሀዊነት ማስተዳደር ከቻሉ ሌሎች ዜጐች በተለያየ ሙያ ተሰማርተው አገራቸውን ማገልገል አለባቸው ብዬ ስለማምን እኔም በመምህርነት ሙያ ብቻ ተሰማርቼ ተግባሬን በትክክል ስወጣ ኖሬያለሁ፡፡

ይሁን እንጂ የፖለቲካ ድርጅቶች የሰዎች ስብሰብ እንደመሆናቸው መጠን ሁሉን ነገር ያለእንከን ይፈጽማሉ ብሎ ማመን ስለማይቻል ጊዜ ሊሰጣቸው እንደሚገባ በመረዳት ኢትዮጵያን እያስተዳደረ ያለው ፓርቲ የሚሰብከውን መተግበር እየተሳነው ሲሄድ ወይም በተፃራሪው ሲተገብር ሆን ብሎ አለመሆኑን ለራሴ ለማሳመን ሃያ አመታት ያህል ጥረት አድርጌያለሁ፡፡ በመጨረሻም በመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ላይ በተለይ ደግሞ በኦሮሞ ሕዝብ ላይ የሚደርሰውን በደል ዝም ብሎ መመልከትን ህሊናዬ አልቀበል አለኝ፡፡

- ሦስት መቶ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ጥያቄ እንኳን ሳይቀርብላቸው በአንድ ቀን ሲባረሩ
- በየዩኒቨርስቲው ያሉ ሌሎች ደግሞ በየዓመቱ ሲደበደቡና ሲንገላቱ
- የፋብሪካ ዝቃጭ አተላዎች በማንአለብኝነት ህዝብ ወደሚጠጣቸው ወንዞች ሲለቀቁና አደጋ ሲያስከትሉ
- ለፌዴራሉ መንግስት ከፍተኛውን ገቢ የሚያስገባ ህዝብ በአንፃሩ ግን በነፍስ ወከፍ እጅግ ዝቅተኛው የፌዴራል በጀት ድጐማ ሲመደብለት
- መሬቱ በሰበብ አስባቡ በግፍ እየተወሰደ ተቸብችቦ ሌሎችን ባለፀጋ ሲያደርግ፤ የሱ ቤተሰቦች ግን የትም ሲበተኑ
- ቋንቋው ቀድሞ ሲነገር ከነበረበት ቦታ እየጠፋ ሲሄድ
- ከኤኮኖሚው ዘርፍ ወጥቶ የበይ ተመልካች ሲሆን
- የዛሬ 120 ዓመት የኦሮሞ መንደር በነበረቸው ፊንፊኔ በቋንቋው የሚማርበት አንድ ት/ቤት ወይም አንድ የእምነት ሥፍራ እንኳ ሲነፈገው
- የፌዴራል ሠራተኞች ቅጥርና የመከላከያ ሠራዊቱ አመራር ብሔራዊ ተዋጽኦ አግባብ ባልሆነ መልኩ ሲከናወን
- ከሁሉም በላይ ደግሞ ገዥው ፓርቲ ሥልጣን ሲይዝ በእስር ቤት ከነበሩ ኦሮሞ፣ ዛሬ በብዙ እጥፍ የሚሆኑት በፌዴራል ወህኒ ቤቶች ሲማቅቁና ቤተሰቦቻቸው በረሃብ አለንጋ ሲገረፉ እያየሁ ዝም ማለት እንዴት ይቻለኛል?

እነዚህ ነገሮች እንዲስተካከሉ ህገ መንግስቱ በሚፈቅደው መሰረት በሠላማዊ መንገድ አስተዋፅኦ ለማድረግ የአንድ ፓርቲ አባል መሆንን ሳውጠነጥን የኦሮሞ ፌዴራሊስት ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ /ኦ.ፌ.ዴ.ን/ ጥሪ አድርጐልኝ በ2002 ዓ/ም ለመጀመሪ ጊዜ አባል ሆንኩ፡፡ ከዚያም የድርጅቱ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባልና የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል ሆንኩ፡፡ በ2002 ዓ/ም ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ዕጩ ተወዳዳሪ ሆኜ መላው ሕዝባችን በሚያውቀው ሁኔታ ተሸነፍኩ፡፡ በምርጫ ዘመቻ ወቅትም በግልና በቡድን የተካሄዱብኝን ትንኮሳዎች ተቋቁሜ መንግሥት ባሰማራቸው ሁከት ፈጣሪዎች መካከል ቆሜ ለሠላማዊ ትግልና ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እውን መሆን ያለኝን ቁርጠኝነት አስመስክሬያለሁ፡፡ ምርጫውን እንደማላሸንፍና መጨረሻዬም አሁን ያለሁበት እስር ቤት እንደሆነ እየተነገረኝ አንድ ሰላማዊ ታጋይ ማድረግ ያለበትን አድርጊያለሁ፡፡

በፓርቲዬ ውስጥ በተሰጠኝ የሕዝብ ግንኙነት የሥራ ድርሻ ምክንያት በእስር ላይ ስላሉ ኦሮሞዎች ሁለት ጊዜ ያህል ለውጪ ሚዲያዎች ቃለ መጠይቅ በመስብሰብ ከሳሾቼን እንዳላስደስታቸው ከራሳቸው ተነግሮኝ ነበር፡፡ ነገር ግን የሰጠሁት መረጃ ሀሰትም፣ ምሥጢርም እንዳልሆነ ነግሬያቸው በተያየን በሃያ ቀናት ከቢሮዬ ተጠርቼ ታሰርኩ፡፡ ከመታሰሬ ጥቂት ቀናት በፊት ከአምነስቲ ኢንተርናሽናል የመጡ ሰዎች አነጋግረውኝ ነበር፡፡ የእነዚህ ነገሮች ድምር ነው "የአገርና የሕዝብን አንድነት በማፍረስ" ወንጀል አስከስሶ ለእስራት የዳረገኝ፡፡

በሕዝቦች መካከል ግልጽ ልዩነት እየፈጠረ አንዱ ሌላውን እንዲጠራጠር ኅብረቱ እንዲላላና አንድነቱ እንዲፈርስ እያደረገ ያለ ሥርዓቱ ነው ወይስ ይህ ሁኔታ እንዲስተካከል በሰላማዊ መንገድ እያሳሰበ በመታገል ላይ ያለ ሰው ነው የአገሪቱን የግዛትና የፖለቲካ አንድነት በማፍረስ ወንጀል የሚጠረጠረው? ህገ መንግሥቱን በተግባር እየጣሰ ያለውስ መብቴ ይከበር የሚለው ነው ወይንስ መብቱን የገፈፈው ነው?

ድርጅታችን በኢ.ፌ.ዴ.ን ህዝቦች መብታቸው እስከተከበረላቸው ድረስ የመገንጠል ጥያቄ አያነሱም መለየትንም አይፈልጉም የሚል እምነት ስላለውና የአገር አንድና ቁልፍ እውነተኛ እኩልነት የሰፈነበት ሥርዓት ማስፈን መሆኑን ያምናል፡፡

ስለዚህ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግሥት አንቀጽ 39 ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ ያለው እስከመገንጠል የሚለው ሀረግ ጠቃሚ አይደለም በሚል እምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክረሲያዊ አንድነት መድረክ መለስተኛ የፖለቲካ ፕሮራም ውስጥ እንዲካተት ከፈረሙት አባል ድርጅቶች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ እኔም የድርጅቱ አባልና አመራር ይህን ለማሳመን ጉንበስ ቀና በምልበት ሰዓት የአገር አንድነትን ለማፍረስ በመሞከር እንዴት ልከሰስ እችላለሁ?

ማንኛውም ኦሮሞ መብቱን የመጠየቅ አዝማሚያ ወይም ከሥርዓቱ ጋር ያለመተባበር ዝናበሌ ያሳየ እንደሆነ በኦነግነት ፈረጀ ማናቸውንም የግፍ ተግባር መፈፀም ከተጀመረ ሃያ አመታት ተቆጠሩ፡፡ ይህ አድራጎት በአፍሪካ ደረጃ እንኳን ሲታይ ወደር የለሽ ነው፡፡ ናይጀሪያ በየጊዜው ፍንዳታ እያደረሰ ኃላፊነት በሚወስደው የቦኮሃራም ድርጅት አግባብ ተመሳሳይ ቋንቋ የሚናገሩና ተመሳሳይ እምነት የሚከተሉ ዜጐቿን ቁም ስቅል አላሳየችም፡፡ የወደቀው የግብጽ መንግስት እንኳን ህገወጥ ነው ብሎ በፈረጀው የሙስሊም ወንድማማቼች ፓርቲ አመካኝቶ ተቀናቃኞችን ለማጥፋት ዘመቻ አልከፈተም፡፡ ከአንድ የዘር የተገኘ ሁሉ አንድ አይነት የፖለቲካ አመለካከት አለው ብሎ የሚገምት ቢኖር በሥልጣን ላይ

ወደ ገፅ 15 ይዞራል....




# የኢትዮጵያ መምህራን ጥያቄና የትምህርት ሥራ (3)

## በ10 ዓመት ጊዜ የታዩት ለውጦች ለመምህራን ፋይዳ አላቸው?



ገሞራው ካሣ

ከ1994–2004 ባለው ጊዜ የደሞዝ ማስተካከያና የመምህራን የእድገት መሰላል፣ የመንግሥት ሠራተኞች ደሞዝ ጭማሬ እና የመምህራን ደሞዝ እስኬል ማሻሻያ በሚል ይብዛም ይነስ ለውጥ ተድርጓል፡፡ ምንም ስም ይሰጠው የመምህራን ቀልብ የሚያርፈው ምን ያክል ብር በነበራቸው ደሞዝ ላይ እንደተጨመረ ማየቱ ላይ ነው፡፡ ችግራቸው ጊዜ አይሰጥም፡፡ ችግር የማይፈታ የደሞዝ ጭማሪ ደግሞ ከውለታ አይቆጠርም፡፡ እንደውም ሊያስኮርፍ ይችላል፡፡ «እንዳያማህ ጥራው እንዳይበላ ግፋው» ነው፡፡ ከብሩ የመግዛት አቅም በየጊዜው ማሽቆልቆልና የዕቃዎች ዋጋ እለት በለት እያሻቀበ ከመሄዱ አንጻር በ10 ዓመት ከታዩት ለውጦች አንዳቸውም የመምህራንን ህይወት የመለወጥ አቅም የላቸውም፡፡ መምህራን የሆዳቸውን በሆዳቸው ይዘው ልግፋው ብለው ቢጨክኑም የማይገፋ ህይወት ነው የገጠማቸው፡፡ እስቲ ቀረብ ብለን ከሰንጠረዥ 2 ጓዳቸውን እንየው፡፡ የጀማሪ መምህራን መነሻ ደሞዝ ለአስረጂነት የተመረጠው ለሥራ መደቡ በህግ የተተከለ ሁሉም መምህር በውስጡ የሚያልፍበት አነስተኛው ደሞዝ ስለሆነ ነው፡፡

በ1994 የተጀመረው የመምህራን የደረጃ እድገት መሰላል ስም እንጂ ቁሳዊ ጠቀሜታው እዚህ ግባ የማይባል ከመሆኑም በላይ ከችሎታና ታታሪነት ይልቅ የፖለቲካ ታማኝነት ስላጠላበት የታሰበውን ግብ አልመታም፡፡ ከታች ከተሰጠው ሰንጠረዥ 2 እንደሚነበበው በጥር 2003 መምህራን ከ35-39% ልዩ ጭማሪ እንደገናም በሚያዚያ ወር 2004 የተገለጸላቸው የመምህራን የደሞዝ እስኬል ማሻሻያ ሥርአት ከተደረገ በኋላ የአንድ የመጀመሪያ ደረጃ (1-8 ት/ቤት) መምህር መነሻ ወርሀዊ ደሞዝ ብር 1233 ነው፡፡ በጥር ወር 2003 በተደረገው ጭማሪ ብር 1172 ስለሆነ ከነሀሴው ልዩነቱ ብር 61 ነው፡፡ ይህ ሰው በትንሹ ሦስት ልጆች ቢኖሩት ከነሚስቱ አምስት ቤተሰብ ይሆናል፡፡ ጤፍ፣ ቅቤ፣ ሥጋ፣ አትክልት፣ ፍራፍሬ ለዚህ ቤተሰብ ዛሬ አይታሰብም፡፡ እንደ ቅንጦት ምግብ ይቆጠራሉ፡፡ እንደውም መገዛት ያለበትን ቀለብ መጠንና ዓይነት የሚወስነው በጁ ላይ ያለው ገንዘብ እንጂ ቤተሰቡ በቀን በሳምንት መመገብ የሚኖርበት መጠንና ዓይነት ለወር ተሰልቶ መሆኑ ከቀረ ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ ሰንጠረዥ 3 ከሞላ ጎደል አሁን ያለውን ለመኖር መሠረታዊ የሆኑ የምግብ ምርቶች ዋጋ በአዲስ አበባ ከተማ ያሳያል፡፡ በክልል ከተሞችም ብዙ የዋጋ ልዩነት አይታይም፡፡ ጥቂት የሚቀንሱ ቢኖሩም የሚጨምሩም ስላሉ በሀገር አቀፍ ደረጃ ለሚመዘን ነገር እዛው በዛው የሚካካስ ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ ይህ መምህር (ባለ 1233 ብር የወር ደሞዝተኛው) የሥራ ግብር ታክስ ተቆርጦለት፣ ከቤት ኪራይና ካለፈው ወር ብድር ክፍያ በተረፈችው ብር ስንት ኪሎ ገብስ፣ ስንዴ፣ ሽሮ፣ በርበሬ ሽንኩርት ምን ያክል ሊትር ዘይት ለወር ፍጆታ መግዛት ይችላል? ሳሙና፣ ውሃ፣ መብራት ፣ ስልክ፣ የእድር ክፍያ፣ ልብስ ያልቃል፣ የጤና ችግር ሊገጥም ይችላል፣ ወዘተ ምኑን ከምን ማድረግ ይቻለዋል?

ሠንጠረዥ 2፡- በየደረጃው ያሉ የጀማሪ መምህራን መነሻ ደሞዝ ከ1994– 2004 በዕኛ አቆጣጠር

| ተ.ቁ. | የሥራ መደቦች | የት/ቤት ደረጃ | መነሻ የወር ደሞዝ በብር | ዘመኑ/ዓ. ም. |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 1ኛ ዙር የመጀመሪያ ደረጃ | 1-4 ክፍል | 305 | 1994 |
| | 2ኛ ዙረ የመጀመሪያ ደረጃ | 5-8 ክፍል | 445 | |
| | የመጀመሪያ ዲግሪ | 2ኛ ደረጃና መ/ማሰልጠኛ | 636 | |
| ምንጭ፡- Ethiopian Ministry of Education, Teachers' Salary Increment and Rank Promotion Declaration,1994 | | | | |
| 2 | ለሁሉም መምህራን ከ35-39% የደሞዝ ጭማሪ በመደረጉ | | | ጥር 2003 |
| | የመጀመሪያ ደረጃ (የአገልግኖት ዓይነት) | እጥ 7 የርከን ደሞዝ 1 | 1172 | |
| | የ2ኛ ደረጃ (የአገልግሎት ዓይነት) | እጥ 9 የርከን ደሞዝ 1 | 1571 | |
| | | | | |
| 3 | የመምህራን፣ የርዕሰ መምህራን እና የሱፐርቫይዘሮች የደሞዝ እስኬል ማሻሻያ በመደረጉ | | | |
| | የትምህርት ቤቱ ደረጃና የሥራ መደቦች | | መነሻ ደሞዝ | ነሀሴ 2003 (ይፋ የተደረገው ሚያዚያ 2004) |
| | ጀማሪ መምህር (ዲፕሎማ) | 1ኛ -8ኛ ክፍል | 1233 | |
| | ጀማሪ መምህር (ዲግሪ) | 9ኛ-10ኛ ክፍል | 1644 | |
| | ጀማሪ መምህር (ማስተርስ) | መሰናዶ (11ኛ-12ኛ ክፍል) | 2131 | |

ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር - ለተራ ቁጥር 2 የምንግሥት ሠራተኞች የደሞዝ እስኬል (ጥር 2003 ዓ. ም.) እና ለተራ ቁጥር 3 የመምህራን፣ የርዕሰ መምህራን እና የሱፐርቫይዘሮች የደሞዝ እስኬል (ነሀሴ 2003 ዓ. ም.)

በአራዳዎች ቋንቋ ቁምራ (ቁርስ፣ ምሳ፣ እራት) ለአዋቂዎች እያሰለሰ ታስቦ እንዲውል፣ ለህፃናት ከሦስት ሁለቱ በፈረቃ በየቀኑ እንዲሰጥ የሚለውን ፌዝ መሰል የብሶት ሐረግ ይህ መምህር (ባለ 1233 ብር የወር ደሞዝተኛው) አይጋራውም ማለት ይከብዳል፡፡ የመከራ ሕይወት መግፋት ማለት ይሄው ነው፡፡ አንድ እራሱን ሆኖ የሚኖር መምህርም ቢያበስል፣ ሆቴል ቢመገብ ዞሮ ዞሮ ሂሳቡ እዛው ነው፡፡ እሱ (መምህሩ) ከነቤተሰቡ በዚህ ዓይነት እየተራበና እየታረዘ ከርሱ የባሱ ወይም እንደሱው የሚጎሳቆሉትን እያየ ሊጽናና አይችልም፡፡ መምህር ነውና የችግሩን ምንጭ ብቻ ሳይሆን መፍትሄውንም ጠንቅቆ ያውቀዋል፡፡ የቀለም ልጆቹና ወላጆቻቸው ብሶቱን ይጋሩታል፡፡ ወደው አይደለም፣ ከላይ እንደጠቀስኩት የራሳቸው ጉዳይ ስለሆነ ነው፡፡ ለዚህም ነው መንግሥት በመምህራን ጥያቄ ላይ ሁለት ሦስት ጊዜ ሊአስብበት ይገባል እየተባለ ውትወታው የጠናው፡፡ በታማኝነታቸው ለሥልጣን የበቁና ለመንግሥት መረጃ አቀባዮችም በመሬት ላይ ያለውን እውነታ እንጂ አለቃ መስማት የሚፈልገውን እየለቀሙ ቢነግሩት (ቁጡ ባለስልጣኖች የዚህ ዓይነቱ ችግር ሰለባዎች የሚሆኑ ይመስለኛል) ጉዳት እንጂ ምንም ጥቅም እንደሌለው ሊአውቁና ሊታረሙ ይገባል፡፡ የእውነት ሚዛን ሲደፋ አለቃና ምንዝር ብሎ ነገር የለም፡፡ ሁሉም የተጠያቂነት ድርሻውን ማንሳቱ የማይቀር ነው፡፡

መምህራን የሙብት ጥያቄ ባነሱ ቁጥር በየዘመኑ መጠነኛ ለውጥ በመንግሥት ሲደረግ ነበር፡፡ አሁንም ይብዛም ይነስ ለውጥ ስለመደረጉ ከላይ አይተናል፡፡ አንድም ጊዜ

ወደ ገፅ 14 ይዞራል....

መ/ር ቀለሙ ሁነኛው

Kelemhun@yahoo.com

# የአቶ መለስ ሦስት ትልልቅ ፍርሀቶች

የሰው ልጅ ምን ቢጀግን ጥቂት ፍርሃት በውስጡ ትኖራለች፡፡ ይህች ቅንጣት ፍርሃት በእድሜ ርዝማኔ እያቆጠቆጠች ጀግንነቱን ልትሸረሽረው ትችላለች፡፡ "የውሃ ጠብታ አለትን ትበረብራለች" እንዲሉ፡፡ ከሁሉም በላይ የሰው ልጅ አይቀሬውን ሞት ይፈራል፡፡ ምን ቢቸገሩ ምድራዊ ህይወት ታጓጓለች፡፡ የኢራቁ ሳዳም ሁሴን በአሜሪካ መራሹ ህብረ ብሄር ጦር ላይ ሲፎክሩ ከርመው በመጨረሻው ከተሸሸጉበት ጉድጓድ ወጥተው በስቅላት የሞትን ፅዋ ተጎነጩ፡፡ ቅምጥሉ ሙአመር ጋዳፊ ተቃዋሚዎቻቸውን "በረሮዎች፣ አይጦች . . ." እያሉ ሲዝቱባቸው ቆይተው ተሸሽገው ከነበረበት የውሃ መውረጃ ቱቦ ውስጥ ሲያዙ "Don't kill me" ሲሉ በፍርሃት ተንቀጠቀጡ፡፡ ወኔ ከዳቸውና ሞታቸው የተራ ወሮበላ ሞት ሆነ፡፡ ሞትን ፈርተው መኖርን ቢመኙም በነገሱባቸው ረጅም አመታት የሰሩት ግፍና ኢ-ሰብአዊ ተግባር ህይወትን ነፈጋቸው፡፡

በአለማችን ላይ ብዙዎች ራሳቸውን በሞት ይቀጣሉ፡፡ በህይወት ሳሉ ከመሰቃየት ለዘዓለለም መሰናበት ዕረፍት መስሎ ይታያቸዋል፡፡ በኢትዮጵያውያን ዘንድ የምን ጊዜም ጀግናችን አድርገን የምናስባቸው አፄ ቴዎድሮስ በጠላት እጅ መውደቅን ፈርተው ሞትን ደፈሩ፡፡ በውርደት ከመኖር በሞት መሰናበትን መረጡ፡፡ "ስም ከመቃብር በላይ ይውላል" እንዲሉ ስማቸው ምንጊዜም ህያው ሆኖ ይኖራል፡፡

ሕወሓት/ኢህአዴግን ከሦስት አስርት ዓመታት በላይ የመሩት ጠቅላይ ሚ/ር መለስ ዜናዊ በ17 ዓመታት መራር ትግል ውስጥ የነበራቸውን ሚና በተመለከተ አያሌ ፀሐፍት ብዙ ብለዋል፡፡ የትግል አጋሮቻቸው ይመሰክራሉ፡፡ አቶ መለስ በጦር ግንባር ላይ በመሰለፍ ረገድ የነበራቸው ድርሻ ኢምንት እንደሆነ ይነገራሉ፡፡ ጠብመንጃ ደግነው ምላጭ የሳቡባቸው ወቅቶች ከፍ ሲል ከነ ጄኔራል ሀይሎም አርአያ ዝቅ ሲል ደግሞ ከነታምራት ላይኔና ተፈራ ዋልዋ ተርታ አያሰልፋቸውም፡፡ እሳቸው ትናንትም ሆነ ዛሬ የፖለቲካው ቁማር ዘዋሪ ናቸው፡፡ የቀበሮ ጉድጓድ ውስጥ መሸገው የእነ ማኪቬሌንና የእነ ማኦሴቱንግን ፍልስፍና የሚያጠኑ ተጋዳላይ ነበሩ፡፡ በወቅቱ ለፍርሃት የሚዳርጓቸውን ነገሮች ለማስወገድ ጊዜ አያባክኑም፡፡ ዛሬም ቢሆን ከጨዋታ ውጭ ማድረግን ተክነውበታል፡፡

ፍርሀት አንድ፡- ዘፈንና ዘፋኞችን (ሙዚቃ) መፍራት

የጥንቶቹ ነገስታት በጦር ሜዳ ውሏአቸው ለሚያስመዘግቡት ድል ሽለላና ፉከራ ወኔ አቀጣጣይ መሣሪያዎች ናቸው፡፡ ጀግኖች አባቶቻችን እየሸለሉና እየፎከሩ በዋሉበት የጦር ሜዳ ድልን ዘክረዋል፡፡ ሕወሓት ሽምቅ ተዋጊዎች የጀግና ዘፈን ሞተራቸው ነበር፡፡ በተፋፋመ ጦርነት ላይ እያሉ ከበስተኋላ የሚሰሙት የከበሮ ድምፅና የክራር ቅኝት እንዲሁም ዘፈን ደረታቸውን ለጥይት እንዲሰጡና ጥለው እንዲወድቁ ያጀግናቸው ነበር፡፡ በጦሩ መሀል የሚቋቋሙት የኪነት ቡድኖች ከተዋጊው ጀርባ ጠብመንጃ ካነገበው ሽምቅ ተዋጊ የማይተናነስ የጀግንነት ተግባር ፈፅመዋል፡፡

ወታደራዊው ደርግም ከወያኔና ከሻዕቢያ ጋር በነበረበት ጦርነት ይህንን ለመጠቀም ሞክሯል፡፡ በየክፍለ ጦሩ የኪነት ቡድኖችን እያቋቋመ የጦር ሠራዊቱን የውጊያ ሞራል ለመገንባት ጥሯል፡፡ አልፎ ተርፎ ነፍሱን ይማረውና ታዋቂውን ድምጻዊ ጥላሁን ገሰሰን ከታዋቂ የሙዚቃ ባንድ ጋር ወደ ሰሜን አዝምቶ ነበር፡፡ ጥሌ በመረዋ ድምፁ፡-

"ግፋ በለው፣

ገስግስ በለው

ግደል ተጋደል በርታ ወገኔ

በጥንቱ ታሪክ በባትህ ወኔ"

እያለ ሲዘፍን ሠራዊቱ ከፍተኛ ድልን ተቀዳጅቷል፡፡ አቶ መለስ የስልጣን ኮርቻው ላይ ከወጡ በኋላም በህዝብ ዘንድ የሚወደዱ ድምፃውያን የዘፈን ግጥሞቻቸው የሰነቁትን ጭብጥ በብርቱ ይፈትሹ ነበር፡፡ ባንድ ወቅት ኦነግ የሽግግር መንግስቱን ጥሎ ከአገር ከወጣና የትጥቅ ትግል ካወጀ በኋላ ኦሮሚያ ክልል ላይ የነበረው እንቅስቃሴ ያሰጋቸው አቶ መለስ የኦህዴድ ከፍተኛና መካከለኛ ካድሬዎችን ሰብስበው ወርፈዋቸዋል፡፡ "ከሺህ የኦህዴድ ካድሬ የፀጋዬ ደንዳና አንድ ሙዚቃ አገር ያናውጣል፡፡" ሲሉ የካድሬዎችን ብቃት ተችተዋል፡፡ በዘመናችን ስማቸው በፍጥነት ገንኖ ከወጡ ድምጻውያን መሀከል ወጣቱ ሙዚቀኛ ቴዎድሮስ ካሳሁን "ቴዲ አፍሮ" ተወዳዳሪ አይገኝለትም፡፡ በተለይም ወጣቱ

ወደ ገፅ 8 ይዞራል....

# የተሳከረው የኢኮኖሚ ፖሊሲና ውጤቶቹ



ነብዩ ኃይሉ

የገንዘብ አቅርቦት (money supply) ወደ አንድ የንግድ ስራ ወይም ወደ ገንዘብ ተቋማት የሚገባ ወይም የሚወጣ የገንዘብና በአንድ ኢኮኖሚ ውስጥ በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኘውን አጠቃላይ ገንዘብ ይመለከታል፡፡ የገንዘብ ዝውውርም ጤናማ ፍሰት የሚኖረው መንግስት ውጤታማ የኢኮኖሚ ፖሊሲ መቅረፅ ሲችል መሆኑን የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች ያስረዳሉ፡፡ መንግስት ከገንዘብ ጋር በተዛመደ የሚከተላቸው የፊስካል (fiscal policy) እና የሞኒተሪ ፖሊዎች (monetary policy) የተሳከሩ የሚሆኑበት ጊዜ ግን ኢኮኖሚው ታማሚ ይሆናል፡፡ ይህ አይነቱ ችግር በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ውስጥ በጉልህ መታየት ከጀመረ ዋል አደር ቢልም፣ አሁን አሁን ግን በንግዱ ማህበረሰብና በግል ንግድ ባንኮች ላይ የከፋ ጉዳት በመድረስ ላይ ይገኛል፡፡

## የተራበ ነጋዴ

የመንግስት የተሳከረ የኢኮኖሚ ፖሊሲ የተራበ ነጋዴ እያበራከተ ይመስላል፡፡ ቁጥራቸው ጥቂት ያልሆኑ ነጋዴዎች በስራቸው ላይ የደረሰውንም ሆነ በዙሪያቸው ባሉ ሌሎች ነጋዴዎች ላይ ደረሰ የሚሏቸውን የገንዘብ እጥረቶች አስመልክተው እንደሚናገሩት፣ በዚህ ወቅት የንግድ ስራ ፈታኝ እንደሆነባቸው ነው፡፡ ከጓደኞቹ ጋር በመሆን በአስመጪና ላኪነት የንግድ ስራ ከተሰማራ አምስት አመት እንዳስቆጠረ የሚናገረው ታሪኩ ጠና፣ በገንዘብ እጥረቱ ብዙ እንደተቸገረ ይናገራል፡፡ ነጋዴው እንደሚለው ካለፈው አንድ አመት ጀምሮ ከሩቅ ምስራቅ ሀገራት የተለያዩ አልባሳትን በማስመጣት ስራ ላይ ባተኮረባቸው ጊዜያት በተደጋጋሚ የገንዘብ እጥረት አጋጥሞታል፡፡ «ያለኝን ገንዘብ አሟጥጬ፣ ከጓደኛም ከቤተሰብም ብዬ፣ ከታይላንድና ከቻይና የጫንኳቸውን ልብሶች ለማስገባት በአራጣ ለመበደር ተገድጃለሁ፡፡» የሚለው ታሪኩ አራጣ ለመበደር ከመወሰኑ በፊት የተለያዩ ባንኮችን ደጅ እንደጠና ያስታውሳል፡፡ በመጨረሻም በጓደኞቹ ምክር በ30 በመቶ የወለድ ክፍያ የሶስት ወር ቼክ በመስጠት ከአበዳሪው የሚያስፈልገውን ገንዘብ ወስዶ እቃዎቹን ለመርካቶ ገበያ አደረሰ፡፡

ይህን የመሳሰሉ ብድሮችን ለነጋዴዎች የሚያቀርቡ ባለአራጣዎች ባንኮች ለመሸፈን ያልቻሏቸውን የአጭር ጊዜ ብድሮች በማቅረብ ከ20 እስከ 30 በመቶ የሚደርስ ህገወጥ ጥቅም ያገኛሉ፡፡ ታሪኩ የድካሙን ያክል ሳይጠቀም ያስመጣቸውን አልባሳት ማስረከቡን በመጥቀስ ቢያማርርም፣ ይህ አይነቱ እድል መገኘቱም ትልቅ ነገር እንደሆነ ያምናል፡፡ በዚህ መንገድ የገንዘብ እጦታቸውን ለማቃለል የሚገደዱት እንደ ታሪኩ ያሉት ነጋዴዎች ለአራጣ ነጋዴዎች የሚከፍሉትን ከፍተኛ መጠን ያለው ወለድ ብቻቸውን ይሸከሙታል ብሎ ማሰብ ቂልነት ነው፡፡ ሸማቹም ተጨማሪ ወጪ እንዲያወጣ መገደዱ የማይቀር ነውና፡፡

የገንዘብ ድርቁ ያልነካካቸው ነጋዴዎች እንዳሉ የሚናገሩም አሉ፡፡ እነዚህ ወገኖች እንደሚሉት የተወሰኑ ነጋዴዎች ያለምንም ችግር የባንክ ብድሮችን እያገኙ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ በነጋዴዎች መካከል ኢፍትሀዊ ፉክክር መፍጠሩን የሚያምኑት የኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የኮሙኒኬሽንና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምሪያ ስራአስኪያጅ አቶ አዲሱ ተክሌ «ጉዳዩ ጠ/ሚ/ሩ ባሉበት ተነስቶ ውይይት ተደርጎበታል» ይላሉ፡፡ አቶ አዲሱ ይህን ያልተገባ ጥቅም የሚያገኙት በጣት የሚቆጠሩት ባለሀብቶች በመንግስት ይሁንታ አሊያም ከባለስልጣናቱ ጋር ተሞዳሙደው ሊሆን እንደሚችል ይገምታሉ፡፡ እኩል ዕድልና ተጠቃሚነት ባልሰፈነበት ሁኔታ እኩል መፎካከር የማይችሉት ነጋዴዎች አማራጫቸው ከሁለት አይዘልም፡፡ አንድም የመንግስትን ጫማ እየሳሙ ሲያስፈልግም ከባለስልጣናቱ ጋር በሙስና መጠላለፍ፤ ሁለትም የኢፍትሀዊው ፉክክር ሰለባ መሆን፡፡

እነዚህንና መሰል የንግዱ ማህበረሰብ ችግሮች መፍትሄ በማፈላለግ ረገድ የንግድ ምክር ቤቶች ብዙ ቢጠበቅባቸውም ተጨባጭ መፍትሄ ሲያሰጡ አይስተዋልም፡፡ ምክር ቤቶቹ የንግዱን ማህበረሰብ አይወክሉም የሚሉ ወቀሳዎችም ይሰነዘሩባቸዋል፡፡ ከጥቂት ወራት በፊት በአዲስ አበባ ንግድ ምክር ቤት ቴሌ ማርኬተሮች ውትወታ ያለ ምዝገባ ክፍያ አባል እንደሆኑ የሚናገሩት አስተያየት ሰጪ የገንዘብ እጦቱን በተመለከተ ምክር ቤቶቹ ያደረጉት እንደሌለ መታዘባቸውን ይናገራሉ፡፡ «ምክር ቤቶቹ የንግዱን ማህበረሰብ ጥቅሞች ለማስጠበቅ በሌሎች ሀገራት የሚታየውን አይነት ጫና የማሳደር ኃይል የላቸውም፡፡» የሚሉት እኚሁ የምክር ቤቱ አባል «የምክር ቤቶቹ ኃላፊዎች የሚይዟቸው የተልፈሰፈሱ አቋሞች ለራሳቸው ብድር እስካገኙና ስልጣናቸውን ተጠቅመው የተወሰነ ጥቅማ ጥቅሞችን እስካገኙ ድረስ የሌላው ነጋዴ የገንዘብ እጥረት ደንታ እንደማይሰጣቸው ያስረዳል፡፡» በማለት ይተቻሉ፡፡ የአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ምክትል ዋና ጸሀፊ የሆኑት አቶ ተፈሪ አስፋው በዚህ ሀሳብ አይስማሙም፡፡ በአቶ ተፈሪ እምነት የገንዘብ እጥረት ቢኖርም ዋንኛው የንግዱ ማህበረሰብ ችግር የዋጋ ግሸበት የሸማቾችን የመግዛት አቅምን ማዳከሙ ነው፡፡ «የንግዱ ማህበረሰብ አሉብኝ የሚላቸውን ችግሮች ሁሉ እየያዝን ዝም ብለን መጮኽ አንፈልግም፤ጥናት ማድረግ አለብን» የሚሉት ምክትል ዋና ጸሀፊው የገንዘብ እጥረቱን አስመልክቶ ከንግዱ ማህበረሰብ ወደ ምክር ቤቱ የመጡ ቅሬታዎች እንደሌሉ ይናገራሉ፡፡ የችግሮችን ምንጭ ለመለየት ጥናት ማድረግ አስፈላጊነት ሊሆን ይችላል፡፡ ሆኖም አፍጦና አግጥጦ የንግዱን ማህበረሰብ አደጋ ላይ እየጣለ ያለን ችግር «በጥናት ግኝት» እስካልተረጋገጠ «ችግሩ የለም» ማለት የንግዱን ማህበረሰብ እወክላለሁ ከሚል ተቋም የሚጠበቅ አይደለም፡፡

ለምክርቤቱ ቅርበት ያላቸው አንዳንድ ምንጮች እንደሚገልፁት ምክር ቤቶቹ በከፍተኛ ደረጃ የመንግስት ጣልቃ ገብነት ስላለባቸው የቀድሞ ጥንካሬያቸው ከድቷቸዋል፡፡ በመሆኑም መንግስትን ሞግተው የንግዱን ማህበረሰብ ጥቅም ከማስጠበቅ ይልቅ የይምሰል ጩኸት ማሰማትን መርጠዋል፡፡ «የግሉ ዘርፍ ደካማ በመሆኑ፣ ይህም ቼምበር ደካማ ነው» የሚሉት የኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የኮሙኒኬሽንና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምሪያ ስራአስኪያጅ አቶ አዲሱ ተክሌ የመንግስት ጣልቃ ገብነት እንደሌለ ያስተባብላሉ፡፡ መንግስት ተጠንተው በሚሰጡት ችግሮችና መፍትሄዎች ላይ አፋጣኝ መፍትሄ አይሰጥም የሚለውን ትችት የሚጋሩት አቶ አዲሱ «እኛ የሙያ ማህበር ስላልሆንን በመንግስትና በነጋዴው መሀከል እንደ ድልድይ ከማገልገል ባለፈ ችግሮችን ለመፍታት ሰላማዊ ሰልፍ ልንጠራ አንችልም፡፡» በማለት የምክር ቤቱን ጥርስ አልባነት የሚያሳብቅ አስተያየት ይሰጣሉ፡፡

መንግስት ለራሱ ጥቅም ከኢኮኖሚው ላይ የሚመጠው ገንዘብ የንግዱ ማህበረሰብ ላይ ካደረሰው ድርቅ ባለፈም የግል ባንኮች ላይ ከፍተኛ ጉዳት በማድረስ ላይ ይገኛል፡፡

## መንግስት የግል ባንኮችን እየዘረፈ ይሆን?

የአክሰስ ካፒታል የጥናት ቡድን ታህሳስ 20 (Ethiopia: Macroeconomic Handbook 20011/12) ይፋ ባደረገው አመታዊ የጥናት ሪፖርት እንደጠቆመው መንግስት እየተከተለ ያለው የኢኮኖሚ ፖሊሲ የተሳሳተ እንደሆነ ጠቁሞ ነበር፡፡ የጥናቱ ግኝት እንደሚያመላክተው በመንግስት የተሳከረ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ጉዳት እየደረሰባቸው ከሚገኙ የግል ዘርፎች ውስጥ ባንኮች በዋናነት ተካተዋል፡፡ የግል ባንኮች ላጋጠማቸው የገንዘብ አቅርቦት ችግር ለመዳሰስ ስንነሳ በተለይ መጋቢት 2003ን እናስታውሳለን፡፡ ወሬው ሁሉ « አባይ...አባይ... ግድብ...» በነበረበት ባለፈው አመት መጋቢት በብሔራዊ ባነክ የግል ባንኮችን የሚያሽመደምድ አንድ መመሪያ ወጥቶ ነበር፡፡ መጋቢት 29/2003 የወጣው ይህ መመሪያ ባልተጠበቀ ሁኔታ ወደኋላ ስምንት ወር ተስፈንጥሮ ተግባራዊ እንዲሆን መወሰኑ እንዲሁም በመንግስት ስር በሚተዳደሩት ባንኮች ላይ ተፈፃሚ አለመሆኑ፣ የግል ባንኮች የመመሪያውን አላማ በጥርጣሬ እንዲመለከቱት ያደረገ ነበር፡፡ ጥቂት ቆይቶም የባንኮቹ ድሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢዎች አቶ መለስን ለመማፀን መሞከራቸው ተሰምቶ ነበር፡፡

መመሪያው እያንዳንዱ የግል ባንክ ከሚያበድረው ገንዘብ 27% የሚሆነውን ለቦንድ ግዢ የማዋል ግዴታ ጥሎበት ነበር፡፡ መንግስት ከግል ባንኮች የሚሰበስበው ገንዘብ መብዛት ባንኮቹ ለደንበኞቻቸው ብድር እንዳይሰጡ የሚያደርግ ውጤት እንዳለው በእስካሁኑ ሂደት ለማየት ተችሏል፡፡ በተለይም ባንኮችን በተሻለ መጠን ተጠቃሚ እንደሚያደርግ የሚታመነውን የአጭር ጊዜ ብድር ለመስጠት ባለመቻላቸው በባንኮቹም ሆነ እንደ አስመጪ እና አከፋፋይነት በመሳሰሉ ዘርፎች ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ነጋዴዎችን እጅግ የሚጎዳ ነው፡፡ ባንኮቹ የመካከለኛ እና የረጅም ጊዜ ብድሮችን እንዳይሰጡ ደግሞ የብድሮቹ ባህሪ ከሚፈልገውን ያክል ከፍተኛ ከጥቂቶቹ በቀር ተቀማጭ የላቸውም፡፡ በመሆኑም አንዳንድ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ደንበኛ ለማበራከት ቅርንጫፍ ማብዛት ላይ የማተኮር እርምጃ እየወሰዱ ይገኛሉ፡፡

ብሔራዊ ባንክ ያወጣው መመሪያ የግል ባንኮች አሁን በደረሱበት ደረጃ እንዲዳከሙ ከማድረግ ባለፈ በሂደት ከገበያ ሊያስወጣቸው እንደሚችል የባንክ ባለሙያ የሆኑት አቶ ሙሼ ሰሙ ያስጠነቅቃሉ፡፡ ኢህአዴግ ደርግ የግለሰቦችን ሀብትና ንብረት ከቀማበት መንገድ በከፋ ደረጃ የግል ባንኮችን እየዘረፈ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ «ባንኮቹ 5% ከፍለው የሰበሰቡትን በ3% ለመንግስት እንዲያስረክቡ በማድረግ በአደባባይ እየዘረፈ ነው፡፡» የሚሉት አቶ ሙሼ በዚህና ሌሎች ጫናዎች ምክንያት አዳዲስ ጀማሪ የሆኑት ባንኮችብዙ ተቀማጭ ስለማይኖራቸው በቀላሉ ወደ ኪሳራ ሊገቡ ይችላሉ፡፡ ነባሮቹ ባንኮችም ቢሆኑ ሁኔታው በዚህ ከቀጠለ በጥቂት ጊዜ ውስጥ ፈታኝ ሁኔታ ውስጥ ሊገቡ እንደሚችሉ ያስጠነቅቃሉ፡፡

የመመሪያው መንፈስ በወቅቱ ከፍተኛ ደረጃ ደርሶ የነበረውን የዋጋ ግሽበት ለመከላከል እንደተ ወሰደ የቁጥጥር ስልት አድርገው ወስደውት እንደ ነበር የሚናገሩት ስማቸው እንዲገለፅ ያልፈለጉ የአንድ የግል ባንክ የቅርንጫፍ ስራአስኪያጅ «መመሪያው የግል ባንኮችን ከማዳከም ባለፈ በግሸበቱ ላይ ያመጣው ውጤት አልታየኝም፡፡»ይላሉ፡፡ ቀደም ሲል በተጠቀሰው የአክሰስ ካፒታል የጥናት ቡድን ሪፖርት ላይ እንደተጠቀሰው ዋንኛው የዋጋ ግሸበት ምንጭ የመንግስት የኢኮኖሚ ፖሊሲ ህፀፅ ውጤት ነው፡፡

መንግስት የግሸበቱ ምንጭ እየተመዘገበ ያለው የኢኮኖሚ እድገት እንደሆነ ሲገልፅ ቢሰነብትም፣ ይህ ሀሳብ ስህተት መሆኑን ለማስረዳት ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት እያሳዩ የሚገኙ ሀገራትን የዋጋ ግሸበት ደረጃ መመልከት በቂ ነው፡፡ *የአይ.ኤም.ኤፍIMF (www.imf.org) የመስከረም ወር ዳታ እንደሚያመላክተው በፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ከምስራቅ አፍሪካ በአንደኝነት የምትመራው ኤርትራ ያስመዘገበችው የዋጋ ግሸበት 12.3% ሲሆን ከኤርትራ ያነሰ የኢኮኖሚ እድገት እያስመዘገበች ያለችው ኢትዮጵያ ግን 38.1 የዋጋ ግሸበት በማስመዝገብ ከአፍሪካ አንደኛ ከአለም ደግሞ ቤላሩስን ተከትላ ሁለተኛ ደረጃን ይዛለች፡፡ ይህ የሚያረጋግጠው የግሸበቱ ምንጭ ተመዘገበ ሚባለው የኢኮኖሚ (የቁጥር) እድገት እንዳልሆነ ነው፡፡* መንግስት ኢኮኖሚው ውስጥ ያለውን ገንዘብ እየመጠጠ ያለው የዋጋ ግሸበቱን ለማስወገድ እንዳልሆነም ለማረጋገጥ ብዙ ሳይኬድ እጅግ እየበዛ የመጣውን የመንግስት የገንዘብ ወጪ መመልከት ይቻላል፡፡ በመንግስት የትራንስፎረሜሽን እቅድ ሰፍሮ የሚገኘው የመንግስት የአመት በጀት ከ85 ቢሊዮን ብር በላይ ነው፡፡ መንግስት በዚህ የተሳከረ የኢኮኖሚ ፖሊሲው የንግዱን ህብረተሰብና የግል ባንኮችን በማሽመድመድ የሚመጠውን ገንዘብ በራሱ መዋቅር በመርጨት ላይ ተጠምዷል፡፡

# ምን መደረግ አለበት (ሁለት)

ዶ/ር ፈቃዱ በቀለ

በቁጥር 40 እትማችን «በርግጥስ የኢህአዴግ አገዛዝ ልማታዊ መንግስት ነዉ ወይ?» የሚል የዶ/ር ፈቀዱ በቀለን ፅሁፍ የመጀመሪያ ክፍል ማዉጣታችን ይታወሳል፡፡ ለዛሬዉ የተጀመረዉን «ምን መደረግ አለበት» የመጨረሻ ክፍል ሁለት እነሆ፡-

የተቀላጠፈና ሰውን የሚያከብር አሰራር ካለ ለፈጣን ኢኮኖሚ ዕድገት ያመቻል። ብዙ ጥናቶች እንደሚያረጋግጡትና፣ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴም በሰዎች የሚካሄድና በጊዜና በአካባቢ የሚወሰን እንደመሆኑ መጠን የኢንስቲቱሽን ለውጥና፣ ኢንስቲቱሽኖች በልዩ ልዩ የስራ መስክ መዳበር ያለባቸው እንደሆኑ የበለጸጉ አገሮች ታሪክ ያስተምረናል። ከዚህ ጋር ተያይዘው በመንግስት የሚደገፉ የምርምርና የጥናት እንዲሁም የቴክኖሎጂ አፍላቂ ኢንስቲቱሽኖች መቋቋም አለባቸው። ይህ ሁኔታ የግዴታ ያለውን የትምህርት ተቅዋም በአዲስ መልክ ማደራጀት እንዳለብን ይጠቁመናል። በአሁኑ ወቅት ካለበቂ ጥናትና የሰውና የማቴሪያል ኃይል፣ እንዲሁም ካለበቂ ላቦራቶሪና ቤተ-መጻህፍት የተቋቋሙት ኮሌጆች ወይም ዩኒቨርሲቲዎች ወደ ዕደ-ጥበብ ማሰልጠኛነት መቀየር አለባቸው። ከዚህም ስንነሳ ስፊና አጠቃላይ የሆኑ የዕደ-ጥበብ ሙያ መስኮችንና የኢንጂነሪንግ ኮሌጆችን ማስፋፋቱና ማዳበሩ ለዕድገት አመቺ ነው። የጊዜውም ጥያቄ በዕውቀት ላይ የተመሰረተ ኢኮኖሚ መገንባት ነው። ከዚህ ውጭ ከውጭ የሚመጣን ውድድር መቋቋም አይቻልም። እንዲያውም ለዕድገት ዋናው ቁልፉ የጥሬ-ሀብት ተትረፍርፎ መገኘት ሳይሆን የዕውነተኛ ዕውቀት ባለቤት መሆን ነው። በየአገሩ እንድምናየው የጥሬ-ሀብት አገር አምራቾች በዕድገታቸው የተዛነፉና በሙስና ላይ የተመሰረተ አገዛዝ ነው ያላቸው። ይህ ዐይነቱ ሁኔታ ግን የተፈጥሮ ህግ አይደለም። ከባህል ተሃድሶ አለመኖር ጋርና ከህብረተሰበአዊ ኃላፊነት አለመሰማት ጋር የተያያዘ የአገዛዝ ስልት ሲሆን፣ በተጨማሪም የተሳሳተ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ከመከተል ጋር የሚያያዝ ነው።

ለአንድ አገር ዕድገት መንግስት የሚከተለው ፖሊሲ ብቻ ሳይሆን ወሳኙ፣ በአገር ውስጥ ከብዙ ክርክር በኋላ የሚዳብር የኢኮኖሚ ቲዎሪና ፖሊሲም መኖር ወሳኝ ሚናን ይጫወታል። አንድ አገዛዝም በእርግጥም ለአገሩ ዕድገት የሚቆረቆርና በታታሪነት ሊሰራ የሚችለው በጥሩ ቲዎሪና ፖሊሲ የሚመራ እንደሆነ ብቻ ነው። ይህ ደግሞ በየጊዜው መመርመር አለበት። ስለዚህም አንድ አገዛዝ የሚመራበት የኢኮኖሚ ፖሊሲ የአገሩን ጥቅም የሚያስጠብቅ መሆን አለበት። ለውጭ ኃይሎች መፈናፈኛ የማይሰጥ መሆን አለበት። ለዚህ ደግሞ ኢትዮጵያዊነትን ከደሙ ጋር ያዋሃደ ኢትዮጵያዊ ኃይል ያስፈልጋል። ይህ ኃይል ዕውቀት ያለው፣ በአዋቂዎች የተከበበና ምክር የሚሰማ መሆን አለበት። ከዚህ ጋር ተያይዞ የተለያየ አመለካከት ያላቸው ግለሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች ለአንድ አላማ በአንድነት መነሳት አለባቸው። በሳይንስ የማይረጋገጥን ርዕዮተ-ዓለም ሽፋን የሚያደርግና ከአገር ጥቅም ይልቅ ለራሱና ለውጭ ኃይሎች ጥቅም የሚታገል የፖለቲካ ድርጅት ለዕድገትና ለህብረተሰብአዊ መተሳሰር እንቅፋት እንደሚሆን ከመጀመሪያውኑ መታወቅ አለበት። ስለሆነም ለአገር እታገላለሁ ብሎ የሚነሳ ማንኛውም ኃይል ከውጭ ኃይሎች ጋር በጥቅም የተሳሰረ መሆን የለበትም። በሌላ አነጋገር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከውጭ ኃይሎች ጋር የውስጥ ለውስጥ ግኑኝነት የፈጠረና በነሱም አማካይነት ስልጣን ላይ እወጣለሁ የሚል የመጨረሻ መጨረሻ ተልዕኮው ጥፋት ይሆናል። ከብዙ

ወደ ገፅ 12 ይዞራል....

# ኢህአዴግ በአንድ ቀን ከ104 ሰዓት በላይ ፕሮፓጋንዳ እየሰራ ለምን ምንም ፕሮፓጋንዳ በማይሰሩት ተበለጠ?

ለዛሬ ፅሁፌ መነሻ የሆነኝ በኦሮሞያ ክልል የፊንፊኔ ዙሪያ ሰራተኞችን በሊዝ አዋጁ ዙሪያ የመንግስት ተወካይ የሆኑ የዚሁ አካባቢ ካድሬዎች ያነጋግሯቸዋል:: መንግስት አንዳንድ ኪራይ ሰብሳቢዎችን ለመቆጣጠር ባደረገዉ ትግል የተለያየ ስልት ሲቀይስ እንደቆየ በመግለጽ አሁንም የግለሰቦችን ኪስ ከማዳበር ለሀገር ልማት ማዋል ይቻል ዘንድ መንግስት ሁሉንም መሬት በሊዝ እንዲተዳደሩ ማድረጉ ተገቢና አማራጭ የሌለዉ ተግባር መሆኑን አንዱ ካድሬ ያስረዳል:: ቀጠል በማድረግም መንግስታችን ለህዝቡ ካለዉ ፍቅርና አሳቢነት በመነሳት የቀድሞ ይዞታዎች እስኪሸጡ ድረስ ወደ ሊዝ አለመግባታቸዉ በራሱ የመንግስታችንን አርቆ አሳቢነትን ያሳያል ይላል:: አብረዉት የነበሩትም ካድሬዎች ከመጀመሪያዉ ካድሬ ያልተለየ ዲስኩር ያቀርባሉ:: ለበርካታ ጊዜ ካድሬዎቹ እየተፈራረቁ ተናግረዉ ሲጨርሱ ሀሳብ ከተሰብሳቢዉ ቢጠይቁም ምንም መልስ ያጣሉ:: የዕለቱ መድረክ አስተባባሪዎችም ተሰብሳቢዉን የድጋፍ ሀሳብ ብለዉ ቢጠይቁም ተሰብሳቢዉ ዝም ይላል:: ድጋፍ ያላችሁ የድጋፍ ሀሳባችሁን ስጡ ይባላል:: ተቃዉሞ ቢኖራችሁም ዴሞክራሲ ነዉና ያንንም ማቅረብ ትላላችሁ ይላሉ:: ተሰብሳቢዉም ዝም ጭጭ ይላል:: በዚህ የተናደደዉ ካድሬ ተሰብሳቢዎቹ ስብሰባ እንዲመጡ የተደረገዉ አባላት እና የአባልነት ካርድ ያላቸዉ ብቻ ስለነበሩ የማይናገሩ አባላት ስለማንፈልግ ካርዳችንን መleሱ ይላቸዋል::

ከኢህአዴግ ስህተቶች አንዱና ዋነኛዉ፤ ጥፋቱን የሚነገሩትንና እና ትክክል አይደለህም የሚሉትን እንደ ተቃዋሚ መቁጠሩ ሲሆን፤ በተጨማሪም እንዲሁ ኢህአዴግ የሚሰራዉን ስራ የሚቃወሙት ተቃዋሚዎች እንጂ አባላቱ ስራዉን ሁሉ እንደሚደግፉለት መቁጠሩ ነዉ::

በዚህ ጊዜ አንድ ሰዉ ከመካከላቸዉ ይነሱና እንዲናገሩ ሲፈቀድላቸዉ መናገር ይጀምራሉ:: ‹‹በአንድ ወቅት መንግስቱ ኃ/ማርያም ሊወድቅ ሲል ከተናገረዉ አንድ ቃል ልናገር:: መንግስቱ ኃ/ማርያም ጠመንጃ ገዝተን ሰጠናችሁ፣ ጥይት ገዝተን ሰጠናችሁ፤ ወኔ ደግሞ አንገዛላችሁ? የት እንደሚሸጥ አንወቅና ገዝተን አንስጥ አለ›› አሉ:: ቀጠል አደረጉና ‹‹አሁንም እናንተ የሰጣችሁን ካርድ ለመናገር እንኳ ወኔ ስላልሰጠን ብትወስዱትም ባትወስዱትም ምንም ችግር የለብንም ሲሉ ሁሉም ሰዉ በአንድ ላይ ይስቃል::

እኔ ከዚህ ስብሰባ ንግግር እና ኢህአዴግ ከአባላቱ ሳይቀር አሁን እየተሰጠዉ ያለዉ ምላሽ ለመገምገም እሞክራለሁ::

1) ሰፊዉ የፕሮፓጋንዳ ሽፋን በቀን የሚወስደዉ ጊዜ

የኢህአዴግ መንግስት በሚዲያዎቹ በቀን ቢያንስ ከ104 ሰዓት በላይ ይጠቀማል:: ካድሬዎቹ የፕሮፓጋንዳዉ ስራ ያለዕረፍት እየሰሩ እንደሆነ ይታወቀል:: ሆኖም ኢህአዴግ ከአባላቱ ሳይቀር እምነት ማጣቱ ከምን የመጣ ነዉ? ለምሳሌ ፕሮፓጋንዳዉን በሚዲያ እንዴት አንድ መቶ አራት ሰዓት በላይ እንደተጠቀመ ብንመለከት:-

ሀ) የኢትዮጵያ ሬዲዮ በቀን 18፡00 ሰዓት በተለያዩ ቋንቋዎች ከጥዋቱ 12፡ ሰዓት እስከ ሌሊቱ 6፡00 ሰዓት ድረስ ፕሮፓጋንዳ ያስተላልፋል

ለ) ሬዲዮ ፋና በዚሁ ሰዓት በተለያዩ ቋንቋዎች በቀን 18፡00 ሰዓት ከጥዋቱ 12፡ሰዓት እስከ ሌሊቱ 6፡00 ሰዓት ድረስ ፕሮፓጋንዳ ያስተላልፋል

2)ሐ) የፋና ሬዲዮ ከዓለም አቀፍ ስርጭቱ በተጨማሪ በሻሸመኔ፣ በሀረር አካባቢ፣ በደሴ፣ በጂማና አካባቢዋ በጎንደርና አካባቢዋ በተመሳሳይ ሰዓት ቢያንስ እያንዳንዳቸዉ ከስድስት ሰዓት ያላነሰ ይጠቀማሉ:: ይህም ቢያንስ 30፡00 ሰዓት ያህል ይጠቀማል ማለት ነዉ::

መ) በተጨማሪ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በተመሳሳይ ሰዓት 24 ሰዓት በተለያዩ ቋንቋዎች ይጠቀማል::


ሠ) ኢቲቪ 2 እንዲሁ በተመሳሳይ ሰዓት የተለያዩ ፕሮገራሞችን ያስተላልፋል::

ረ) በኤፍ ኤም አዲስ ሬዲዮ በተመሳሳይ ለ24 ሰዓት ይጠቀማል:: እነዚህን ሰዓቶች በአንድ ላይ ብንደምራቸዉ 18+18+30+24+24=104 ሰዓት በቀን ይሆናል ማለት ነዉ::ይህ ስሌት በትክክል ጊዜ ተወስዶ ቢሰላ ያለጥርጥር በቀን ከ300 ሰዓት በላይ ይሆናል::

ይህ ሁሉ ነገር ሲሆን ሚዲያዎች ከጥቂቶቹ በስተቀር አብዛኛዎቹ የኢትዮጵያ ህዝብ ንብረቶች ናቸዉ:: የኢትዮጵያ ህዝብ እኩል ሊጠቀምባቸዉ በተገባ ነበር:: ሆኖም ኢህአዴግ ሁሉንም ያለከልካይ እየተጠቀመባቸዉ ነዉ:: ሆኖም ዉጤት አምጥቶባቸዋል ወይ? ቢባል ምንም ዉጤት አላመጡም::

3)የገባዉንቃል አለመፈጸሙ

ኢህአዴግ በፕሮፓጋንዳዉ ዘርፍ ዉጤት ሊያመጣ ያልቻለዉ በአብዛኛዉ የሚገባዉን ቃል ሊፈጽም ያለመቻሉ ነዉ:: በትንሹ እንኳን የመናገር፣ የመሰባሰብ፣ በነጻነት የመጻፍ፣ በፖለቲካ ፓርቲዎች በህጋዊ መንገድ ተደራጅዉ መንቀሳቀስ እንደሚችሉ ቢገልጽም ከነዚህ መሐል አብዛኛዉ አላደረገም:: የፖለቲካ ፓርቲዎች ህጉን ተከትለዉ ቢቃወሙም በተለያየ መንገድ አባላቱን ከማስፈራራት ጀመሮ፣ ከስራ የሚያባርር መሆኑ ለምሳሌ አንድነት ፓርቲን የኢትትዮጵያ ህዝብ ንብረት በሆነዉ አዲስ



ኢ/ር ዘለቀ ረዲ

ዘመን ጋዜጣ እና በኢቴቪ ለህዝብ ሲከሰዉ ይታያል:: በዚህም አባላቶቹ ሳይቀሩ የተጻፈዉና በመሬት ላይ የሚደረገዉ በመለያየቱ በያዙት ወረቀት ብቻ አባል ሲሆኑ በልባቸዉ ግን ፈጽሞ ከኢህአዴግ ጋር አይደሉም::

4)ኢህአዴግ ሁኔታዎችን ለማሻሻል አለመሞከሩ

ኢህአዴግ በአሁኑ ሰዓት እያደረገ ያለዉ "የበላችዉ እያስገሳት፣ በላይ በላይ ያጎርሳታል" እንደተባለዉ ምሳሌ ህዝቡ በመንግስት ላይ እየተማረረ መሆኑ እየታወቀ የህዝቡን ብሶት ከማዳመጥ ይልቅ ሌላ ህዝቡን የሚያማርር ነገር እየተጨመረ እንደሆነ ይታያል:: ይህ ነገር ደግሞ ማንንም አይጠቅምም:: ምክንያቱም ከህዝብ ጋር መወያየት እየተቻ ለምንም ዉጤት የሌላቸዉን አንዳንድ ነገሮችን መጠቀሙ በመንግስት ፈጽሞ አይጠቅመዉም:: በእርግጥ አንዳንድ ስብሰባ እንዲመሩ ኃላፊነት የተሰጣቸዉ ካድሬዎች ትክክለኛ የህዝቡን ስሜት ለበላይ አካላቸዉ ያቀርባሉ ወይስ? አልሰራችሁም ተብለዉ እንዳይወቀሱ የህዝቡን ተቃራኒ አስተሳሰብ በሪፖርት መልክ ያቀርባሉ ለሚለዉ መልሱን እነርሱ ራሳቸዉ እንጂ ማንም አይመልሰዉም::

ነገር ግን እየተደረገ ያለዉ ነገር በመንግስት ላይ ጊዜዉ ይራቅም ይቅረብም አይታወቅም እንጂ ቁጣ አይቀሰቀስም ብሎ መገመት ሞኝነት ነዉ:: ለነገሬ መቋጫ እና ኢህአዴግ እያደረገ ካለዉ ነገር በመነሳት በአንድ ወቅት አንድ ወዳጄ ያጫወተኝን ጉዳይ ላቅርብ፤ ነገሩ እንዲህ ነዉ፤ አንድ ሰዉ በጣም ብዙ ሙዝ ይበላል:: የበላዉ ሙዝ በጣም ከመብዛቱ የተነሳ ቁንጣን ያንፈራፍረዋል:: ታዲያ አንድ ወዳጁ ‹‹ምን ሆነሃል?›› ቢለዉ ‹‹ብዙ ሙዝ በልቼ ቁንጣን እያጣደፈኝ ነዉ›› ይለዋል:: ‹‹ታዲያ እኮ አንድ ጣህትን በጉሮሮህ ብትከተዉ የሚያስጨንቅህ ነገር ይወጣልሃል›› ቢለዉ ‹‹አንተ ሞኝ ነህ፤ አንድ ጣት የሚያስገባ ቦታ ቢኖረኝማ ሌላ አንድ ሙዝ እጨምርበት ነበር አለ›› ይባላል:: አሁንም በህዝቡ ላይ ያለዉን መከራ ቢቀንስለት ይሻላል ተብሎ ለሚቀርብ ጥያቄ ሌላ መከራ በኖረና በጨመርነዉ የሚል ሃሳብ ያለ እስኪ መስል ድረስ እየተሄደ ነዉ::

# የአቶ መለስ ሦስት ...

ከ ገፅ 6 የዞረ....

"... አዲስ መንግስት እንጂ ለውጥ መቼ መጣ" የተሰኘው የሙዚቃ ግጥም ለአቶ መለስ ግዙፍ መርዶ ሆነ:: ኢህአዴግ ለአመታት የኳተነበትን የልማትና የዕድገት ፕሮፓጋንዳ የቴዲ አንድ ዘፈን መሬት ላይ ፈጠፈጠው:: አርቲስቱም በአቶ መለስ ጥርስ ውስጥ ገባ:: ቴዎድሮስ ካሳሁን በሕዝብ ዘንድ ያለውን ዝና ለማደብዘዝ ለኢትዮጵያ ሚሊኒየም ቴዎድሮስ ታደሰ በክብር ታጅቦ ከአሜሪካ አዲስ አበባ ገባ:: ሚዲያዎች ሁሉ ያን ሰሞን ቴዎድሮስ ታደሰን አነገሱ:: የቴዲ አፍሮ ሙዚቃዎች በኢቴቪ እና በሬዲዮ እንዳይተላለፍ መመሪያ የተላላፈ ይመስል ዛሬም ቢሆን በተከታታይ አይቀርቡም:: አቶ መለስ ወደረኞቻቸውን የሚበቀሉት ቀናት ቆጥረውና አድብተው በመሆኑ አርቲስቱ በመኪናው ሰው ገጭቶ ገድሏል በሚል ሰበብ ተከሶ ዘብጥያ ወረደ:: አቶ መለስም የፍርዱ ሂደት በሚታይበት ሰሞን "የአዲስ አበባ ህዝብ ብዙ መሠረታዊ ችግሮች እያሉበት አንድ ዘፋኝ ለምን ታሰረ ብሎ ይጮህል" ሲሉ ተናገሩ::

የድምፃዊው መታሰር ግን እጅግ የላቀ እውቅናን አስገኘለት እንጂ አልጐዳውም:: በሚሊዮን በሚቆጠር ኢትዮጵያዊ ልብ ውስጥ ዛሬም እንደገነነ አለ:: ለፋሲካ በዓል በለቀቀው አልበሙ ምድሪቱ እየተናወጠች ስናይ ህዝቡ ለእሱ ያለውን ፍቅር እናስተውላለን:: ሁሉም የዘፈኖቹን የግጥም ስንኞች እንደ እውቀት ደረጃው እየመረመረ ከኢህአዴግ ፖለቲካ ጋር ሲያያይዘውና ከኢትዮጵያዊነት ጋር ሲያቆራኘው ይደመጣል:: እርግጥ የቴዲ አፍሮ አልበም በተለቀቀ ቁጥር በኢህአዴግ ቤት የፍርሃት መርዶ በኢትዮጵያውያን ዘንድ የምስራች እንደሚሆን ጥርጥር የለውም:: ካንድ የመድፍ ጥይት የአንድ ከራር ቅኝትና የከበሮ ድለቃ ለህወሓቶች የላቀ ዋጋ እንዳላቸው ጠንቅቀው ያውቃሉ:: ለዚህም ከነሱ ርዕዮት ፈንገጥ ባሉ አርቲስቶች ላይ የማይቀኙት::

ፍርሃት ሁለት:- መያዶች NGO (መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች)

ለህወሓት /ኢህአዴግ ድል የመያዶች አስተዋፅኦ የላቀ ነበር:: ደርግ ይከተለው የነበረው የሶሻሊዝም ርዕዮት ዓለም (Ideology) ከምዕራቡ ዓለም ጋር በብርቱ ያቃቃረው እንደነበር ይታወቃል:: ኮሎኔል መንግስቱ በየአደባባዩ ክንዳቸው እስኪዝል ድረስ የአሜሪካንን ኢምፔሪያሊዝም ማውገዛቸውና የኢትዮጵያ ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ በአሜሪካ መንግስት ዘንድ ተፈላጊ በመሆኑ በወቅቱ ህወሓት በምዕራቡ ዓለም ተቀባይነት ነበረው:: በዚህ መነሻነት በሰብአዊ ድርጅቶች ሰበብ የህወሓት መሪዎች ጠቃሚ መረጃዎችን ያገኙ ነበር:: አልፎ ተርፎ በእርዳታ ሰበብ ኢኮኖሚያዊ ድጋፍም ነበራቸው:: በወቅቱ ህወሓት ድል አድርጎ በተቆጣጠራቸው አካባቢዎች መያዶች ያደረጉት የምግብና የቁሳቁስ እርዳታ በምስጢር ተሸጦ ለጦር መሣሪያ መግዣ እንደዋለ የቢቢሲ ቴሌቪዥን ጣቢያ ባንድ ወቅት እንደ ዘገበውና አቶ መለስን እንዳስቆጣቸው ይታወቃል::

ከዚህ አንጻር በምርጫ 97 ዓ.ም የውጭ እርዳታ ድርጅቶች (መያዶች) የምርጫው ውጤት የተጭበረበረ መሆኑን አሳማኝ መረጃዎችን በመያዝ ለአሜሪካና ለአውሮፓ ህብረት ማቀበላቸው ኢህአዴግን በብርቱ አሸብሮታል:: በምስራቅ ኢትዮጵያ ኦብነግን ለመውጋት በተደረገው መጠነ ሰፊ ዘመቻ በክልሉ ሠላማዊ ህዝብ ላይ የተፈፀሙ ኢ-ሰብአዊ ድርጊቶች ይፋ በማውጣታቸውና የኢህአዴግ መንግስትን የሚያሳጡ በመሆናቸው እንደ ቀይ መስቀል የመሳሰሉ ሰብአዊ ድርጅቶች በአካባቢው እንዳይንቀሳቀሱ እስከ ማገድ ተደርሷል:: አንዳንዶቹም ድርጅታቸውን ዘግተው ከአገር እንዲወጡ ተደርጓል:: በወሰዷቸው ጊዜያዊ እርምጃዎች ያልረኩት አቶ መለስ አሳሪ ህጎችን ለመደንገግ ጊዜ አላበከኑም:: ሀገር በቀል እና የውጭ መያዶችን እንቅስቃሴ የሚያሽመደምድ ህግ በፓርላማ ፀድቆ ተግባር ላይ ዋለ:: ታላላቅ የአለም የሰብአዊ መብት ድርጅቶችና የምዕራቡ ዓለም መንግስታት በብርቱ ቢቃወሙም አቶ መለስ "ወይ ፍንክች የአቦይ ዜናዊ ልጅ" ሲሉ በአቋማቸው ፀኑ:: ዛሬ የእያንዳንዱን መያድ /NGO እንቅስቃሴ ኢህአዴግ በአይነ ቁራኛ ነው የሚከታተለው::

ፍርሃት ሦስት:- ጋዜጠኞችን መፍራት

በየትኛውም ዓለም የሚታተሙ ጋዜጣዎች ያለ ጋዜጠኞች አይታሰቡም:: አንድ ጋዜጠኛ የዘወትር ተግባሩ እውነትን ያለ ማድላት አንጥሮ በማውጣት ለህዝብ ማቅረብ ነው:: በአደጉት አገሮች ለአገር ሕልውና የሚያሰጋ ድርጊት እንኳን ቢሆን ጋዜጠኛው ምስጢሩን ፈልፍሎ ለአደባባይ ያበቃዋል:: ለአብነት ያህል እንኳን ብንጠቅስ አሜሪካ በጓንታናሞ ቤዝ በምታጉራቸው እስረኞች ላይ የምትፈፅመውን ድብቅ ኢ-ሰብአዊ ተግባር ፈልፍለው አውጥተዋል:: አሜሪካ በተለይም በአረቡ አለም ዘንድ ውግዘት ገጥሟታል:: እንደዚሁም በኢራቅ ውስጥ የአሜሪካን ወታደሮች በእስረኞች ላይ ይፈፅሙ የነበረውን አሰቃቂ ተግባር ይፋ አድርገውታል:: ሌላው አስገራሚ ነገር የአሜሪካን 42ኛው ፕሬዚደንት የነበሩት ቢል ክሊንተን ሥልጣን ላይ እያሉ ሞኒካ ከምትባል ሴት ጋር በሚስጥር መማገጣቸውን ለአለም ህዝብ ይፋ ያደረጉት (ፕሬዝዳንቱን ፍርድ ፊት ያስቆሙት ጋዜጠኞች ነበሩ::) ይሄ ታዲያ የሚቻለው አፍሪካ ውስጥ እንዳይመስላችሁ:: አሜሪካ ወይም እንግሊዝ፣ ፈረንሳይ፣ ጣሊያን በመሳሰሉ ዴሞክራሲ በጐለበተባቸው አገራት ነው::

ህወሓት/ኢህአዴግ ባካሄደው የ17 ዓመታት እልህ አስጨራሽ ትግል ውስጥ የጎላ አስተዋፅኦ ካበረከቱ ጋዜጠኞች መሀከል ደራሲና ጋዜጠኛ በአሉ ግርማን የሚወዳደረው

ወደ ገፅ 14 ይዞራል....

# ምልከታ

## "እውነት የራሷም የውሸትም ማስረጃ ነች"


ሰለሞን ስዩም

በህይወት ቆይታ ውስጥ ምጡቅ `እጓለዎችን` ታዘብኩ፡፡ አንዱ እጓለ እኔ እንጂ አብዛኛው አንባቢ የማያውቁልኝ ነው፡፡ የቤተ ክህነቱ ምሁር፣ የእዉነት ተከላካይ፣ የይሉኝታ ገዳይ፡፡ ሁለተኛው ግን ፈላስፋው እጓለ ገብረ ዮሐንስ ናቸው፡፡ በዘመኔ ከሚነሱትና ውዳሴ ከበዛላቸው ሰዎች የማይንሱ ግን የተረሱ ጀግና ይመስሉኛል፡፡ ዶ/ር እጓለ ገብረ ዮሐንስ የአካዳሚያዊ እውቀት ረድፍ አደላዳይ ይመስላሉ፡፡ ባደረጓቸው ንግግሮች የጥንቃቄ አምባ እንደነበሩ ይነገርላቸዋል፡፡ ፕ/ር መስፍን ወ/ማሪያም ቀጥታና /ፊት ለፊት/ ተናጋሪ ቢሆኑም ሀሳባቸው ሁሌም ቀጥተኛ ነው አልልም፡፡ ፕ/ሩ ትኩረታቸው የያዙትን ጉዳይ ያለፍርሃት በመፃፍ ላይ ነው፡፡ ፕ/ሩ በባህሪያቸው ሰንጣቂ ቢሆኑም ቅሉ ተቺ መካሪም ይመስሉኛል፡፡ በአፃፃፋቸው የተለያዩ የስንዴ ዘሮችን ማሳው ላይ ከሚለይ ገበሬ ጋር ይመሳሰላሉ፡፡ አሁን አሁን ወደ አደባባይ የመጡት ዶ/ር ዳኛቸው አሰፋ ደግሞ ወደኛ የዘረውን ሳንቲም ግልባጭ እንዳለው ማሳየት ሥራዬ ያሉ ናቸው፡፡ ዶ/ር ዳኛቸው የስንዴ ዘሮችን ማሳው ላይ ከመለየት ይልቅ የማሳውን ስንዴ በነዶ በነዶ ወደ ማሰር ያዘነብላሉ፡፡

የዛሬ ጽሑፌ መነሻ ዶ/ር እጓለ ናቸው፡፡ ጭብጤ ደግሞ ዶ/ር እጓለ ከግሪካዊዉ የፍልስፍና ሰዉ ፒኖዘ የተዋሱት ነዉ፤ አንድ እውነት የያዘ አካል፣ የያዛት እዉነት የራሷም የውሸትም ማስረጃ ሆና ሳለ ስለምን የያዘውን እውነት ውሸቱን በማጉላት እንድንመዝናት ይፈልጋል የሚል ነው፡፡ ነገር ግን እላለሁ፡- በህይወት አጋጣሚ የዋሸኋችሁ ሰዎች እንደምን ስለ እውነት ሊፅፍ ተነሳ አትበሉኝ፤ በዲያሌቲክስ (dialectics) ህግ ተፈጥሮ በተቃርኖ ህግ የምትመራ ናት፡፡ እውነት የምትለው ውሸት ማለት ሲኖር ነው፤ በነገራችን ላይ ኢህአዴግ የሶሻሊዝም አቀንቃኝ ነበር ቢባልም የዲያሌቲክስ (ተቃርኖ) ህግን ለመስማት ያለ መፍቀዱ ይገርማል፡፡ ለልማትም ላለመልማትም ኢህአዴግ እኔ ከሚለው በተቃራኒ ምንም ሀሳብ መኖር የለበትም ይላል፡፡ ከግንብ ጋር ቴስታ እንደመግጠም እኮ ነው፡፡

ኢህአዴግ ስራዎቹን ሰርቶ ምስክርነቱ ለኛ ቢተው መልካም ነበር፡፡ ነገር ግን ከመስራቱ ‹እውነታ› ይልቅ ከዚህ ቀደም አልተሰራም የሚለው ፕሮፓጋንዳ ሁለንተናውን ይሻማል፡፡ በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ ያለውን ቅሬታም በዚሁ መልኩ መግለፅ ይችል ነበር፡፡ የቀደመው የኢትዮጵያ ታሪክ ባለበት የራሱን አዲስ ታሪክ ቢሰራ ከመታየት አያግደውም፡፡ መነሻዬ የሆኑት ዶ/ር እጓለ ለዚህ አይነቱ አስተሳሰብ "አንድ ሰው ለራሱ የማይመስለውን ነገር ለማፍረስ ብቻ ይሰለፋል፤ ሌላው ደግሞ ማፍረስን ለሌላው ትቶ በገዛ ሀሳቡ መሠረት አዲስ ለመገንባት ብቻ ይሰራል፤ እኔ የሁለተኛውን እመርጣለሁ" በማትም የተሻለውን መጥፎ ይመርጣሉ፡፡

አብዮታዊ ዴሞክራሲ አንድ እውነት ነበር፡፡ መንፈሳዊ ተቋማት የሚሰጡት ትምህርት ደግሞ ሌላ እውነት ነው፡፡ በኢህአዴግ ስሌት ግን አብዮታዊ ዴሞክራሲ እንዲሰርፅ ቤተ ክርስቲያን አሊያም መስጊድ ጭምር ይህነኑ ሀሳብ መስበክ አለባቸው፡፡ ስለዚህ የሀይማኖታዊ ትይማኖት መስፋፋት መገታት አለበት፡፡ ይህንን ያስተዋሉት ዶ/ር ዳኛቸው አሰፋ "አሁንስ ትንፋሽ አጠረን፤ ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ ማምለጫ የነበሩት የእምነት ተቋማትም ዛሬ የዚህ ሀሳብ መነኃሪያ በመሆናቸው ወዴት መሸሽ እንዳለብን ጠፍቶናል" ብለዋል፡፡

ሌላው የኢህአዴግ ፀባይ፣ አመጣሁት የሚለውን እድገት ለማስረዳት ቀዳሚዎቹን ውርደት ማከናነብ የግዴታ አድርጎ መያያዙ ነው፡፡ በመንገድ ዘርፍ የተገኘው እድገት በአፄ ምኒልክ ከነበረው ጋር ካልተወዳደረ አይታመንም፡፡ እንግዲህ ዘመኑ የመጀመሪያዋ መኪና ወደ አገር የገዛችበት ነው፡፡ ለዚያች አንዲት መኪና ስንት ኪሎ ሜትር መንገድ እንደሚያስፈልግ እናንተዉ አስሉ፡፡ ይህ ማለት አንድን ባሮጌ ቤት የሚኖር ሰው ቤትህ የማይረባ ነው እንደማለት ነው፡፡ ነገር ግን ይህም ሳይባል ከጎኑ ሌላ መስራት በቂ ነው፤ አዲሱ ቤት ስለራሱም አዲስነት ስለሌላኛውም አሮጌነት ብቻውን ይነገራል፡፡

22ኛው የአለም ኢኮኖሚ ጉባዔ በአዲስ አበባ ሲደረግ አቶ መለስ ዜናዊ በሀሙሱ ፓናል ውይይት ላይ ‹ቀዳሚ› ነበሩ፡፡ በዚህ ሁኔታቸው አንድ ነገር አስተውያለሁ፤ የረዥም ዘመን ስልጣን በነገሮች ሁሉ ስልቹ ያደርጋል፡፡ የታንዛኒያው ፕሬዝዳንት በመለስ ዜናዊ ላይ ያሳዩት ብልጫም ከዚሁ የመነጨ ሊሆን ይችላል፡፡ በዚያ ውይይት አቶ መለስ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሞራል እያመሀኙ ልመና መጀመራቸውን አስተውለናል፡፡ የግል ባለሀብቱም ካድሬ እንዲሆን ይመኛሉ፡፡ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ህግ መሠረት አንድ ፓትሪያርክ በህይወት እያሉ ሌላ ሊሾሙ አይችሉም፡፡ በኢትዮጵያ የኢህአዴግ አገዛዝም አንድ ጠ/ሚኒስቴር እስካለ ድረስ ሌላ ወደ ስልጣን አይመጣም፡፡ በዚህ አጋጣሚ አንድ ከማላዊ የመጡ `አነስተኛ` አርሶ አደር የሚገርም ንግግር ሲያደርጉ አስተውያለሁ፡፡ ሰውየው "ፖለቲከኞች" መጪውን ምርጫ ያስባሉ፤ የሀገር ተቆርቋሪነት ያላቸው መሪዎች ግን ስለቀጣይ ትውልድ ያስባሉ" ሲሉ ሰምቼ ተደነቅሁ፡፡ ይህን የአገራዊነት ኃሊየት (state theory) በተደጋጋሚ አይተን ኢህአዴግ ለመንግሥት እንጂ ለሀገር ክብርም ፍቅርም የሌለው መሆኑን ከነምሳሌው አስቀምጠን ነበር፡፡ በመሆኑም ምርጫ በመጣ ሰሞን የሚነግሩን የልማት እቅዶች እንዲሁም ጫና አታካች ነው፡፡

ኢህአዴግ ትምህርትን የፈለሰፍኩት እኔ ነኝ ለማለት ይዳዳል፡፡ ተቺዎች በበኩላቸዉ ትምህርት የሞተችዉ ባርሱ ጊዜ ነዉ ይላሉ፡፡ በዘመናችን ያልተማረ ሰው ሰው አይደለም፡፡ ለዚህ ነው የአንድ ሰው መማር ሰብዓዊ መብት ነው የምንለው፡፡ "ሰው ከሙሉ የሰውነት ደረጃ የሚደርሰው በት/ት ነው" ይላሉ ፈላስፋው እጓለ ገብረ ዮሐንስ፡፡ ፕላቶ ደግሞ "ሰው ትክክለኛውን ትምህርት ያገኘ እንደሆነ ለስላሳና (Noble) እግዚአብሔርን የሚመስል ፍጥረት ነው፤ ትምህርት ያላገኘ እንደሆነ ግን በምድር ላይ ካሉት አራዊት ሁሉ የባሰ ነው" ይላል፡፡ አንድ የተማረና ያልተማረ ሰዉ ጉዳያቸዉን እንዲያስረዱ እድል ቢሰጣቸዉ የተለያዩ ደረጃ ይይዛሉ፡፡ ያልተማረ ሰዉ ጉዳዩን በቃል ብቻ ያስረዳል፤ ለዚያዉም እንልተማረ ሰዉ፡፡ እንዳልተማረና እንደተማረ ማስረዳት መካከል ያለዉን ልዩነት ደግሞ ታዉቁታላችሁ፡፡ የተማረ ሰዉ ግን የሰዉነት ብልጫ የሚሰጡት በፅሁፍና በማንበብ የማቅረብ ሀይል አለዉ፡፡ በዚያ ላይ በቃል እንኳ ቢያቀርብ እንደተማረ ሰዉ ነዉ፡፡ ኢህአዴግ "ትምህርትን ፈለሰፍኩ" ማለት ነው የሚቀረው፡፡ እኔ እስከማውቀው ድረስ ያለንበት ስልጣኔ የሰው ልጅ የኖረበት ዘመን ሁሉ ድምር ውጤት ነው፡፡ አሁን ማለት ያ ሁሉ ማለት ነው፤ ከባለፈው የተፈታ አሁን የለም፡፡ ከባለፈው የተቆራረጠ አሁንነት፣ ማንነት የለም፡፡ እውነትም እንዲሁ ናት፤ እውነት ለአሁን ነው፤ አሊያም አሁን ማለት በጃችን ስላለው መረጃ ብቻ እያወራን ነው ማለት ነዉ፤ ፕላቶን ዲያሎግ የሚለው ለዚህ ነው፡፡ በየትኛውም ምልልስ የማናቸውም ሀሳብ የመጨረሻ እውነት አይሆንም፡፡

ኢህአዴግ እውነት ማለት ራሱ ይመስለዋል፡፡ በትምህርቶቻችን ዲያሎግ የሚል ነገር የለም፡፡ ይህ ቀርቶ ዲያሎግን ያላካተተው የፍልስፍና ት/ት እንኳ እንዲዘጋ ይፈለጋል፡፡ ለዚህ ነው ዶ/ር ዳኛቸው አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከመደፈሩም በላይ እነ ጁነዲን ሳዶ በየ6 ወሩ እየመጡ ፕሬዝዳንቱን ከጀርባ ባይተነፍሱበት እንደሚፈልጉ የተናገሩት፡፡

አዲስ ነገር መስማት መቻል አለብን፤ ግሪካዉያን ለዚህ የተሰሩ በመሆናቸዉ ዘሬ ባለም የነሱ የስልጣኔ መንፈስ ያልሰፈረበት ሀገር የለም፤ በተለይ አዉሮፓዉያን፡፡ ጳዉሎስ የሚባለዉ የወንጌል ሰባኪ አዲስ ነገር መናገሩን ያወቁት ግሪካዉያን መንገደኛ ዝር በማይልበት አሪዮስ ፋጎስ በተባለ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ግቢ ዉስጥ እንድናገር እድል ሰጥተዉታል፡፡ የዛሬዉ ፓርላማ እንደማለት ነዉ፡፡

በሀገራችን ዛሬም ከሀያ አመታት በፊት መናገር የጀመሩት አቶ መለስ ዜናዊን ነዉ የምንሰማዉ፤ በቢሮም፣ ጳዉሎስ በተጋበዘበት ፓርላማም፡፡ ሚኒስቴር እንኳ አይናገርም፤ ተቃዋሚዎች ከተናገሩ ሽብር ነዉ፡፡ በኢትዮጵያ ያለው ነገር የሚገርም ነው፤ ዲያሎግ የሚባል ነገር የራስ ምታት ነው፡፡ ለዚህ ነው ጠ/ሚ/ሩ ብቻ አውሪ የሆኑበት (monolog) የሚሉት የአንድ ሰው ሁሉን የማስረዳት "የካድሬ አስተማሪነት አባዜ" የተፈጠረው፡፡

## "ልጆችሽን ለአንድ ወር እረፍት ላኪያቸው"

መቼም ያልሞተ ይገናኛል አይደል? ያው በመልዕክትም ቢሆን ብንገናኝ ምን ይልሻል፤ ምንም፡፡ እኔ እምለው ከዛሬ 60 ዓመት በፊት እኔ በቀውጢ ሰዓት ሳለሁ ልጆችሽን ልከሽ በነፍስ ደርሰሽልኛል፤ ውለታሽንም ቢሆን አልረሳሁም፡፡

ትዝ ይልሽ እንደሆን እኔ እና አንቺ ከጠበቀው ወዳጅነታችን ይልቅ የነፃነት ጠበቃ የሆኑ ልጆችሽ ዳዳ ጐድጓዳዬን ጐብኝተው ተመጣጣኝ እንደነበርንም አይደለም የነገሩኝ? ዛሬ ግን ስላንቺ ስሰማ ውስጤ ይሸበራል፤ ይቆጨኛልም፡፡ ለምን ብትይ ያኔ ልጆችስ የነበራቸው ያ የነፃነት ፋና ወኔ ዛሬ እንደሌለና ቤትሽ በውጥረት መንገሱን ከወረኞቹ መገናኛ ብዙኃን ሰምቻለሁና፡፡

የልጆችሽ ብሶት ከሰማይ ይልቅ በምድር፤ ከአስተዳዳሪዎችሽ ይልቅ የሩቅ ወዳጆችሽ ዘንድ ይሰማል፡፡ ለምን ይሆን? በተለይ የልጆችሽ ስደት፣ ርሃብ፣ ምሬት፣ የፍትህና የነፃነት እጦት ኽረ ስንቱ ይነገራል፡፡ ያኔ አንቺን ላለማስደፈርና ለማስከበር ስንት ጀግኖች እንዳልተዋደቁልሽ ዛሬ ዛሬ ስሰማ "አሸባሪ ናቸው" እየተባሉ ባንቺው ምድር ሲንከራተቱና ሲሰቃዩ ባዛኙቱ ልደታ የተሰየመው ፍርድ ቤት ያለውን ሁኔታ የታዘበ ልጄ አጫውቶኛል፡፡ አዘንኩልሽ፣ ከልቤም አምርሬ አለቀስኩልሽ፡፡ ፈጣሪ ፅናቱን ሰጥቶ ለአሳሪዎች ቅንልቦና፣ ፍቅርና ርህራሄን፤ ለታሳሪዎች ደግሞ እርቁንና ምህረቱን እንዲሰጥልሽ ተመኘሁ፡፡

እኔ ያው እንደምታውቂው በሚዳሰስና በሚጨበጥ የምጣኔ ሀብት ዕድገት፣ የመልካም የሆነ የሰብዓዊ መብት አያያዝ፣ የመልካም አስተዳደርና የዴሞክራሲያዊ መብት አጠባበቅ እምርታ ማሳየቴን ዓለም ያወቀው ፀሐይ የሞቀው መሆኑን ሳትሰሚ የቀረሽ አይመስለኝም፡፡ ያንቺ ዕድገት ግን ዜጐሽ ሲራቡ በአመራሮችሽ አምባገነንነት ጥጋብ ሲሆን ይህም ከራሴ ጐረቤት ያመሳስልሻል፡፡ የነጻነት ፋና ወጊው ህዝብሽ ነፃነቱን እንዳጣም ሰምቻለሁ፤ አልሰማሁ አይምሰልሽ ሰምቻለሁ፡፡ ግን


ብስራት ወ/ሚካኤል

አይዞሽ እሺ፡፡ ሰው ያገኘሽ ዕለት ነፃ ይወጣሉ፡፡ አንቺም ያልፍልሻል፡፡

እኔ እምለው አመራሮችሽ የአምባገነንነትን መፈወሻ ፀበል አላገኙም ልበል? ወይስ አይፈልጉትም? ውድ ወዳጄ አይዞሽ ተስፋ አትቁረጪ፡፡ ልጆችሽ የነፃነት እና የምግብ ርሃብ ሲጠናባቸው እንደኔ ልጆች ይበረቱ ይሆናል፡፡ እስከዛው ግን ስላንቺ መልካም የምሰማበትን ቀን እየተመኘሁ ለዛሬው ተሰናበትኩ፡፡ ያንቺው የልብ ወዳጅ ደቡብ ኮሪያ ለማልረሳሽ ኢትዮጵያ፡፡ ኢትዮጵያም የያኔውን አቅሟንና አቋሟን እያስታወሰች ብትቆጭም ወዳጇ በላከችላት ደብዳቤ አልከፉትም፡፡ ይልቁንም ወዳጅ አያሳጣኝ ማለት እንዲህም አይደል? በማግስቱ ሌላም የተላከ ደብዳቤ ስላለ ብታነቡትስ

ወዳጄም፣ ስለምን እንደምጀምር ባይገባኝም የኋሊት ጉዞሽ ስላልተመቸኝ እባክሽ "ቀኝ ኋላ ዙር" የሚለውን መርህ ትተሽ "ወደፊት ሂድ" የሚለውን መተግበር ይገባሽ ነበር፡፡ ነገር ግን ይህን ባለማድረግሽ በነበረ እየቀረሽ እንደሆነ ይታወቅሻል? አዝናለሁ፡፡ ያው ያንቺን ቋንቋ መናገር ባልችልም መንደሪንን ወደ አንቺ ቋንቋ አስተርጉሜ ስላንቺ የተሰማኝን ልገልፅ ወደድሁ፡፡

መቼም አመራሮችሽ ክፍውን እንጂ በጐ ነገርን መኮረጅም ሆነ መማር ያልፈጠረባቸው በመሆኑ ለልጆችሽ ክፉ አባዜ ተጭነው መምጣታቸውን ከልጆቼ አንደበት ሰምቻለሁ፡፡ የዛሬ 21 ዓመት ገደማ ይመስለኛል አንዲቷን ሀገር ሁለት ቦታ እንድትገነጠይ የዓለም መንግስታት ድርጅት ቢሮ ደጅ የጠኑት ልጆችሽ በስቃይ እየመሩ እንደሆነ ከብላቴናዎች እሮሮ መረዳት ችያለሁ፡፡

የሚገርመው ታይዋን የምትባል አንዷ ጐኔ ከእኔ መነጠል ፈልጋ ለእኔም ለምዕራባውያንም አቤቱታ አቅርባ ነበር፡፡ አንቺን እየመሩ ያሉት ጐበዝ "የለም! ታይዋን ከእናት ሀገሯ መነጠል የለባትም" ሲሉ ተሟገቱልኝ፡፡ ያኔ እንዴት ደስ እንዳለኝ ብነግርሽ መቼም ውስጥሽ በቅናት እንደሚያር አልጠራጠርም፡፡ ግድየለም ቻይው፡፡

እኔ ያልገባኝ! አንቺን ለመገነጣጠል ደጅ የጠኑት ለእኔና ታይዋን አንድ መሆን ምን ያህል ቢቆረቆሩልኝ ይሆን? እውነት ለመናገር የሁለተኛው ቻይና ክንፍ መሪ ነበር የመሰሉኝ፡፡

እቴ! አንዳንዴ ናፍቆ ብዙ ያስወራ የለ? ምን ላድርግ ብለሽ ነው፡፡ ቆይ የአንቺ አባወራ ከእኔ ጌቶች አፈናንና አምባገነንነትን መውረሳቸው ለምን ይሆን? ይገርምሻል ልጆቼን ለዓመታት እየመራ ያለው ኮሚኒስት ስርዓት የአምባገነንነትን ካባ ማውለቅ ባይችልም ልጆቼ ዘንድ ሙስና ሲፈፀም የተገኘ በስቅላት ስለሚቀጣ በልጆቼ ዘንድ ሙስና ሃራም መሆኑን ዓለም ያውቀዋል፡፡ አመራሮቼ ለሀገር ያላቸው ፍቅርማ በቃላት ተገልፆ አያልቅም፡፡ በቴክኖሎጂ መስክም ቢሆን ያለው ዕድገት ልክ እንደ ህዝቤ ቁጥር ነው ብል ማጋነን አይሆንብኝም፡፡ አንቺ ጋር ግን በተቃራኒው ያለ ይመስለኛል፡፡ ሆዬ!

ያንቺ ጌቶች ግን መልካሙን መዋስ አልፈጠረባቸውም እንጂ አምባገነንነቱን ብቻ ከእኔ መዋሳቸው አሳዝኖኛል፡፡

ወደ ገፅ 12 ይዞራል....

# ቆይታ

# እኛ ለወጣቱ ምን አስተላልፈን ነው የምንወቅሰው?

የዛሬው እንግዳችን አቶ ዳምጠው አለማየሁ ይባላሉ፡፡ በአሁን ወቅት የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ የብሔራዊ ምክር ቤት አባል ሲሆኑ በተጨማሪም የፓርቲው የፖለቲካ ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ አባልና የትምህርትና ስልጠና ዘርፍ ኃላፊ ናቸው፡፡ በተለያዩ ርዕስ ጉዳዮች ከባልደረባችን ብስራት ወ/ሚካኤል ጋር አጭር ቆይታ አድርገዋል፡፡

➢ ማኅበራዊ ህይወትዎ እንዴት ነው?

ጥሩ ነው፡፡ ያው ባለትዳርና የልጆች አባት ነኝ፡፡ በአካባቢዬ ካለው ማኅበረሰብም በጥሩ መግባባት እየኖርኩ ባሉት ማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች ሁሉ እሳተፋለሁ፡፡

➢ ወደ ፖለቲካው ህይወትስ መቼ ገቡ?

ያኔ የ17 ዓመት ልጅ እያለሁ በወቅቱ (በ1960ዎቹ) እንቅስቃሴ ላይ በመሳተፍ ነው የጀመርኩት፡፡ ከዛን ጊዜ ጀምሮ ለሀገራችን ዜጐች የተመኘሁት መልካም ነገር ስላልተሳካ ዛሬም ድረስ እየታገልኩ ነው፡፡ በተለይ ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘ ጀምሮ በመአህድ፣ በመኢአድ፣ በብርሃን ፓርቲ ውስጥ የበኩሌን አስተዋፅዖ አበርክቻለሁ፡፡ በአሁን ወቅት ብርሃን ከአንድነት ጋር ከተዋሃደ በኋላ በአንድነት ውስጥ የፖለቲካ ጉዳይ ውስጥ የቻልኩትን እየሰራሁ ነው፡፡

➢ አሁን ያሉበትን ፓርቲ ለምን መረጡ?

ያው ከያዘው ሀገራዊና ህዝባዊ ዓላማ አንፃር ነው፡፡ አንድነት ውስጥ ያሉት አመራሮችና አባላት ትልቅ ሀገራዊ ስሜት ያላቸው፣ ኃላፊነትን ለመሸከም የተዘጋጁ እና እጅግ በጣም ጥሩ የሆነ ፕሮግራምና መተዳደሪያ ደንብ ያለው በመሆኑ ልመርጠው ችያለሁ፡፡ ምክንያቱም የእኔም ዓላማ በመሆኑ ልመርጠው ችያለሁ፡፡ ሌላው በውስጡ ያለውም አሰራር የተሻለ ነው፡፡ ምክንያቱም የእኔም ዓላማ ሀገራዊና ህዝባዊ ጥቅምን ለማስጠበቅ ስለሆነ አንድነት ፓርቲ ውስጥ ሆኜ ለመታገል ወስኛለሁ፡፡

➢ ከዚህ በፊት ከነበረዎት የትግል ልምድና ተሞክሮ አንፃር የታዘቡትን ቢነግሩኝ፡፡

ብዙ ጊዜ የታዘብኩት አንዳንድ በፖለቲካ ትግል ውስጥ ያለው እንቅስቃሴ አመራር ላይ ያለውን ግለሰብና ፍላጐት ላይ የተንጠለጠለ ነው፡፡ ገዥው ፓርቲ ጋርም ብትሄድ በአሁን ወቅት የሀገሪቱ ፈላጭ ቆራጭነትም በግለሰብ እጅ ወድቋል፡፡ ይሄ ደግሞ አደጋ አለው፡፡ ለዚህም ነው ተቃዋሚዎችም ለውጤት ያልበቃነው፤ ገዥው ፓርቲ (ኢህአዴግም) ሀገሪቷን በተሻለ መልኩ ያልመራው፡፡ አሁን አንድነት ፓርቲ ውስጥ ግን በአንድ አመራር ፍላጐትና ጥቅም ላይ የተንጠለጠለ ባለመሆኑ በፊት ካሳለፍኩት ልምድ የተሻለ ነው፡፡

➢ ቤተሰብዎ የእርስዎን የፖለቲካ ተሳትፎ ምን ያህል ይደግፍታል?

ቤተሰቦቼ በተለይ ባለቤቴም ሆነች ልጆቼ ጥሩ ይደግፉኛል፣ ሀሳቤንም ይረዱልኛል፡፡ ነገር ግን የማደርገው የትግል አስተዋፅዖ ፍሬ የሚያፈራ መሆን እንዳለበት ያስጠነቅቁኛል፡፡ ምክንያቱም እስካሁን ካሳለፍኩት የትግል ጉዞ አንፃር ድጋፋቸው ባይለየኝም ውጤት ላይ ደርሰን ባለመታየታችን ደስተኛ አይደሉም፡፡ አሁን ግን የማደረገው ትግል ፍሬያማ መሆን እንዳለበት እኔም እየተሰማኝ ስለሆነ ከትግል አጋሮቼ ጋር በፅናት እየተንቀሳቀስኩ ነው፡፡

➢ በአሁን ወቅት በእርስዎ ዕድሜ አካባቢ ያሉ አባቶችና እናቶች ወጣቱን ሀገራዊ ስሜት የለውም ሲሉ ይወቅሳሉ፡፡ እርስዎስ?

እኔ በዚህ አልስማማም።

➢ ለምን?

ምክንያቱም መጀመሪያ እኛ ለወጣቱ ምን መልካም የሀገሪቷንና የህዝባችንን ታሪክ ነገርነውና ነው የምንወቅሰው? አሁን በገዥውም ሆነ በተቃዋሚዎች ውስጥ ያለነው ተመሳሳይ ትውልዶች ነን፡፡ ለወጣቱ ጥላቻንና ቂም በቀልን አትርፈን ለመውቀስ ሞራሉም ያለን አይመስለኝም፡፡ ቢቻል በገዥውም ሆነ በተቃውሞ ጐራ ያለን አባቶችና እናቶች ለልጆቻችን እውነተኛውን የሀገራችንን ታሪክ ልንነግራቸውና ለወጣቶች መልካም አርአያ ልንሆን ይገባል፡፡ ወጣቶችንም ልናቀርባቸውና በመልካም ጐን ልናንፃቸው ይገባል፡፡ ስለዚህ ወጣቱን መውቀስ ትተን ልናቀርበውና በትውልድ መካከል የተፈጠረውን ክፍተት ልንሞላው ይገባል ባይ ነኝ፡፡

➢ ብዙዎቹ የእርስዎ አቻዎች ደፍረው ወደ ፖለቲካው በንቃት ሲሳተፍ አይታይም፡፡ ለምን ይመስሎዎታል?

የየራሳቸው ምክንያት ይኖራቸዋል፡፡ ምናልባት ከዚህ በፊት በአንዳንድ ሰዎች በሚያዩት አላስፈላጊ ድርጊት አዝነውም ሊሆን ይችላል የሚል እምነት አለኝ፡፡ ይህ ማለት ግን ከታሪክ ተጠያቂነት ይድናሉ ማለት አይደለም፡፡ ለምሳሌ እኔ ምንም እንኳ ሽበት ብታይብኝም እስከቻልኩት ድረስ እታገላለሁ፡፡

➢ ብዙ ጊዜ ኢህአዴግን ብቻ ስትወቅሱ ይሰማል፡፡ ተቃዋሚዎችስ ጋር ችግር የለም ብለው ያስባሉ?

በእርግጥ በተፈጠሩት የሀገሪቱ ችግሮችና ባለው እንቅስቃሴ መዳከም የመጀመሪያው ተጠያቂ ኢህአዴግ ቢሆንም ተቃዋሚዎች ጋርም ችግር እንዳለ የሚካድ አይደለም፡፡ በተለይ ተቃዋሚዎች የፖለቲካ ፓርቲንና ፖለቲካን ከሀገራዊ እና ህዝባዊ ዓላማ ይልቅ የስራ መስክ በማድረግ ቁጭ ብለው ሳይሰሩ ደመወዝ የሚቀበሉ አሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ ተቃዋሚ ነን እያሉ የገዥው ኢህአዴግ አጋር ሆነው ሲያገለግሉ አንዳንድ የፖለቲካ ድርጅቶች ደግሞ ተቃዋሚዎችን ብቻ ለመቃወም የተመሠረቱ የሚመስሉ አሉ፡፡ አንዳንዶቹ ድርጅቶች ደግሞ በግለሰብ አመራር ፍላጐትና ጥቅም ላይ የተጠንጠለጠሉ ስለሆነ በአግባቡ የህዝብን መብትና ጥቅም ከማስጠበቅ ይልቅ የወገኖቻችንን ስቃይ እያበረቱ ያሉ አሉ፡፡

እርስ በርስ ተቀራርቦና ቢያንስ በሚያስማማ ሀገራዊ ጉዳይ ላይ እንኳ ተቀራርቦ የመስራት ነገር ብዙ አይታይም፡፡ በአጠቃላይ ተቃዋሚዎች ጋርም ችግር የለም ማለት አይቻልም፡፡ ቢሆንም ግን አንድነት ፓርቲ ከሌሎች የተሻለ ነው፡፡

➢ መፍትሄው ምንድነው ብለው ያስባሉ?

ተቀራርቦ መስራትና ለሀገርና ለህዝብ ጥቅም ቅድሚያ መስጠት ነው ብዬ አስባለሁ፡፡ የግል ፍላጐትና ጥቅምን ለማስጠበቅ ከመሯሯጥ ለቆሙለት ህዝባዊ ዓላማ ትኩረት መስጠቱ ጥሩ መፍትሄ ነው፡፡ ገዥው ፓርቲም ቢሆን ዜጐችን ከማስፈራራትና ከማሰር ይልቅ ሀገሪቱን ከገባችበት ችግር ለማውጣት ቅንነት ቢኖረው ለመንግስትም ለሀገሪቱም ሆነ ለህዝቡ እንዲሁም ለተቃዋሚዎችም ይጠቅማል፡፡

➢ በአሁን ሰዓት ስለ ኢትዮጵያ ምን ታዝበዋል? በአጭሩ ቢገልፁልኝ፡፡

በሀገራችን ብዙ ችግር አለ፡፡ የኑሮ ውድነት፣ የፖለቲካ አለመረጋጋት፣ የመሰረታዊ ፍጆታዎች አቅርቦት ማነስ፣ የሀገሪቱ ገንዘብ መጋሸብ፣ የሸቀጦች የዋጋ መናር፣ ጥራት ያለው ትምህርት ለዜጐች ያለመዳረስ፣ ፍትሃዊ የሀብት ክፍፍል ያለመኖር፣ የተዛባና ያልተረጋጋ የንግድ ሥርዓት መኖር ህዝቡን ለከፍተኛ ችግር አጋልጦታል፡፡ ሀገራችንም ብትሆን የተረጋጋ ሁኔታ ላይ አይደለም ያለችው፡፡

➢ አንድነት በአሁኑ ወቅት እንዴት እየተንቀሳቀሰ ነው?

በጥሩ ሁኔታ እየተንቀሳቀሰ ነው፡፡ ነገር ግን የአንድነት ፓርቲ እንቅስቃሴ በአጭር ጊዜ ከግቡ እንዲደርስ የመላው ኢትዮጵያውያን ንቁ ተሳትፎ አስፈላጊ ነው፡፡ ምክንያቱም የህዝብ ተሳትፎ ወሳኝ ነውና፡፡ አሁን ህዝባዊ ውይይቶችንም በስፋት እያካድን ስለሆኑ ሁሉም ሊተባበረን ይገባል፡፡

➢ በመጨረሻ መናገር የሚፈልጉት ነገር ካለ ዕድሉን ልስጥዎት

ሁሉም ዜጋ ሀገሪቱን ከገባችበት አዘቅት ውስጥ ለማውጣት የበኩሉት ድርሻ እንዲወጣ ጥሪ ነው የማስተላልፈው፡፡ በተለይ ተቃዋሚዎችም ሆኑ ኢህአዴግ የመጠላለፍና የጥላቻ ፖለቲካን ከማራመድ ቀርበን በአንድነት ልንወያይና ልንጋገር ይገባል፡፡ ተቃዋሚዎችም ልዩነታችንን አጥብበን ሀገራችንን ከውድቀት ህዝባችንን ከስቃይ ልንታደግ ይገባል እላለሁ፡፡ ህዝቡም ቢሆን ለመብቱ የሌሎችን ግፊት ከመጠበቅ ይልቅ በራሱ መብቱንና ጥቅሙን ለማስጠበቅ ሊታገል ይገባል፡፡ አሁን ባለው ሁኔታ ሀገራችን የምትቀጥል ከሆነ ምናልባት በድንገት ፈንድቶ ያልታሰበ አሳዛኝ ክስተት ልናስተናግድ እንችላለንና ሁላችንም ልናስብበት ይገባል፡፡



## ኢፍትሐዊነትንና አድሎን ...

ከ ገፅ 15 የዞረ....

በፎቶግራፍ ላይ እንደሚታየው ቁጥሩ ብዙ የሆነ ህዝብ ሜዳ ላይ ተሰብስቦ ይታያል፡፡ እንደሚታወቀው አነግ በ1984 ዓ/ም በመጨረሻ ሽግግር መንግሥቱን ለቆ ከወጣ በኋላ እንዲህ ዓይነት ስብሰባ በመሀል ከተማ አደባባይ ሊደረግ ይችላል ተብሎ አይታሰብም፡፡ በፎቶ ግራፉ ላይ የሚታዩ ሰዎች ብዙዎች በህይወት የሉም፡፡ በፎቶግራፉ ላይ የሚታየው የራሴ ገጽታም ከዛሬ ጋር ሲስተያይ የፎቶውን ዕድሜ ይናገራል፡፡ በፎቶግራፉ ላይ የሚታየው ቦታም ዓለምተፈሪ መሆኑ ተለይቶ ይታወቃል፡፡ እኔ ደግሞ በ1985 ዓ/ም ከዚያ ተዛውሬ ስለሄድኩ እና ወደዚያ ለመመለስ እድሉ ስላልነበረኝ፣ ቢኖረኝ ኖሮም ያንን ሰብሰባ ማካሄድ እንደማልችል ይታወቃል፡፡

በአጠቃላይ ከዛሬ ሃያ ዓመት በፊት በወቅቱ ህጋዊ የነበረና በሚኒስትሮች ም/ቤት አራት የካቢኔ ሚኒስተሮች የነበሩትና መዲናዋን (አዲስ አበባን) ጭምሮ በአርማዎቹ አጥለቅልቆት በነበረ ድርጅት አርማ ጋር የተነሳኸው ፎቶ ግራፍ የአገር ግዛትና ፖለቲካዊ አንድነት ለመንካትህ ማስረጃ ነው ተብሎ ሊቀርብብኝ ስለማይገባ ክቡር ፍ/ቤቱ ውድቅ እንዲደረግልኝ እጠይቃለሁ፡፡

ማጠቃለያ

ያለመተደል ሆኖ በአገራችን መልካም አስተዳደር አፈአዊ እንጂ ተግባራዊ ሆኖ ስለማያወቅ አንዱ የሠራውን ሌላው እያፈረሰ በዓለም ፊት በኩራት አንገታችንን ቀና የምናደርግበት ሳይሆን በሀፍረት የምንሸማቀቅበት፤ ለልጆቻችንም ተስፋን ሳሆን የስጋት ቅርስ እየተውንላቸው አበሳን እንደ ዱላ እየተቀባበልን ዛሬ ላይ ደርሰናል፡፡ ይህ እንዳይቀጥል የሳተው በጊዜ እንዲመለስ የተጣመመው እንዲቃና የተበላሸው እንዲስተካከል ጎረቤት ሳይሰማ፣ ፈረንጅ ገመናችንን ሳያውቀው አድብተን ሰንጠፋፋ ችግራችን ገለጥለጥ አድርገን ተወያይተን ተከራክረን ተወቃቅሰን መፍትሔ እናበጅለት፡፡ ይህንንም አንዱ ባንዱ ላይ ዱላ ሳይሰነዝር ቃታ ሳይስብ፣ ወደ እስር ቤት ሳይጎትተው በሠላማዊ መንገድና በፍቅር እናድርገው የሚል ጽኑ አቋም ነው፡፡ እኔና ድርጅቴ የምናራምደው፤ ይህ በኛ በጎ ጥረትና ፍላጎት ብቻ የሚሳካ ባይሆንም እኛ ግን በዚሁ መንገድ እንጓዛለን፤ ኢፍትሃዊነትንና አድልኦን አሜን ብሎ ውርደት ከመቀበል መከራና ስቃይን በክብር ማስተናገዳችንን እንቀጥላለን፡፡ በመጨረሻም ፍትህ ከጎናችን ትቆማለች፡፡

# በአሜሪካ የሚገኘዉ ሲኖዶስ ለሙስሊሞች ተቃዉሞ ድጋፍ ሰጠ



በአቡነ መልከዔዲቅ የሚመራዉና በስደት የሚገኘዉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ሲኖዶስ ባወጣዉ የአቋም መግለጫ የሙስሊሞች የሙብት ጥያቄ እንደሚደግፉ ማስታወቁን ምንጮቻችን ገለፀ፡፡ ሲኖዶሱ 33ኛ መደበኛ ጉባኤዉን ባደረገበት ወቅት በበርካታ አገራዊ ጉዳዮችም ላይ እንደተወያየበት የገለፁጽ ምንጮቻችን በተለይም በአሁኑ ወቅት በመላ ሀገሪቱ የተዳረሰዉን የሙስሊሞች የሙብት ጥያቄ ላይ ሰፊ ዉይይት ማድረጉ ታዉቋል፡፡

ምንጮቹ አክለዉም ሲኖዶሱ በአቋም መግለጫዉ መንግስት በሃይማኖት ጉዳዮች ውስጥ የሚያደርገውን ጣልቃ ገብነት በመቃወም፣ ከሙስሊም ወንድሞቻችን ጎን እንቆማለን ማለቱን ዘግበዋል፡፡ ሲኖዶሱ በመንግስት ተገደሉ ላላቸው ሙስሊም ወገኖች ሀዘኑን ገልጧል፡፡ በተቃውሞ ተሳትፈው በእስር ላይ የሚገኙ ሙስሊም ወንድሞቻችንና እህቶቻችን በአፋጣኝ እንዲፈቱ ጠይቋል፡፡ ከስፍራው የደረሰን መረጃ እንዳመለከተው በዋልድባ ገዳም ዙሪያ እየደረሱ ባሉ ችግሮች ዙሪያ በሰፊው የተወያየው ቅዱስ ሲኖዶስ ህዝበ ክርስቲያኑ ከሙስሊም ወንድሞቹና እህቶቹ ጋር በመተባበር በዋልድባ ገዳም ላይመንግስት እያደረሰ ያለውን ችግር ህዝበ ክርስቲያኑ ከሙስሊሙ ወንድሞቹ ጋር በተቃዉሞ እንዲተባበር ጠይቋል

እነረዲ.ቃወም ጥሪ አስተላልፏል፡፡

ይህንን ዜና አስመልክቶ ምላሻቸውን እንዲሰጡን የጠየቅናቸው አዲስ አበባ ያለው ቅዱስ ሲኖዶስ የጠ/ቤተክህነት ዋና ጸሀፊ ብፁዕ አቡነ ህዝቅኤል ስለጉዳዩ የሰሙት ነገር እንደሌለና በሙስሊሞች እንቅስቃሴ ዙሪያም በስልክ ምንም አይነት ምላሽ መስጠት እንደማይፈልጉ ተናግረዋል፡፡

የሙስሊሞችን የሙብት ጠያቄ እያስተባበረ ያለው ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶ አቡበከርም ኮሚቴያቸው በጉዳዩ ላይ ገና እንዳልተወያየበት ተናግረው የግል አስተያየታቸውን ከመስጠት ተቆጥበዋል፡፡

## ርዮት ዓለሙ በሚቀጥለው ጥቅምት ወር ውስጥ ሽልማቷን ትቀበላለች

የተፈረደባትን 14 ዓመት እስራትና 33 ሺ ብር ቅጣት በመቃወም በይግባኝ ክርክር ላይ የምትገኘው ጋዜጠኛና መምህርት ርዕዮት ዓለሙ የተሸለመችውን ዓለም አቀፍ ሽልማት በጥቅምት ወር 2005 ዓም በአሜሪካን አገር በሚከናወን ሥነ-ሥርዓት እንደምትሸለም ተዘገበ፡፡ እራሳቸውን ለአደጋ በማጋለጥ በአስቸጋሪ አካባቢዎች እውነተኛ ዘገባዎች መዘገብ ለቻሉጋዜጠኞች የሚሰጠውን ሽልማት በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳድራ አሸናፊ የሆነችው ኢትዮጵያዊቷ ጋዜጠኛ ርዕዮት ዓለሙ በፈረንጆች አቆጣጠር ኦክቶበር 24 እና 29 በኒዎርክና በሎሳንጀለስ ከተሞች እንደሚሰጥ ታውቋል፡፡

ከርዮት ጋር አሸናፊ ሆነው የተመረጡት ከአዘርባጃንና ከፍልስጢም ከተመረጡት ሁለት ሴት ጋዜጠኞች ጋር መሆኑን የዓለም አቀፉ የሴቶች ሚዲያ ፋውንዴሽን በዘገባው አስታውቋል፡፡ ርዕዮት ዓለሙ ከኮተቤ መምህራን ማሠልጠኛ ኮሌጅ ሠርተፍኬትና በዲፕሎማ ከመመረቋም በላይ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በእንግሊዘኛ ቋንቋ፤ በቲያትርና ሥነ-ጥበብ ሞያ ሁለት ዲግሪዎችን የተቀበለች ውጣት ስትሆን የጋዜጠኝነት ሞያን አጥብቃ ስለምትወድ አጫጭር ኮርሶችንና ውርክሾፖችን በመውሰድ የጋዜጠኝነት ሞያዋን አዳብራለች፡፡ ርዕዮት ወቅታዊ ሞጋችና ገንቢ ትችቶችን በማቅረብ የምትታወቅ ጋዜጠኛ ነች፡፡

## ኢቴቪ በወንጀል...

ከ ገፅ 1 የዞረ....

እኛ የምናውቀው አዘጋጅና አቅራቢ ራሱ ጋዜጠኛው አብዲ ከማል መሆኑን ነው ብለዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የኢቴቪን ነገረፈጅ አቶ ተማም ሁሴንን የዘጋቢ ፊልሙ አዘጋጅ ማነው? ሲል የጠየቃቸው ሲሆን አቶ ተማምም የብሔራዊ መረጃና ደህንነት ከኢቴቪ ጋር በመተባበር ያዘጋጀው መሆኑን አስረድተዋል፡፡ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ ክሱ ጉዳዩ በፍ/ቤት እየታየ ነው ተብሎ በኢቴቪ የተገለፀውን አስመልክቶ የክሱ የመዝገብ ቁጥርና ፋይሉ ተያይዞ እንዲቀርብ ትዕዛዝ በመስጠት መዝገቡን መርምሮ ምላሽ ለመስጠት ለግንቦት 10 ቀን 2004ዓ.ም ከቀኑ 8፡15 ሰዓት ተለዋጭ ቀነ ቀጠሮ ሰጥቷል፡፡

በተያያዘ ዜና በነ አንዱዓለም አራጌ የክስ መዝገብ ፍርድ ይሰጣል ተብሎ ለግንቦት 3 ቀን 2004 ዓ.ም ፍ/ቤቱ ቀነ ቀጠሮ ሰጥቶ እንደነበር ይታወቃል፡፡ በዕለቱ የፍርዱን ሂደት ለመታዘብ የአሜሪካን አምባሳደርና የተለያዩ ዓለም አቀፍ ዲፕሎማቶችን ጨምሮ የተከሻስ ቤተሰቦችና ወዳጆች፣ የአንድነት ፓርቲ አመራሮችና አባላት፣ የሀገር ውስጥና ዓለም አቀፍ የመገናኛ ብዙኃን ጋዜጠኞች ተገኝተዋል፡፡ ነገር ግን የችሎቱ አዳራሽ በመጥበቡ ምክንያትም አብዛኞቹ ጋዜጠኞች፣ የተከሳሽ ቤተሰቦችና ወዳጆች እንዲሁም የአንድነት ፓርቲ አመራሮች ሳይገቡ መቅረታቸውን ለመታዘብ ችለናል፡፡ አቶ አንዱዓለም አራጌም ፍርዱን የሚታዘቡ ቤተሰቦቻችንና ጋዜጠኞች ስላልገቡ በሰፊ አዳራሽ እንዲሆን የጠየቁ ሲሆን ፍ/ቤቱ የቀረቡትን ማስረጃዎች መርምሮ አለመጨረሱን በመግለፅ በዕለቱ ፍርድ እንደማይሰጥ በማስታወቅ ፍርድ ለመስጠት ለሰኔ 14 ቀን 2004 ዓ.ም ተለዋጭ ቀጠሮ ሰጥቷል፡፡

## አቶ በቀለ ገርባ የመከላከያ ምስክሮቻቸውን አሰምተው ጨረሱ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ ከፍተኛ አመራርና የኦፌዴን ም/ሊቀመንበር እንዲሁም የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህር የሆኑት አቶ በቀለ ገርባ ቀሪ አራት የመከላከያ ምስክሮቻቸውን ቃል አሰምተዋል፡፡

የመከላከያ ምስክሮቻቸውም የአቃቤ ህግ ምስክሮችን የሚያስተባብል ጭብጥ መሆኑ ታውቋል፡፡ በዕለቱ የቀረቡት መከላከያ ምስክሮችም አቶ አንዱዓለም አራጌ፣ አቶ ጉቱ ሙሊሳ፣ አቶ ኦልባና ሌሊሳ እና ወ/ት በቀለች ደገፉ ናቸው፡፡

በተለይ አቶ አንዱዓለም በአቶ በቀለ ገርባ ላይ የአቃቤ ህግ ምስክር የነበሩት ተማሪ ኢዮስያስ አበራ በራሱ ፈቃድ የመድረክ ድርጅት አባል መሆን እንደሚፈልግ ጠይቋቸው እሱ ኦፌዴን ውስጥ ኦሮምኛ ባለመቻሉ ወደ አንድነት ቢገባ ተመሳሳይ ዓላማና ትግል እንደሚያደርጉ ገልፀውለት እንደነበርና ከዚያም ከአንዱዓለም አራጌ ጋር እንዲገናኝ እንዳደረጉት ተናግረዋል፡፡ አቶ አንዱዓለምና ተማሪ ኢዮስያስ ካዛንቺስ ተገናኝተው ስለ ሰላማዊ እና ህጋዊ ትግል መወያየታቸውን ተናግረዋል፡፡

አያይዘውም ተማሪ ኢዮስያስ አበራም የኢህአዴግ አባል እንደሆነና ጥንቃቄ እንዳደርግ አቶ በቀለ ነግረውኛል ሲሉ ለፍ/ቤቱ አስረድተዋል፡፡ ከአቃቤ ህግም የኢህአዴግ አባል መሆኑን ካወቁ እንዴት ሊያነጋግሯቸው ቻሉ ተብሎ ለቀረበላቸውም ጥያቄ በፊትም ብዙ ደህንነቶችና የኢህአዴግ አባላት ያናግሯቸው እንደነበርና "ዓላማችን ስለሰላማዊና ትግል ማስተማርና እነሱንም መቀየር ስለሆነ እያወቅሁ አነጋግሬአለሁ" ሲሉ የምስክርነት ቃላቸውን ሰጥተዋል፡፡ የተከበሩ አቶ ጉቱ ሙሊሳ (የቀድሞ ፓርላማ አባል)፣ አቶ በቀለ ገርባን ከመታሰራቸውና ከቃሊቲ ማረሚያ ቤት ውጪ ፊት ለፊት እንደማያውቋቸውና ያስተዋወቃቸውም አቶ ኦልባና ሌሊሳ በቅርቡ እስር ቤት እያሉ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ የአቃቤ ህግ ምስክር የነበሩት እና ስማቸውን ኢማና ኢርኮ ያሉት ግለሰብ አቶ ጉቱ ቤት ከአቶ በቀለ ገርባ ጋር ሄደናል ያሉት ስህተት መሆኑንና አብረውም ቤታቸው መጥተው እንደማያውቁና አስረድተዋል፡፡

አቶ ኦልባና ሌሊሳና ወ/ት በቀለች ደገፉ በበኩላቸው የአቃቤ ህግ ምስክር ሆነው የቀረቡት አቶ ኢማና ኢርኮ የተባሉት ግለሰብ ትክክለኛ ስማቸው ሽፈራው ኤቢሳ መሆኑንና የመኖሪያ አድራሻቸውም ነቀምት ሳይሆን አምቦ እንደሆነ አስረድተዋል፡፡ ምስክሩም ለረጅም ጊዜ የወንድማቸው የቅርብ ጓደኛ እንደሆነና የኦህኮ አባል እንደነበር ያሉት ሰነዶችና ፋይሉም አቶ ሽፈራው ኤቢሳ ስም እንዳለ አስረድተዋል፡፡

የአቶ በቀለ ገርባ ጠበቃም ለፍ/ቤቱ ለ1ኛ እና 2ኛ ተከሳሽ ሁለት ተጨማሪ መከላከያ ማስረጃ ያቀረቡ ሲሆን በተለይ ስሙን ኢማና ኢርኮ የተባለው ግለሰብ በእኛ ኪሳራ በፖሊስ ተይዞ ይቅረብና ማንነቱን የሚገልፅ ህጋዊ ሰነዶች እንዲረጋገጥልን ሲሉ ፍ/ቤቱን ጠይቀዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የቀረበውን ተጨማሪ የመከላከያ ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ትዕዛዝ በመስጠት የ2ኛ ተከሳሽ የአቶ ኦልባና ሌሊሳን የመከላከያ ምስክሮችን ቃል ለመስማት ለግንቦት 17 ቀን 2004 ዓ.ም ተለዋጭ ቀነ ቀጠሮ ሰጥቷል፡፡

### አቶ ተመስገን ዘውዴ ከመደበኛ ስራቸው ተሰናበቱ

የቀድሞ ፓርላማ አባልና የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ (አንድነት) ፓርቱ የውጭ ጉዳይ ኃላፊ አቶ ተመስገን ዘውዴ ባምቢስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ውስጥ ከሚሰሩበት መደበኛ ስራቸው መሰናበታቸው ተገለፀ፡፡

የፓርላማ የሥራ ዘመናቸውን በክብር ካጠናቀቁ በኋላ በድርጅቱ ውስጥ በጄነራል ማናጀርነት ተቀጥረው እየሰሩ እንደነበር የተጠቆመ ሲሆን ነገር ግን ድርጅቱ ቅጥር ከፈፀሙ ከወር በኋላ ኦፐሬሽንስ ማናጀር ሆነው ማገልገላቸው ታውቋል፡፡

ስለጉዳዩ አቶ ተመስገን ዘውዴን ጠይቀናቸው ከድርጅቱ እስከተሰናበቱበት ቀን ድረስ ያለምንም የስራ መመሪያ አንድ ዓመት ከ2 ወር አገልግሎት በኋላ ድርጅቱ የሀገሪቱ አሰሪና ሠራተኛ ህግ ከሚፈቅደው ውጭ የተቀጠሩበት የሥራ ቦታ ጊዜያዊ በመሆኑ የሥራ ውሉን አቋርጠናል በማለት ያለምንም ማስጠንቀቂያ እንዳሰናበታቸው በተለይ ለዝግጅት ክፍላችን ገልፀዋል፡፡

እንደ አቶ ተመስገን ገለፃ ከሆነ ጉዳዩ በቀጥታ ከፖለቲካ ጋር የተያያዘ እንደሆነ በመጠቆም በተለይ የገዥው ፓርቲ ባለስልጣናት ለድርጅቱ ዋና ስራ አስኪያጅና ባለቤት እንዲሁም ለም/ሥራ አስኪያጅ "አቶ ተመስገን ዘውዴ እዚህ ድርጅት ውስጥ መስራታቸው አደጋ አለው" የሚል ማስጠንቀቂያና ዛቻ ይደረግባቸው እንደነበር ለመሰናበታቸው ዋናው ምክንያት እንደሆነ አስታውሰዋል፡፡

ከባለስልጣናቱ ማስፈራሪያም በኋላ ከቢሮ እንዳይወጡ መደረጋቸውንና፣ በፓርቲያቸውና ህዝባዊ የፖለቲካ ስብሰባ ላይ እንዳይሳተፉና ከመገናኛ ብዙኃንም ጋር እንዳይገናኙ በስራ አስኪያጁ እና በም/ሥራ አስኪያጁ በኩል ጥብቅ ቁጥጥር ጫና ይደረግባቸው እንደነበር ተጠቁሟል፡፡ በአሁኑ ሰዓት ጉዳዩንም ወደ ህግ ሊወስዱት በሂደት ላይ መሆናቸውንም ለማወቅ ተችሏል፡፡

ባምቢስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ሥራ አስኪያጅ ሚስተር ከራላምቦስ ቲመስ በበኩላቸው ጉዳዩ ከፖለቲካ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት እንደሌለውና የተመደቡበት የሥራ መስክ ታጥፎ በአሁን ወቅት ድርጅቱ ስላላስፈለገው የ6 ወር ደመወዝ ካሳ እንደከፈሏቸው ገልፀውልናል፡፡ የድርጅቱ የህግ አማካሪ አቶ አለሙ ደነቀው በበኩላቸው የስራ መስኩ የማያስፈልግ በመሆኑ መታጠፉን እንደሚያውቁና ለአቶ ተመስገንም የ6 ወር ደመወዝ ካሳ እንደተከፈላቸው በመግለፅ ቀረ የሚሉት ነገር ካለ በህግ አግባብ መጠየቅ እንደሚችሉ ጠቁመዋል፡፡

# ምን መደረግ ...

ከ ገፅ 7 የዞረ.....

የአፍሪካ አገሮች ታሪክ የምንማረው በተለይም አሜሪካንን ተገን አድረገው ስልጣን ላይ የወጡ ኃይሎች ህዝቦቻቸውን ወደ ዕውነተኛው ነፃነት ሊያመሩት አልቻሉም። ከዚህ ጋር ተያይዘው የሚሄዱ የአሰራር ዘዴዎች ወይም ባህሎች እጅግ አስፈላጊ ናቸው። ስነ-ምግባርና ሞራል፣ ዲሲፕሊንና የጠበቀ አደረጃጀት ግን ደግሞ በየጊዜው የሚሻሻል፣ ታታሪነትና ህብረተሰብአዊ ኃላፊነት፣ ጥበብን የሚያስቀድም የአሰራር ስልት ለአገር ዕድገት በጣም ያመቻሉ። ይህም ማለት ለፖለቲካ ስልጣን ወይም ኃላፊነት እታገላለሁ የሚል የግዴታ በራሱ ላይ የባህል ለውጥ ለማካሄድ የሚዘጋጅና ሂስንም የሚቀበል መሆን አለበት። ተነካሁ ብሎ የሚያኮርፍ ለኃላፊነት ብቃት የለውም።

ወደ ሀብት ጥያቄ ስንመጣ የኢህአዴግ አገዛዝ አዲስ የሀብት ግኙኝነትና ክፍፍል ሁኔታ ፈጥሯል። የተወሰነው የህብረተሰብ ክፍል ብቻ ተጠቃሚ እንዲሆን በማድረግ ሰፊውን ህዝብ ከመሪቱና ከንብረቱ አፈናቅሎታል፤ እያፈናቀለውም ነው። ይህም ማለት ህጋዊ ባልሆነ መንገድ የተገኘ ሀብት በሙሉ ከተመረመር በኋላ በመንግስት ቁጥጥር ስር በመዋል ወደ ህዝብ የሚመለስበት ሁኔታ ይዘጋጃል። ከዚህም በላይ በተለይም ለውጭ ኢንቬስተሮች እየተባለ የተሰጠው የእርሻ መሬት ካለምንም ካሳ ተወርሶ ለአራሹ ህዝብ ይመለስለታል። ለህዝብ መፈናቀል ምክንያት የሆኑ ባለስልጣናትና የውጭ ኢንቬስተሮች በአካባቢው ላይ ላደረሱት ጉዳትና የህዝብ መፈናቀል ተጠያቂ ሲሆኑ፣ በተለይም ኢንቬስተሮች ካሳ እንዲከፍሉ ይገደዳሉ። እዚህ ላይ በአንዳንድ ግለሰቦችም ሆነ ድርጅቶች የሚናፈሰው እንደዚህ ዐይነቱ እርምጃ የዓለም አቀፍ ህግና ስምምነትን ይጥሳል የሚለው ትጥቅ አስፈቺ አነጋገር ቦታ የለውም። አገርህን አንተ በፈለግኸው መልክ አትገንባ የሚል ህግ የለም። በአንድ አገር ውስጥ የሚገኝ ሀብት ሆነ መሬትም ጭምር በዚያ አገር የሚኖር ህዝብ ሀብት ነው። እንደ ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት እንደዚህ ካደረጋችሁ ብድር አንሰጣችሁም የሚለው ዛቻ ቦታ የለውም። ማንኛውም ከውጭ የሚመጣ ግፊትና ጫና በኛ የተባበረ ኃይልና ዕምነት ብቻ ነው ሊፈርስ የሚችለው። በመሆኑም የእርሻ መሬት በግለሰብም ሆነ በማህበር በመደራጀት ለሚያርስ ሁሉ በይዞታ ይሰጠዋል። ገበሬው መሬቱን በስነስርዓት የማልማት መብትና ግዴታ ሲኖረው፣ የመሸጥ ወይም የመለወጥ መብት አይኖረውም። ከወላጅ ወደ ልጅ የሚተላለፍ ይሆናል ማለት ነው። የከተማ ቦታዎች ደግሞ ህብረተሰቡ እንዲኖርበት ሆነው ጥበባዊ በሆነ መልክ የሚዘጋጅበት ሁኔታ ይፈጠራል። ሰፊውን ህዝብ ወደቆሻሻ መኖሪያ ቦታ የሚገፈትር አጉል ፖሊሲ ይቆማል። ሪል ስቴትስ የሚባሉ የአገርን ዕድገትና የሰፊውን ህዝብ መብት ያላከተቱና ለተወሰነው የህበረተሰብ ክፍል ተብለው የሚሰሩ የህንፃ አሰራሮች እንዲቆሙ ይደረጋሉ። የሪል ስቴቶች መስፋፋት ልዩ ዐይነት ሰግሪጌሽንን የሚያመጣ ስለሆነ መቆም አለበት። ስለሆነም የከተማን ቦታ ሰፊው ህዝብ በግለሰብም ሆነ በማህበር በመደራጀት ከአራት ፎቅ በላይ ከፍ የማይል ቤት እንዲስራ ማንኛውም ድጋፍ ከመንግስት እንዲሰጠው ይደረጋል። ለዚህ ደግሞ በአገሪቱ ውስጥ ያለው፣ የተለያየ የዲንጋይ ዐይነት፣ ለጡብ የሚሆን አፈርና ሌሎች ማቴሪያሎች ለቤት ስራ የሚያመቹ ናቸው። በአውሮፓ ውስጥ የቤት አሰራርን ታሪክ ላጠና በአጭር ጊዜ ውስጥ ሰፊውን ህዝብ በማንቀሳቀስ ነው ከተማዎችንና አዳራሾችን እንዲሁም የመንግስት መስሪያ ቤቶችን መገንባት የተቻለው። ፍላጎትና ዲሲፕሊን ካለ የማይሰራ ነገር የለም ማለት ነው። ለከተማዎች ግንባታ የሚሆን አርኪቴክተሮችን፣ የህንፃ ስራ አዋቂዎችን፣ የከተማ ዕቅድ አውጪዎችን፣ ሶስዮሎጂስቶችንና ፈላስፋዎችን ያቀፈ ልዩ ኢንስቲቱት እንዲቋቋም ይደረጋል። ከውጭ ከጣሊያን፣ ከፖላንድ፣ ከፖርቱጋልና እነዚህን ከመሳሰሉት አገሮች አዋቂዎችና አናጢዎች በማምጣት ብዙ ትምህርትና ልምድ መቅሰም ይቻላል።

አንድን ከተማም ሆነ አገር ለመገንባት የገንዘብ ጉዳይ ወሳኝ ነው። ስለሆነም በሶስት አቅጣጫ የሚሰራ የባንክ አደረጃጀት መቋቋም አለበት። በየክፍለ ሀገሩ ርካሽ ብድር የሚሰጡ የመንግስት ባንኮች መቋቋም አለባቸው። ከዚህ በተጨማሪ ለዕድገት የሚሆንና በግለሰቦች እጅ ያለን ገንዘብ የሚያንቀሳቅስ ልዩ የዕድገትና የመልሶ መገንባት ባንክ ይቋቋማል። ከዚህም በላይ በሳንቲም የሚቆጠር ልዩ ዐይነት ፈንድ ሪይዚንግ ሲይስተም ይፈጠራል። በዚህ መልክ የሚገኘው ገንዘብ ለየክፍለ ሀገሮች እንደፍላጎታቸውና ዕድገታቸው የመገንቢያ ዕርዳታ ይሰጣቸዋል። በሁለተኛ ደረጃ፣ በግለሰብ ደረጃ የሚንቀሳቀስ የባንክ ኢንስቲቱት ይመሰረታል። የግለሰብ ባንኮች ጥብቅ የሆነ የአሰራር ህግን እንዲከተሉ መመሪያ ይወጣል። በሶስተኛ ደረጃ፣ በማህበር የተደራጀና የሚተዳደር ባንክ ይቋቋማል። የእነዚህ ሁሉ የገንዘብ ምንጭ የማዕከላዊ ባንክ ሲሆን፣ በተለይም የብደርን አሰጣጥ የሚቆጣጠር ልዩ ተቆጣጣሪ መስሪያ ቤት ይቋቋማል። በዚህ መልክ በባንክ አማካይነት ሊንቀሳቀስ የሚችል ሀብት በመፍጠር ለማኑፋክቱር ተከላና የግዴታ ለጠቅላላው የአገር ግንባታ እንዲውል ይደረጋል። በብድር የሚሰጠው ገንዘብ ወለዱ ዝቀተኛ በመሆን ከብዙ ዐመታት በኋላ የሚከፈል ይሆናል። የውጭ ገንዘብን

ወደ ገፅ 14 ይዞራል....

# ሰሙ ለአንድነት...

ከ ገፅ 1 የዞረ....

መብቶችን አስፈላጊነት፣ ኢትዮጵያ በአለም አቀፍ ደረጃ የተቀበለችቻቸውን ኮንቬንሽኖች እና ትርጓሜ ያላቸውን በዝርዝር አስረድተዋል፡፡ በተቃራኒው ሀገራችንን በተባበረቱት መንግሥታት ደረጃ የተቀበለቻቸውን የሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎች ጭምር እንደማትተገብር በምሳሌ ጭምር አብራርተዋል፡፡ በምሳሌያቸውም የፍርድ አሰጣጥ ገለልተኛ አለመሆን፣ ዜጎች ወንጀለኛ መሆናቸው ሳይረጋገጥ መታገት፣ መታሰርና የመሳሰሉትን አንስተዋል፡፡ አቶ ዳን ይርጋ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች (ነፃ ሰው፣ አካላዊ ደህንነትና ሰብአዊ ክብር) የኢኮኖሚ ማህበራዊ ባህላዊ መብቶችና የአካባቢ ደህንነትና የልማት መብት በሚሉ ሦስት ክፍሎች ዘጠኝ ዋና ዋና ርዕሶችን በውይይቱ ወቅት ዳሰዋል፡፡ ዘጠኙ ትኩረት የነበሩት የሰብዓዊ መብቶች አስፈላጊነት፣ የሰብዓዊ መብቶች መሠረታዊ ባህሪያት፣ ዓለም አቀፍ የሰዎች የመኖር ዋስትና፣ ህጋዊ መሠረት፣ ተፈጥሯዊ ክብር፣ የመንግሥት የግለሰብና የተቋማት ግዴታዎች፣ ሰብዓዊ መብቶች በማን ይፀድቃሉ፣ የሰብዓዊ መብት ሰነዶች በማን ይረቀቃሉ፣ ሰብዓዊ መብቶች በማን ጥበቃ ይደረግላቸዋል? የሚሉ ነበሩ፡፡ የለቱ ስልጠና ሰልጣኞቹ ከፍተኛ ተሳትፎ ያረጉበት ሆኖ ማለፉን የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ አቶ ደምሴ መንግሥቱ ተናግረዋል፡፡

# "ልጆችሽን ....

ከ ገፅ 9 የዞረ....

ለልጆችሽም የጭቃ ውስጥ እሾህ መሆናቸው የአደባባይ ምስጢር ስለሆነ ላንቺ አልነግርሽም፡፡

ቅር የማይልሽ ከሆነ አንድ ያልገባኝ ነገር አለና ብጠይቅሽስ? አንቺ ጋር አንዴ በኃይማኖት አንዴ በጐሳ ሌላ ጊዜ ደግሞ በፖለቲካ አሊያም በድንበር ልጆችሽ እርስ በርስ እንዲጋጩ ይደረጋል አሉ፡፡ ይገርማል፡፡ አንቺ ጋ ያለው የዘመኑ ስልጣኔ ይሄ ሆኖ አረፈ እንዴ?

ቆይማ! ብዙ ልጆችሽ በርሃብ አለንጋ እየተገረፉ ነው መባሉን ሰምቼ ከልቤ አዝኛለሁ፡፡ ያው እንደምታውቂው የእኔ ልጆች ብዛት ከ1.2 ቢሊዮን በላይ ነው፤ ያንቺ ግን ከ90 ሚሊዮን አይበልጡም፡፡ ስለዚህ ምናለ የልጆችስ "መሪ ነን" ያሉት ሁሌ ከነቤተሰቦቻቸው እየመጡ እኔ ዘንድ ከሚዝናኑ ልጆችሽ በሙሉ ለአንድ ወር እረፍት እኔ ጋር መጥተው ቢያሳልፉ፣ ቢጠግቡና ቢዝናኑ? እመኚኝ ከልቤ ነው፡፡ እባክሽ ወዳጄ ልጆችሽን በሙሉ ለአንድ ወር እረፍት ላኪያቸው፡፡

ሆዴ! ፈቃድሽ ከሆነ በጌቶችሽ የተራቡ ልጆችሽ መጥገባቸው ከሚነገር በተግባር ቢያንስ በቀን ሦስቴ ለአንድ ወር ቢመገቡ አንዋስ! ቀለብ ከእኔ ብያለሁ፡፡ መልሱንም በጉጉት እጠብቃለሁ፡፡ ያንቺው ቻይና ለምንጊዜም ወዳጄ ኢትዮጵያ፡፡

# የሰሞኑ "ቤት ለመምህራን" አዲሱ የኢህአዴግ

## የማስቀየሻ ስልት ወይስ ማካካሻ?

ይመር እንግዳ

መቼም የመኖሪያ ቤት እጥረት በሽገር ሜርኩሪ ነው ማለት ይቻላል፡፡ በመዲናችን ትንሽዬም ትሁን የአንገት ማስገቢያ ያላችው ነዋሪዎች ከሌላው በተሻለ ሁኔታ እንደሚኖሩ አያጠያይቅም፡፡ የሌለው ደግሞ ሁሌም ዕቃውን እየጫነ ቅናሽ ቤት አለበት ተብሎ የሚገመትባቸውን ሰፈሮች ሲያዳርስ ይኖራል፡፡ እንዲህ አይነቱ ዜጋ ደግሞ ለቁሳዊና ሞራላዊ ድቀት እንደተዳረገ፣ እንዳማረረና እንዳለቀሰ የሚኖር ዜጋ ነው፡፡ ስለዚህ ቤት ከህልውናችን ጋር የተያያዘ ነው ለድፍን አዲስ አበቤ፡፡

ይህንን ጠንቅቆ የሚያውቀው ብኤልዜቡል ኢህአዴግ ሁሌ ስለመኖሪያ ቤት ችግር ያወራል፤ ግን ነዋሪውን እያፈናቀለ መሬት ከመቸብቸብ በስተቀር እዚህጋ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ብሎ ለማንም ቅንጣት ቦታ አላቀመሰም፡፡ ዕድላችንና ተስፋችን "የበሬ ምንድነው ይወድቃል" ብላ ቀበሮ ስትከተል ዋለች እንደሚባለዉ ነው የሆነው፤ የመ/ሩ ነገር፡፡

የካቲት 22/2001 ዓ/ም ከአገሪቱ ከተለያዩ ክልሎች ከመጡ ተወካዮች ጋር ሲወያዩ የደሞዛቸውን ጉዳይ እንዲሁም የመኖሪያ ቤት ችግሮቻቸውን ለመፍታት መሆኑን ትኩረት ሰጥቶ እንደሚንቀሳቀስ ጠ/ሚኒስትሩ ዲስኩር አስምተው ነበር፡፡ መ/ሩም የመኖሪ ቤት ችግራችንና የደመወዛችን ሁኔታ እልባት ሊያገኝ ነው እያለ ሲፍነከነክ ከረመ፡፡ ወዲያውኑም በአ/አ በተለያዩ ት/ቤቶች የሚፈልጉትን የቤት መጠንና አቅም ፎርም እንዲሞላ የቅጽ መዐት ተበተነ፡፡ መ/ሩም "ተመስገን አዶናይ ፀሎታችንን ሰማን" እያለ ቅጹን በጥንቃቄ ሞላ፤ ምንም የለም፤ አሁንም ከቆይታ በኋላ ሌላ ቅጽ ተሞላ፡፡ አሁንም ምንም የለም፡፡ ሌላ ቅጽ ተሞላ፤ ክፍያ ከባንክ ወይስ ከራስ ቁጠባ፣ ባለሁለት፣ ባለ ሦስት፤ ባለ አንድ ክፍል ወዘተ የሚሉ መጠይቆች ያሉት ቅጽ ተሞላ፤ አሁንም ዝም፣ ጸጥ ረጭ ተባለ፡፡ ቅጾች ቤርሙዳ ውስጥ እየሰመጡ ቀሩ፡፡ መ/ሩ ግራ ተጋባ፡፡ ምንድን ነው እየተሠራ ያለው? እያለ እርስ በርሱ አጉረምርሞ ዝም አለ፡፡ በዚህ ጽሁፍ ፀሐፊ እምነት ጥያቄዎች በቂ ጊዜ ለጥናት እንደሚያስፈልጋቸው ያምናል፡፡ ነገር ግን የሚመለከተው አካል ተሸከርካሪ ወንበር ላይ ከመንጎማለል ቅጹ ምን ደረጃ እንደደረሰ ለየት/ቤቱ በደብዳቤ ማሳወቅ ይችል ነበር፡፡ በእርግጠኛነት የተሠጠው ጊዜ ግን ከበቂም በላይ ነበር ይህን መረዳት ያቃታቸው፤ ካድሬዎች ነገሩን አበላሹት፡፡

እኔ እስከአሁን የሚገርመኝ ሁለት ጓደኛሞች ሲሉ የነበሩትን እያስታወስኩ እስቃለሁ፡፡

- "ባለ ስንት ክፍል ነው ቅጹን የሞላኸው"
- "ባለ ሶስት"
- "እንዴ ከየት አምጥተህ ልትከፍል ነው ቅድመ ክፍያውን?"
- "ሁለት ደህና ወንድሞች አሉኝ፤ እነሱ ጉልበት ላይ ወድቄ ቅበሩኝ እላቸዋለሁ" ይላል
- " እኔስ የኔ ጌታ ባለ አንድ ክፍል ነው የሞላሁት፡፡ ይህችንም የማገኝ አይመስለኝም፤ እንዳው ከሚቀር ልሞክር ብዬ ነው" የተባባሉትን ሳስታውስ ... ይገርመኛል፡፡ ሁሌ ቤት፣ ቤት! ቤት!፣ቅጽ! ቅጽ! ቅጽ! እና መሙላት፣ መሙላት መሙላት፣ የሀብት ብክነት፣ የጊዜ ብክነት፤ የሰው ኃይል ብክነት አይ ኢህአዴግ መቼ ነው በቃሉ የሚገኘው? በቀን ሶስቴ ትበላላችሁ ተባልን፤ አሁን በቀን አንድ ጊዜ በመከራ፤ ዝቅተኛ ነዋሪው በቀን አንዴም ላይበላ ይችላል፡፡ ቤት በኬንያ ለመ/ራን ገና ተመርቀው (ከከፍተኛ ተቋማት) ወደ ሥራ ሲገቡ በ30 ዓመት ክፍያ የሚከፈለውን ስምምነት አድርገው ቁልፍ ተረክበው ሥራ ይጀምራሉ፤ እንዲህ ነው ከመጀመሪው ለሙያው ክብር ከተሰጠው መ/ሩም በትጋት በፍቅር በመስዋዕትነት ትውልድ ይቀርፃል ማለት ነው፤ ህልውናው ተስፋ ብቻ ስላልሆነ በተግባር ስለተረጋገጠ ወደ ዋናው ጨዋታችን ስንገባ መምህራን በተደረገው የእርከን ማሻሻያና የመንግስት ሚዲያዎች ከእውነታው የራቀ ዘገባ የተበሳጬት መ/ራን የአቋም መግለጫ በማዉጣት የስራ ማቆም እስከማድረግ ተራመዱ፡፡ ምንም እንኳ ጠ/ሚኒስትሩ እንደተናገሩት "99.9% የሆነው መ/ር በእርከን ማሻሻያው የረካ ነው ቢሉም እኔ ደግሞ ገልብጬ "99.9% የሆነው መ/ር በእርከን ማሻሻያው ያልረካነው" እላለሁ ምን ይለኛል፡፡ እሳቸውም አሉ እኔም አልኩ ማንኛችን ትክክል እንደሆንን መልሱን ለመ/ራን ትቼዋለሁ፡፡ የጉዳዩ ቀዳሚ ባለቤቶች ስለሆኑ እውነታውን ያውቁታልና እናላችሁ በዛም በዚህም ብለው የመ/ሩን የመብት ጥያቄ የተቆጣጠሩት ቢመስሉም በአመድ እንደተዳፈነ ረመጥ መምህሩ በአስፈሪ ዝምታ ውስጥ ይገኛል ጠርጣራው ኢህአዴግም ልክ የአረብ አገር አብዮት ሲቀጣጠል ድንገት ብንን ብለው " አባይን እገድባለሁ" ብለው እንዳስቀየሱት ሁሉ በነገራችን ላይ የዓባይ ግድብ / የህዳሴው ግድብ/ "ማስረሻ" እንደሚባል ሣትሠሙ አትቀሩም፡፡ መቼም ወሬ አይደበቅም ዛሬም ባሳለፍነው ሳምንት የቤት መሙያ ቅጽ በአስቸኳይ ሙሉ እየተባለ በየት/ቤቱ መምህራን በመሙላት (በመመዝገብ) ላይ ይገኛሉ፡፡ አንዳንድ ምንጮቻችን እንደገለጹልን ከሆነ "ምን ቅጽ መሙላትና መመዝገብ የተለመደ ነገር ነው እንሞላለን፤ እንሞላለን መቼ እንደሚሞላ (እንደሚሳካ) ባናውቅም ኤዲያልኝ" በማለት እያሞሉ ናቸዉ። ስሙ እንደይገለጽ የሚፈልግ መ/ር "አሁንም ስማችሁን ተመዝገቡ ተብለን እየተመዘገብን ነው። እውነት ከሆነ እጅግ ኩራት ነው፡፡ ነገ ግርን የኢህአዴግን ባህሪ ከብዙ ልምዶችና ተሞክሮዎች ስንገመግመው አይታመንም። ዛሬ የተናገረውን በነጋታው ሽምጥጥ ነው; በቃ ተወኝ እባክህ ልጆቼን ላሣድግበት"በማለት አስተያየቱን ይሠጣል፡፡

በመጨረሻም የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ ‹‹ለምን ቅጽ ይሞላል? ለምን መምህራን ለመኖሪያ ቤት ፍላጎት ይመዘገባሉ›› የሚል ጨለምተኛ አስተሳብ የለውም። ነገር ግን አንድ ሥጋት አለው። ምናልባት የሰሞኑን የመ/ራን መከፋትና አስፈሪ ዝምታ ለማረጋጋት የታሰበ ነገር ግን እውነት ያልሆነ የሚል እምነት አለው። ሆኖም ግን እንደ ከዚህ ቀደም በወረቀት የሚቀርም ይመስለኛል፡፡ የመ/ሩን ማጉረምረምና አስፈሪ ዝምታ እንደ "ማስረሻው" ግድብ ለማስቀየስስ ቢሆን? ያው እስከዚያው በጠኔ ካልሞትን ጊዜ የሚያደረገውን ማየታችን አይቀርም ወይ እውነት ሆኖ፡-

"እንጉርጉሮው ይብቃ ይገባል ውዳሴ

ጉዞውን ጀምሯል ቤቱ ግስጋሴ"

የሚል ነጠላ ዜማ ይለቃል አልያም፡፡" አመልሽ ነው አንቺ ድሮም አመልሽ፤ አደርጋለሁ እንጂ ዜሮ ነው ተግባርሽ" የሚል ነጠላ ዜማ ይለቃል ማለት ነው፡፡ ጊዜ ለኩሉ "ያህዌ ይርኤ" እግዚአብሔር ያያል፡፡

# አርበኞች የፕሬዝደንታቸውን ልመና አወገዙ

የኢትዮጵያ ጥንታዊት አርበኞች ማህበር አባላት የማህበሩ ፕሬዝደንት ሚያዚያ 27 ቀን 2004 ዓ.ም ብሔራዊ በዓል ሲከበር ያደረጉትን ንግግር አወገዙ:: አባላቱ ይህንን ያወገዙት "የማህበሩ አባላት ያልመከሩበትንና ያላመኑበትን ሚያዝያ 27 ቀን 2004 ዓ.ም በበዓል ላይ ንግግር አድርገዋል::" በማለት ነው:: እንደ አባላቱ አባባል «ማህበሩ የጀመረውን ህንፃ መጨረስ ያልቻለበትን ምክንያት ሳይወያይና ሳይመካከር መጨረስ ስለአልቻልን መንግሥት ይጨርስልን ብሎ መናገር የማህበሩ አቋም ሳይሆን የሊቀትጉኃን አስታጥቄ አቋም ነው::» ብለዋል::

አባላቱ እንደሚሉት «የማህበሩ አመራሮች በህንፃው ስም ከፍተኛ ሙስና ሲፈጽሙ ቆይተዋል:: ማንም ሳይፈቅድላቸው የማህበሩን ገንዘብ 1,581.000 ብር ለግለሰብ አበድረዋል:: አመራሩ እጅግ ከፍተኛ ገንዘብ መዝብረዋል:: ባንክ ቤቱ ግንባታውን ሳይከታተል ተገቢ ያልሆነ ገንዘብ ወጪ አድርጎ ለምዝበራ ዳርጓል:: በተለይ አማካሪው በህግ ሊጠየቁ ይገባል:: የአርበኛው ም/ቤት ኃላፊነቱን በአግባቡ እየተወጣ አይደለም:: ባልመከረበትና በማያውቀው ጉዳይና በማያውቀው የገንዘብ ወጪ በየመንገዱ ይፈርማሉ:: የም/ቤቱ ድክመት ፕሬዝደንቱና እሳቸው የሾሟቸው ግለሰቦች በማህበሩና በአርበኛው ላይ ወንጀል እንዲፈጽሙ አድርጓቸዋል:: የምክር ቤቱ አባል ያልሆኑ ግለሰቦች በም/ቤቱ ስም እየወሰኑና እየፈረሙ አስተዳደራዊ በደል እየፈፀሙ ናቸው:: ምዝበራና ወንጀል እየፈፀሙ ናቸው::» በማለት ይናገራሉ::

እነዚህ በተደጋጋሚ ዝግጅት ክፍላችን ድረስ በመመላለስ ብሶታቸውን የሚገልፁት አቅመ ደካማ አረጋውያን እንደሚሉት «መንግሥት ለአርበኛው በ20 ዓመት ተከፍሎ የሚያልቅ ግምቱ 20 ሺህ ብር የሆነ 30 ኮንዶሚኒየም ቤት ሰጠ:: አመራሩ ከተረከበ በኋላ ለአርበኛው ሳይነገር ማስታወቂያም ሳይለጠፍ ጥቂት አመራሮች ተመሳጥረው ለዘመዶቻቸው አከፋፈሉት:: ለምንድነው? ብለን ብንጠይቅ አርበኛው አቅም ስለሌለው ነው አሉን:: ይህ በእንዲህ እያለ ለአቅመ ደካማ አርበኞች በነፃ የሚኖሩበት 25 የቀበሌ ቤቶች ተሰጠን:: አሁንም በድጋሚ ማስታወቂያ ሳይወጣ አርበኛውን ሳያማክሩ ጥቂት አመራሮች ለዘመዶቻቸው አከፋፈሉት::» ሲሉ እየተፈፀመ ነው የሚሉትን አስተዳደራዊ በደል ይዘረዝራሉ::

በመቀጠልም አረጋውያን ሲናገሩ «በአንድ ወር ውስጥ ለነዳጅ እስከ ሰባት ሺ ብር ይወጣል:: ም/ፕሬዚደንቱ አይቻልም፤ ብለው ያገዱትን የም/ቤቱ አባል ያልሆኑ ዋና ፀሐፊ ተብለው የተቀመጡት ግለሰብ ወጪ አድርገዋል:: በወር 150 ብር የሚያገኘው አርበኛ በየወሩ ተገናኝቶ እንዳይነጋገር ብቻ ተብሎ ክፍያውን በሁለት ወር አንድ ጊዜ እንዲሆን አደረጉት:: የአስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት ኃላፊው የማህበሩን ቤት ኪራይ ውል ለሂሳብ ሹም እንዲያስረክቡ በአሠራር ቢየጠቁ እንቢተኛ ሆነዋል:: ፕሬዚደንቱ የሂሳብ ሹሙን ሥራ ነጥቀው ይሠራሉ:: ለሥራና ለተለያዩ ጉዳዮች ሲፈለጉ ታምሜአለሁ ይላሉ:: በየወሩ የነዳጅ ብር ልዩ ልዩ ገንዘብ ወጪ አድርገው ለመውሰድ እና ለጥፋት ሲሆን ግን ይመጣሉ:: የታሪክ አጣሪ ጉባኤ በጠቅላላ ጉባኤ ተመርጧል:: በደንቡ መሠረት የሥራ ዘመኑ የም/ቤቱ የሥራ ዘመን ነው:: ሆኖም ግን ፕሬዚደንቱ እንደግል ካምፓኒያቸው ስድስት አባላት ያሉትን የታሪክ አጣሪ ኮሚቴ በትነው የኮሚቴውን ሥራ ደርበው ይሠራሉ:: በዚህም ሙስና እየፈፀሙበት ነው:: የማህበሩ ሰነድ እንዲበላሽ ታስቦ ያልሆነ ቦታ ተከምሯል:: የአርበኛው ታሪክ እንዲወድም፤ ትልቅ የታሪክ በደል እየተፈፀመ ነው::» በማለት ይማርራሉ::

እነዚህ ጥንታዊ አርበኞች እንደሚሉት «ችግሩን ለሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር አመልክተን ሚኒስትር ዲኤታው ክቡር አቶ ረመዳን አሸናፊ ለፕሬዚደንቱ በደብዳቤ ትዕዛዝ ሰጥተው ነበር:: ሆኖም ግን ፕሬዚደንቱ በማን አለብኝነት መመሪያውን ጥሰው ዛሬም ከህግ ውጭ ያሻቸውን ያደርጋሉ:: የማህበሩን ገንዘብ ይዘርፋሉ:: ያዘርፋሉ:: አስተደደራዊ በደል ይፈጽማሉ:: ከማህበሩ ህገ ደንብ ውጪ እንደ ግል ካምፓኒያቸው የፈለጉትን ይሽራሉ፤ የፈለጉትን ይሾማሉ፣ በነፃነት ቀን በገንዘባችን የተደገሰውን ድግስ ይኸ ገብቶ ይብላ:: ይኸኛው እኔን እያጋለጠኝና እየከሰሰኝ ያለ ስለሆነ ግብር ገብቶ እንዳይበላ ብለው ከልክለዋል:: የእኔ ያሏቸውን ደግሞ እስከ ሦስት ቀን ድረስ እንዲመገቡ አድርገዋል:: የነፃነትን ቀን ለማክበር የመጡትን አርበኞች ለማሳሰር ሲያስገፈትሩ ከሥፍራው በፀጥታ አስከባሪዎች እንዲመናጨቁ አስደርገዋል:: ለአገራችን በተዋጋን፣ በደከምን፣ በቆሰልን መብታችንን፣ ገንዘባችንን ጉልበተኛ ቀምቶ መቆሚያ መቀመጫ አሳጥቶናል:: መንግሥት ጀሮውን ይስጠን:: አቤቱታችንን ይስማን፤ አስቸኳይ መፍትሔ ይሰጠን፤ እየተዘረፈ ያለው ገንዘብና ንብረት እየወደመ ያለው ታሪክ የግለሰቦች አይደለም:: የመላው ኢትዮጵያኖች ገንዘብና ንብረት ነው:: የዛሬው ትውልድ ብቻ ሳይሆን የነገውም ትውልድ ታሪክ ነው:: ጩኸታችን ይስማልን» በማለት በሐዘንና በምሬት ተናግረዋል::

# ተማሪዎች በት/ቤት የደኢሕዴን ልሳን እንዲያነቡ መደረጋቸውን ወላጆች አወገዙ

በደቡብ ክልላዊ መንግሥት በሚገኙ አንዳንድ ት/ቤቶች ውስጥ በተለያዩ የትምህርት ዓይነቶች ጣልቃ እየገቡ የደቡብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ደኢህዴን)ን ልሳን እንዲያነቡና እንዲወያዩበት መደረጉ ህገ-ወጥ ተግባር ነው ሲሉ ወላጆች ለዝግጅት ክፍላችን አስታወቁ:: ወላጆች እንደሚሉት "በአሁኑ ጊዜ በደቡብ ክልል በሚገኙ ት/ቤቶች ከ9-12 ክፍል ያሉ ተማሪዎች በደኢህዴን ልሳን እንዲወያዩ ይደረጋሉ:: ውይይቱ የትምህርቱ አካል ተደርጎ ስለሚቀርብላቸው ተማሪዎች ያለማንበብ ወይም ያለመስማት መብት የላቸውም:: እድሜውና እውቀቱ ባልፈቀደበትና ለመደበኛ ትምህርት በተላከ ተማሪ ላይ ይህንን መፈፀም ወንጀል ነው" ሲሉ ያወግዛሉ::

ወላጆች አያይዘውም ሲገልጹ «በትምህርትና በአመለካከታቸው ፈጠን ያሉ ተማሪዎችን በመመልመል ተማሪውን አንድ ለአምስት በማደራጀት የፖለቲካ አስተሳሰባቸውን ለማሸከም ይሰራሉ:: ‹ወጣት ፓርላማ› እያሉ ንጹህ የህፃናትን ጭንቅላትን ተገቢ ላልሆነ ባህርይ እየዳረጓቸው ነው:: ተገቢውን ትምህርት ከማስተማር ይልቅ እድሜ የማይፈቅድላቸውን የዘረኝነት፣ የጥላቻና የልዩነት መርዝ ይግቷቸዋል:: ልጆቻችን መደበኛ ትምህርታቸውን ትተው ተገቢ ባልሆነ ሥራ ተጠምደዋል::» ሲሉ ያማርራሉ:: በጉዳዩ ላይ የሚመለከታቸውን አካላት ሐሳብ እንዲሰጡበት ያደረግነው ጥረት ለጊዜው አልተሳካም::

# በአፈና ያልተረታው ...

ከ ገፅ 2 የዞረ....

ድርጅቶች በገበያ ላይ ከመንግስት የሚያገኙት ያልተገባ ጥቅም በንግዱ ህብረተሰብ ላይ የሚደርሰው የግብር ጫና እንዲሁም መንግስት የሚከተለው የቁጥጥር ስርዓት በህዝቡ ውስጥ ቅሬታን የፈጠሩ ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች እንደሆኑ ይታመናል:: ከዚህ በተጨማሪ በአርሶ አደሩ ዘንድ ቅሬታን የፈጠሩ ተጨማሪ ምክንያቶች አሉ ከእነዚህ መሀከል የማዳበሪያ ዋጋ መወደድ እና አርሶ አደሩ በግዳጅ ማዳበሪያ እንዲገዛ መደረጉ ያለበትንም እዳ ንብረቱን መጦ በአንድ ጊዜ እንዲከፍል መደረጉ ይጠቀሳል::

ሦስተኛው ነጥብ ማህበራዊ ቅሬታ ነው:: መንግስት በህብረተሰቡ ማህበራዊ ህይወት ላይ የሚያደርገው ቁጥጥር እና ጣልቃገብነት በህዝብ ዘንድ ቁጣን ቀስቅሶ ይስተዋላል:: በተለይም ዋንኛው ማህበራዊ ተቋም በሆኑት የእምነት ተቋማት ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ እንዲሁም ጣልቃገብነት ይጠቀሳል:: በተጨማሪም በትምህርት ተቋማትንና በተለያዩ ማህበራትን ክፍለ ፖለቲካ መሳሪያነት መጠቀሙ ያመጣቸው የመብት ጥሰቶች ይጠቀሳሉ::

እነዚህ ቅሬታዎች ወደ አብዮት ሊያንደረድሩ የሚችሉ ይታመናል:: ከእነዚህ ቅሬታዎች መካከል በሊዝ የከተማ ቦታዎችን ለመያዝ አዋጅ 721/2004 የዜጐችን የንብረት ማፍራት እንዲሁም ባፈሩት ንብረት የመጠቀም መብታቸውን ማሳጣቱ፤ የተባባሰውን የኑሮ ውድነት ተከትሎ መምህራን ላነሱት የደመወዝ ጭማሪ ጥያቄ መንግስት የሰጠው አሳፋሪ ምላሽ እና ይህን ተከትሎ መምህራን ባደረጉት የስራ ማቆም አድማ ለማስቆም የተወሰደው እርምጃ እና በሃይማኖት ተቋማት ላይ የሚያደርጋቸው ጣልቃ ገብነቶች የፈጠረው ቅሬታ ወደ ተካረረ ነጥብ ወሰደውታል::

# ሚዛን ተፈሪ ግብርና ኮሌጅ ...

ከ ገፅ 1 የዞረ....

ወንበሮች የሉም:: በግዢ ላይ ከፍተኛ ሙስና ይፈፀማል:: በአንደኛ ደረጃ ምርት ዋጋ ጥራቱ የወረደ ምርት ይገዛል:: ሂሳብ የሚወራረደው በአንደኛ ደረጃ ዋጋ ነው:: የሚገዙት እቃዎች ጥራት የሌላቸውና አገልግሎት የማይሰጡ በመሆናቸው በግምጃ ቤት ተከምረው ይገኛሉ:: የቧንቧ እቃዎች፣ የኤሌትሪክ እቃዎች ማየት ይቻላል:: ጥራት የሌላው የሠራተኛ ደንብ ልብስ ይገዛል:: "ለምንድነው?" ሲባል "ከለበስክ ልበስ ካለበስክ ምን አባክ ታመጣለህ?" ይባላል:: በማለት በምሬት ይናገራሉ::

ሠራተኞቹ በመቀጠልም «ኮሌጁ ውስጥ ከፍተኛ የሆነ አስተዳደራዊ ሙስና ይፈፀማል:: ለይስሙላ የሠራተኛ ቅጥር ኮሚቴ ቢዋቀርም፤ የማስመሰያ ማስታወቂያ ቢወጣም፤ የሠራተኛ ቅጥር የሚፈፀመው በሙስና ነው:: ችሎታ ያለው ተወዳዳሪ ወድቆ መስፈርቱን የማያሟላ ሠራተኛ ይቀጠራል:: ደንብን ያልተከተለ የሠራተኛ እድገት ይሰጣል:: 6 እና 7 ዓመት የሠራ ሠራተኛ እያለ አዲስ ተቀጥሮ የሙከራ ጊዜውን ያልጨረሰ ሠራተኛ እድገት ይሰጣል:: እንዲያውም አንድ ሠራተኛ በወራት ልዩነት ሁለት ጊዜና ሦስት ጊዜ የደረጃ እድገት እንዲያገኝ ይደረጋል:: ጉዳዩን ስናጣራ በጥቅማ ጥቅም የተሳሳሩ ሆነው አግኝተነዋል:: ነባር ሠራተኞች ተከልክለው» አንድ የሙከራ ጊዜውን ያልጨረሰ ሠራተኛ በተከታታይ አራት ጊዜ የትምህርት እድል እንዲያገኝ ተደርጓል ይላሉ::

በማያያዝም ሲናገሩ «በኮሌጁ ውስጥ ምዝበራ የሚደረግበት መስክ አንዱ በተሽከርካሪ ጥገና ነው:: ተሽከርካሪዎችን ሚዛን ተፈሪ ወይም በአካባቢው ከተሞች ካልተቻለም አዲስ አበባ በጥራት ማስጠገን ሲገባ፤ አዋሳ ድረስ እየተወሰደ ተጠገነ ተብሎ ይመለሳል:: ከፍተኛ ወጪ ወጥቶ የተጠገነው ተሽከርካሪ ወዲያውኑ ይበላሻል:: እንደገና ወደ አዋሳ ይላካል:: በዚህ መንገድ የመንግሥት ገንዘብ እየተመዘበረ ነው:: ከመጠን በላይ ነዳጅ ወጭ ይደረጋል:: በመንግሥት መኪና ነዳጅ የግላቸውን ቤት ይሠራሉ:: አሸዋ ሲሚንቶ፣ እንጨት ያመላልሳሉ:: ገንዘብ እየተቀበሉ የግለሰብን እቃ እየጫኑ በመንግሥት መኪናና ነዳጅ ይነግዳሉ:: ገንዘቡ ወደ ግለሰብ ኪስ ይገባል:: በአሁኑ ወቅትም ሁለት መኪናዎች አዋሳ ይገኛሉ:: ብለዋል::

በኮሌጁ ውስጥ ረጂም አገልግሎት ሰጥተናል የሚሉት እነዚህ ሠራተኞች «በኮሌጁ ካሪኩለም መሠረት 30% ቲዎሪ 70% የተግባር ትምህርት ይሰጣል ቢባልም በአሁኑ ጊዜ በኮሌጁ ውስጥ እየተሰጠ ያለው 70 ፐርሰንት ቲዮሪ ነው:: ለመማር ማስተማር አገልግሎት የሚውል የማስተማሪያ እቃ እንዲገዛ ሲጠየቅ ውድቅ ያደርጉትል:: በጀት በተፈቀደ ቁጥር የሚገዙት ከፍተኛ ገንዘብ የሚያኙበትን እቃ ነው:: ለኮሌጁ ኮንፒውተር፣ ላፕቶፕ እንደሚያስፈልግ እናውቃለን:: ቅድሚያ የሚሰጠው እንደ መጽሐፍ ያለ እሱን ትተው ኮንፒውተር ካቅም በላይ ይገዛሉ:: እቀውን ሲገዙ ከመምህራን ወይም ገለልተኛ ሰው አይላክም:: የሚልኩት ሁል ጊዜ ከአመራሩ ጋር በጥቅም የተሳሰረ ሰው ነው:: በዚህ ምክንያት ባለፈው ህዳር የተቀጠሩ አራት ሠራተኞች ሥራቸውን ለቀዋል:: የኮሌጁ ኃላፊዎች በግላቸው በከፍተኛ ሁኔታ በሙስና እንጠረጥራቸዋለን:: በደሞዛቸው ገቢ ሊሠሩት የማይችሉትን ቤቶች ገንብተዋል:: በራሳቸው፣ በሚስቶቻቸው በዘመዶቻቸውና በአማቾቻቸው ስም በተለያዩ ከተማዎች ገንብተዋል:: ለዚህም በቂ ማስረጃ ሰብስበናል" በማለት ይዘረዝራሉ::

የኮሌጁ ኃላፊዎች አለአግባብ የመንግሥትን ንብረት ተጠቅመዋል በማለት በማስረጃ ሲያስረዱ «የኮሌጁ ኃላፊ አቶ ብዙአየሁ ገረመው ‹በሦስት ወር ውስጥ የሚመለስ› ብለው ከኮለጁ 7 ኩንታል ሲሚንቶ ከወሰዱ በኋላ፤ ሦስት ወር ሲሞላ መመለሳቸውን ትተው፤ አስፈርሞ የሰጣቸውን ሠራተኛ በአቀማመጥ ስለተበላሸ ከኃይል እንዲቀነስልኝ ብሎ በደብዳቤ እንዲጠይቅ አደረጉ:: የሙስና ተባባሪዎቻቸውን ኮሚቴ አዋቅረው ስለተበላሸ እንዲቃጠል ብለው የውሳኔ ሃሳብ አስቀረቡ:: በመቀጠልም እሳቸው እንዲቃጠል ወስነው ከኃይል እንዲቀነስ አደረጉ» በማለት ማስረጃዎቹን ያሳያሉ::

« የኮሌጁ እቃዎች በሥርዓት በሠነድ ተመዝግበው የማይያዙ ከመሆኑም በላይ ወጪም ሲደረግ ህግን የተከተሉ አይደሉም:: የሚንቀሳቀሰው ገንዘብ ጣራ መወሰን ሲገባው በኮሌጁ ውስጥ ገንዘብ ያለ ገደብ በገንዘብ ያዥ ስም ይንቀሳቀሳል:: በዚህም ምክንያት የመንግሥት ገንዘብ ለከፍተኛ ምዝበራ ተጋልጧል:: ለተለያዩ መ/ቤትና ለኮሌጁ ኃላፊዎችና ለወንጀል ተባባሪዎቻቸው ንብረቶችን በውሰት ከሰጡ በኋላ አይመልሱም:: ወደ ኮሌጁ ተልኳል የሚባለው ገንዘብና ገቢ የሆነው አይመጣጠንም:: ኃላፊዎቹ የተሰማሩት በምዝበራና በወንጀል ላይ ስለሆነ የኮሌጁ ማህበረሰብ ተሰባስቦ እንዳይነገር ይፈልጋሉ:: በዚህ ምክንያት በምንም ዓይነት የኮሌጁን ሠራተኞች ሰብስበው ማነጋገር አይፈልጉም:: ሠራተኛውን ስለሥራ ጉዳይ ከሰበሰቡትም የሙስና ስራቸው የሚነሳ እየመሰላቸው የኮሌጁን ማህበረሰብ በአንድ ላይ ተሰብስቦ ማየት አይፈልጉም:: ኮሌጁ ለዘጠኝ ዓመት ኦዲተር አያውቀውም:: ጥቆማ የሰጠናቸው የዞኑ መስተዳድር ፖለቲካ ኃላፊና የፌዴራል ሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ም/ኮሚሽነር የሰጠናቸውን መረጃ ለኮሌጁ ኃላፊዎች አሳልፈው በመስጠት ለአደጋ አጋልጠውናል::" በማለት በቅሬታ ይገልፃሉ:: «ከዚህ በፊት ሙስናን ያጋለጠ አንድ የከተማችን ነዋሪ ሙሰኛ የሥራ ኃላፊዎች አቀነባብረው ወደ በረሃ ለሥራ እንዲሄድ ካደረጉ በኁላ አስገድለውታል:: እኛም መንግሥትንና ህዝብን ተማምነን እየታገልናቸው ነው:: ጩኸታችንን ለመንግሥት አሰሙልን» በማለት ተናግረዋል::

የኮሌጁን አቶ ብዙአየሁ ገረመው በጉዳዩ ላይ ሃሳብ እንዲሰጡበት በተደጋጋሚ በስልክ አነጋግረናቸዋል:: አቶ ብዙአየሁ የቀረበውን ጥቆማ "ውሸትና የተቀነባበረ ፈጠራ ነው" ካሉ በኋላ የማስተባበያ ማስረጃቸውን ይዘው አዲስ አበባ እንደሚመጡ ነግረውን ነበር:: ከመጡም በኋላ ሳንገናኝ ተመልሰው ሄደዋል:: ዜናው ከተሰራ በኋላ እንደአስፈላጊነቱ ማስተባበያውን እንደሚሰጡ በስልክ ነግረውናል::

## የአቶ መለስ ሦስት ...

ከ ገፅ 8 የዞረ.....

የለም፡፡ ደርግን የሚያህል አስፈሪና "ሰው በላ" መንግስት የአደባባ ህፀፁን በብዕር መንቀፍ ውጤቱ ሞት ነው፤ ያውም በአደባባይ መረሸን (አብዮታዊ እርምጃ! ኦሮማይ!) በመንቀፉ እሱም የሞትን ፅዋ ተጎንጭቷል (ኦሮማይ)

የበዓሉ ግርማ የብዕር ትሩፋቶች ዘመን ተሻጋሪ እንደሆኑ አያሌ ምሁራን ይመሰክራሉ፡፡ በኢትዮጵያ የስነ ጽሁፍ ታሪክ ውስጥ ታላቅ ለውጥ ያመጣ በአፃፃፉ ቴክኒክና በአቀራረቡ ወደር ያልተገኘለት ደራሲ ነበር፡፡ መንግስቱ ኃ/ማርያም እንኳን በብርቱ ያደንቁት እንደነበር ተናግረዋል፡፡ ነፍሱን ይማረውና ደራሲ ስብሃት ገ/እግዚአብሄርም መንግስቱ ኃ/ማርያም እንዳላስገደሉት በእርግጠኝነት ተናግሯል፡፡

በዓሉን ኦሮማይ የሬሳ ሳጥኑ ሆነ፤ መሞቻውና መቀበሪያው፤ በጦር መሣሪያ ለመድፈር የሚያስፈራውን ደርግ በብዕሩ ደፈረ፡፡ እንግሊዛዊው ደራሲ ጆርጅ አርዌል "Animal farm" በተሰኘው ዘመን በማይሽረው ልቦለድ ድርሰቱ ገሀድ ያወጣውን የነስታሊንን ገመና አካሄድ ተከትሎ ከኮሎኔል መንግስቱ ጀምሮ እስከ ዝቅተኛ ሹማምንት ድረስ በገፀ ባህሪነት የሳለበት ኦሮማይ በህወሓት በተለይም በሻዕቢያ ዘንድ ፍፁም አይወደድም፡፡ የእነሱም ገመና ተዳሷልና፡፡ በጦርነት ወቅት በጦር ሜዳ የዋሉ ከፍተኛ ማዕረግ የነበራቸው መኮንኖች ስለ በዓሉ ግርማ ድፍረት የሚናገሩት በአግራሞት ነው፡፡ በዓሉ ጥይት በጆሮ ግንዱ ስር እያለፈ ከወታደሩ ጋር የቀበሮ ጉድጓድ ወስጥ ሆኖ ሀቁን ይዘግብ እንደነበር ይመሰክሩለታል፡፡

ዛሬም ቢሆን ጋዜጠኞች የአቶ መለስ ብርቱ ስጋቶች ናቸው፡፡ ለእሳቸው የአንድ ጋዜጠኛ ፅሁፍ የኔቶ ሠራዊት በጋዳፊ ጦር ላይ ካዘነባቸው አደገኛ ቦምቦች በላይ ይገዘፉባቸዋል፡፡ የኔቶ ቦምብ የደረመሰው የድንጋይ ክምርና ተራውን ወታደር ሲሆን ጋዜጠኛው ብዕር ግን የሚያዘንበው የቃላት ናዳ በአቶ መለስና በሚመሩት ሥርዓት ላይ ያነጣጠረ ነው፡፡ የእሳቸው ኢህአዴግ የሚፈፅመውን ህፀፅ ጋዜጠኞች ፈልፍለው ለህዝብ ጆሮ ባደረሱ ቁጥር ቁጣቸው ያይላል፡፡ የሀገር ውስጥም ሆኑ የውጭ ጋዜጠኞች በኢህአዴግ ዘንድ ቀንደኛ ጠላቶች ናቸው፤ የኢቴቪ፣ የኤፍ ኤም ሬዲዮ እና የአዲስ ዘመን ጋዜጠኞች ካልሆኑ በቀር፡፡ እነዚያ አሸባሪዎች እነዚህ ደግሞ ልማታዊ ጋዜጠኞች እውነትን መናገር ሽብር ቅጥፈትን መደስኮር ግን ልማት የሆነባት አገር የዛሬይቱ ኢትዮጵያ በዓለማችን ላይ ጋዜጠኞች ለሞት፣ ለእስራትና ለስደት ከሚዳርጉባቸው አገራት መካከል ኢትዮጵያና ኤርትራ በቁንጮነት ይጠቀሳሉ፡፡ ከሁለት አመታት በፊት አዲስ ነገር ጋዜጣ ተዘግታ እነ መስፍን ነጋሽ ከአገር ተሰደዱ፣ በቅርቡ የአውራምባ ታይምሱ ዳዊት ከበደ በኢህአዴግ ወከባ ወደ አሜሪካ ተሸኝቷል፡፡ ሰሞኑን ደግሞ የፍትህ ዋና አዘጋጅ በስበብ አስባቡ ፍርድ ቤት እየቀረበ ነው፡፡ ፍኖተ ነጻነት ጋዜጣም ገና የአንድ ዓመት ልደቷን ሣታከብር ሳንካ እንደገጠማት ባለፈው እትም ላይ አንብበናል፡፡

በአሁኑ ወቅት ከፀረ ሽብር ህጉ የተነሣ ኢትዮጵያ ውስጥ እውነትን አንጥረው የሚዘግቡ ጋዜጠኞችና ጋዜጣዎች ህልውና አደጋ ላይ ወድቀዋል፡፡ ዛሬ በቃሊቲው ማጎሪያ ብዙ ጋዜጠኞች በእስር ላይ ናቸው፡፡ ግማሹም ተፈርዶባቸው ሌሎቹ ፍርዳቸውን እየጠበቁ አገር ወዳዱና ታዋቂው ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ሀቅን በብዕሩ በማንጠቡ ዘብጥያ ከተወረወረ ወራቶች ተቆጠሩ፡፡ የአቶ መለስ መንግስት በአሸባሪነት ሲፈርጀው "pen International" የተሰኘው የጋዜጠኞችን ተግባር የሚዘክረው ዓለም አቀፍ ድርጅቶች የ2012 ተሸላሚ አድርጎ መረጠው፡፡

በ2004 ዓ.ም ድንበር የለሽ የጋዜጠኞች ቡድን በቱሪስት መልክ ወደ አገር ውስጥ ገብቶ በደቡብ ህዝቦች ክልል በተለይም በከምባታና ሀዲያ ዞኖች የእርዳታ እህል ለኢህአዴግ የፖለቲካ ቅስቀሳ መዋሉን በሚስጥር በመዘገብ ለአለም ህዝብ ማሳወቁን ሰምተናል፡፡ ይህን ተከትሎ ኢህአዴግ ሁኔታውን ለማስተባበል ያልፈነቀለው ድንጋይ አልነበረም፡፡ አልፎ ተርፎ በተከታታይ ሚዲያዎች ሲያወግዝ ነበር፡፡ የአሥራ አንድ ዓመት እስራት የተፈረደባቸውም የስዊድን ጋዜጠኞች ከአቶ መለስ ፍርሃት በመነጨ ለሌሎች መቀጣጫ እንዲሆኑ ነው፡፡ መቼም በአገራቸው የተቀማጠለ ኑሮ የሚኖሩና ተርፏቸው እኛን ስንዴ የሚታደጉን ስዊድኖች አድፍጦ ጥይት ከመተኮስ የዘለለ አቅምም ሆነ አለም አቀፍ እውቀትና ለሌላው ኦብነግ ቅጥረኛ ሆነው ይመጣሉ ብሎ የሚያምን ይኖራል ብዬ አልገምትም፡፡

እርግጥ ነው ኢ-ዴሞክራሲያዊ ስርዓትን በሚያቀነቅኑ መሪዎች ዘንድ ጋዜጠኞች ብርቱ ፍርሃትን ይፈጥራሉ፡፡ በየዕለቱ መሪዎችና መንግስታቸው በዜጎች ላይ የሚጭኑትን የጭቆና ቀንበርና የሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብት ጥሰት በማጋለጥ በህዝብ ዘንድ እንዲጠሉና አመኔታን እንዲያጡ ስለሚያደርጋቸው ፍርሀታቸው ትክክል ነው፡፡ "ምን ያለበት ዝላይ አይችልም" እንዲሉ

መቼም የአቶ መለስ መንግሥት ጠቅልሎ የያዛቸው ብዙሃን መገናኛዎች የኢህአዴግን ቅድስና እንጂ እንከኑን አያወሩም፡፡ በአሁኑ ወቅት በመላ አገሪቱ ሥር እየሰደደ የመጣ የብሄረሰብ ግጭት በየአቅጣጫው ይስተዋላል፡፡ በቢሊዮን ዶላር የሚገመት የአገሪቱ ሀብት በየጊዜው በጥቂት ሹመኞችና ስግብግብ ነጋዴዎች እየተመዘበረ ከሀገር ይወጣል፡፡ የህዝብ ንብረት በጠራራ ፀሐይ ይዘረፋል፡፡ የኑሮ ውድነቱ የህዝቡን ጉሮሮ ሰንጎታል፡፡ ጠቅላይ ሚ/ሩም እስከዛሬ አምነው የሽንፈት ቃል ተናግረው አያውቁም ነበር፡፡ በሚያዝያ 9/2004 የፓርላማ ማርፈጃቸው ግን የመንግስታቸው አንድ እጅ በኪራይ ሰብሳቢዎች በመታሰሩ ሽባ እንደሆኑ አመኑ፡፡ ትግሉ መራራ ከመሆኑ የተነሳ "ወይ ኪራይ ሰብሳቢዎች ወይም ልማታዊነት ያሸንፋል" ሲሉ በተስፋ መቁረጥ ተናገሩ፡፡ በሊዝ ፖሊሲውም ዙሪያ "እንደ እንዝርት አሽከረከሩን፣ አጦዙን . . ." በማለት ያጋጠማቸውን እጅግ ፈታኝ መሰናክል ለኢትዮጵያ ህዝብ አሰሙ፡፡ ባለፈው ሰሞን ደግሞ በኦሮሚያ አርሲ ዞን ገደብ አሳሳ ወረዳ ውስጥ ከእምነት ጋር በተያያዘ የተከሰተውን አሳሳቢ ግጭትና ግጭቱ ያስከተለውን ውጤት፣ እንዲሁም በጋምቤላ አካባቢ ለውጭ ባለሀብቶች በሊዝ በተሸጠ የእርሻ ሥራ ላይ በተሰማሩ የውጭ አገርና ኢትዮጵያውያን ዜጎች ላይ የተፈፀመውን ግድያ የኢህአዴ ብዙሃን መገናኛዎች መዘገባቸው የሚያመላክተው በአሁኑ ወቅት አንድን ክስተት በምስጢር መያዝ በማይችልበት ደረጃ መድረሳችንን ነው፡፡ ችግሮች እየተባባሱ በመምጣታቸው ሚዛን የደፉትን እንስማ እንጂ በመላ አገሪቱ በተለይም በገጠሩ አካባቢ የሚከሰቱትን አይደለም ገለልተኛ ጋዜጠኞች የኢህአዴግ ሚዲያዎችም እንዲሰሙትና እንዲዘግቡት አይፈቅድም፡፡ የየክልሉ ባለሥልጣናት ጉዳዩን ይደብቁታል፤ የችግሮቹም ፈጣሪዎች እነሱ ናቸውና፡፡

ዛሬ ለአቶ መለስና ለመንግስታቸው ቪኦኤና የጀርመኑ ዶቼቤሌ ሬዲዮ ጋዜጠኞች ብርቱ ፍርሃት ናቸው፡፡ ጣቢያዎቹን ለማፈን (ጃም ለማድረግ) ከፍተኛ የአገር ገንዘብ ዛሬም ይፈሳል፡፡ ከአሜሪካን መንግስት ጋርም በጉዳዩ ላይ ለመደራደር የተሞከረው ከ ፍርሃት በመነጨ ነው፡፡ ግና ምን ያደርጋል፤ አንድ ቀን "የፈሩት ይወርሳል" እንዲሉ መሆን የሚገባው መሆኑ የግድ ይላል፡፡ ከዚህ ሁሉ ግን ራስን በህዝብ መስታወት መመልከትና አካሄድን ማስተካከል፡፡ አሊያም እንደ ጀግናው አጼ ቴዎድሮስ የክብር ሞትን መድፈር ቢያዳግትም እንደ አንዳንድ አስተዋይ መሪዎች ስልጣን ለህዝብ ለማስከበር መድፈር በ21ኛው ክ/ዘመን ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያችን የሚዘከር አኩሪ ተግባር ይሆናል የሚል እምነት አለኝ፡፡

የኢትዮጵያ አምላክ የሳምንት ሰው ይበለን !

## የኢትዮጵያ መምህራን ...

ከ ገፅ 6 የዞረ.....

የመምህራንን ፍላጎት አርክቶ ግን አያውቅም፡፡ ሽንገላ ፊትም ነበር አሁንም አለ። አፈናው የነበረና አሁንም ያለ ነው፡፡ በእኔ እድሜ ያየኋቸው ሦስቱም የመንግሥት ሥርአቶች (የንጉሡ፤ የደርግና የኢህአዲግ) መምህራን በነጻ ተደራጅተው መብታቸውን የማስከበር አቅም እንዲኖራቸው አይፈልጉም፡፡ እዚህ ግባ የማይባል የተሽመደመደ ማህበር እንዲኖር ግን መምህራን ሳይሆኑ ገዢዎቹ ይበልጥ ይፈልጉታል፡፡ አሁን ኢህአዲግ እያደረገ እንዳለው አንድም ለአናሳ ብሶቶች ማስተንፈሻ፤ አመራሩን በአሽንጉሊቶቻቸው አስይዘው ለመንግሥት ጉዳይ ተላላኪና መምህራንን እርስ በርሳቸው እንዲጠባበቁ ለማድረግ ስለሚጠቅማቸው፤ ሌላውም በዓለም አቀፉ ሕበረተሰብ በተለይም በተባበሩት መንግሥታት ዘንድ መንግስታቸውን ዲሞክራትና የሦስትዮሽ (መንግሥት፤ አሠሪ፤ ሠራተኛ) ሲቪል ጥምረት ባህሪይ ያለውና ብዙሀንን የሚአሳትፍ፤ ሀገሪቱ ተቀብላ የፈረመቻቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና ቃል ኪዳኖች ለማክበርና ለመተግበር መንግሥታቸው አቅምና ፍላጎት ያለው እንዲአስመስልላቸው ነው፡፡

ሙያተኞች ተደጋግሞ እንደተነገረው ከጊዜው ጋር ሲመዘን የንጉሡ የተሻለ ነበር፡፡ በደርግ ዘመን መታመም የጀመረው የመማር ማስተማር ሥራ በኢህአዲግ ብሶበት እያጣጣረ ነው፡፡ ሊሞት የሚአጣጥርን ህመምተኛ ሀኪም በቀጠሮ አያቆየውም፡፡ አስቸኳይ እርዳታ ያደርግለታል እንጂ የኢትዮጵያን ትምህርት ለመታደግ የዚህን ያክል አጣዳፊ እርምጃ ሊወሰድ ይገባዋል፡፡ ለዚህም የመምህራን ሕይወት መለወጥ አንዱና ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ትልቁ ጉዳይ ነው፡፡ መምህራንም በተናጠል ሳይሆን አንድ ላይ መቆም ለነገ የማይባል የህልውና ጉዳይ መሆኑን ላፍታም መዘንጋት የለባቸውም፡፡ መብትን ታግሎ እንጂ ተለማምጦ ወይም በሌላው መስዋእትነት ለማግኘት ማድፈጥ ትርፉ መናቅና ውርደት ነው፡፡ የትም አያደርስም፡፡ ባለስልጣኖቻችን ጠ/ሚኒስቴር መለስን ጨምሮ ቁጣና ዘለፋ የሚቀናቸው ደካማን ከመደራደር ይልቅ በማስፈራራት ጭጭ ማሰኘት እንደሚቀል ስለሚአውቁት ነው፡፡ ለመደራረደር ጠንክሮ መገኘት የግድ ነው፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ በመንግሥት በኩል የመምህራንን ጥያቄና ሕይወታቸውን በንጹህ ህሊና አመዛዝኖ ተገቢ መልስ ቢሰጣቸው ይሄን አሳሳቢ የትምህርት ሥራ ችግር ለመፍታት የመሠረት ድንጋይ እንዳኖረ ቆጥሮ

<u>ሠንጠረዥ 3</u>፡- የሰሞኑ (ከፋሲ በኋላ) የምግብ ምርቶች አማካኝ ዋጋ በአዲስ አበባ ከተማ

| ተ.ቁ. | የምግብ ምርቱ ዓይነት | መጠኑና መለኪያው | ዋጋው በብር | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ንፁህ ስንዴ | 100 ኪሎ | 900-1000 | በቀበሌ የሚሸጠው 450 |
| 2 | ጥራት ያለው በቆሎ | 100 ኪሎ | 700 | እንቅጥቃጭ ያለው 650 |
| 3 | ገብስ | 100 ኪሎ | 950-1000 | |
| 4 | ጥቁር ጤፍ | 100 ኪሎ | 980-1080 | ማኛ ነጭ ጤፍ 1500 |
| 5 | ሽሮ | 1 ኪሎ | 24 | |
| 6 | በርበሬ ከነዛላው | 1 ፈረሱላ (17 ኪሎ) | 900 | 1 ኪሎ የተፈጨ 80 |
| 7 | ሽንኩርት | 1 ኪሎ | 10 | |
| 8 | ስኳር | 1 ኪሎ | 14.50 | |
| 9 | የምግብ ዘይት | 1 ሊትር | 50 | የውጭ ሀገር 62 |
| 10 | ቅቤ የሸኖ | 1 ኪሎ | 180 | ጥራቱ መለስተኛ 170 |
| 12 | ለሥጋ ተመራጭ ዶሮ | ብዛት 1 | 150-180 | የአልፎራ ዶሮ ይቀንሳል |
| 13 | ዕንቁላል | ብዛት 1 | 2.50 | |
| 14 | የከብት ሥጋ ለወጥ | 1 ኪሎ | 85-100 | የቁርጥና ክትፎ 110-120 |

<u>ማሳሰቢያ</u>፡- ክልሉ አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ቢሆንም በማህል ከተማና በዳር ዳር በሚካሄዱ ግብይቶች የሱቅ ኪራይ ልዩነት፤ የተጠቃሚው ሰው ስብጥር አቅም፤ የገበያው ወይም የሱቁ ምቹ ቦታ ላይ መሆንና አለመሆን የመሳሰሉት ለመለስተኛ የዋጋ መለያየት ምክነያት እንደሚሆኑ አንባቢ ልብ ሊለው ይገባል፡፡

ለትምህርት ጉዳይ ከሚሰጠው ትኩረት በመነጨ በተለይ ጥራትን በሚመለከት በህሊናቸው በሚዳኙ ሊበረታታ ይገባዋል እንጂ እንደ ሽንፈት ወይም ድፍረት ቆጥሮት እልህ ውስጥ መግባት ፈጽሞ የለበትም፡፡ ሕዝብም ባገኘው መድረክ ሁሉ ለዚህ ተፈጻሚነት ያላሰለሰ ግፊት ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ ለችግሩ በዋንኛነት ቅድሚያ ተጠያቂው መንግሥት ቢሆንም ሁሉም ዜጋ በማስተማር ሙያ የመገልገል ባለመብት የመሆኑን ያክል ሙያው ለሚደርስበት ችግር የተጠያቂነት ግዴታ እንዳለበት ሊገነዘብ ይገባል፡፡ ዝምታ ለበግም አልበጃት፡፡

## ምን መደረግ ...

ከ ገፅ 12 የዞረ.....

በሚመለከት የግዴታ የውጭ ምንዛሪ በመግንስት ቁጥጥር ስር ይውላል፤ ወይንም እንደ አስፋላጊነቱ ማዕከላዊ ባንኩ ለማሽንና ለዕድገት የሚያገለግሉ ኢንዱስትሪዎችንና የጥሬ ሀብቶችን ለማስመጣት ለአስመጪዎች ያከፋፍላል። ግለሰቦች የውጭ ገንዘብ ወደ ውጭ እንዳያወጡ ጥብቅ ቁጥጥር ይደረግባቸዋል። ማንኛውም የጥቁር ገበያና የአየር ባየር ንግድ እንዲሁም ደላላነት በህግ ይከለከላሉ። ከዚህ በተረፈ ለሞራል ብልሹ የሚሆኑ የመጠጥ ዐይነቶችና፣ ቅጥ ያጣ ከአገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገት ጋር የማይጓዝ የፍጆታ ዕቃ እንዳይገባ ይታገዳል፤ ወይም በመቶ ፐርሰንት ይቀረጣል። በተጨማሪም በአገር ቤት ውስጥ የሚመረቱ ተመሳሳይ ምርቶች ከውጭ በገፍ እንዳይገቡ ገደብ ይደረግባቸዋል፣ ወይም ከፍተኛ ቀረጥ ይጫንባቸዋል። ከዚህ በተረፈ ከውጭ የሚመጡ ሰከንድ ሃንድ ዕቃዎች በጥብቅ የሚከለከሉና እንደ መኪና የመሳሰሉት ደግሞ የተወሰነ ስታንደርድን ያሟሉ መሆን አለባቸው። የአገሪቱን የትራንስፖርቴሽን ችግር ለመፍታት ከፍተኛ ቦታዎች ባሉበት ቦታ በአየር ላይ የሚንቀሳቀስ ቀላል ባቡር ማስገባት፣ በዚህ ዕውቀት ካላቸው እንደ ስዊዘርላንድና አውስትሪያ ጋር ልዩ ስምምነት ማድረግ። በረባዳ ቦታዎች ደግሞ በኤሌክትሪክ ኃይል የሚንቀሳቀስ ስትሪት ካር እንዲስፋፉ ማድረግ። በዚህ መልክ የመኪናን መግባት በመቀነስ በከተማዎች ያለውንም የትራፊክ አደጋና የመንገድ ጥበት መቋቋም ይቻላል።

የአንድ አገር ኢኮኖሚ ፖሊሲው የመጀመሪያው ዓለማ የአገርን ሀብትና የሰው ኃይል በማንቀሳቀስ ድህነትን ማሰወገድ ነው። በብዙ የምዕራብ አውሮፓ አገሮች ከሁለተኛ ዓለም ጦርነት በፊትም ሆነ በኋላ ተግባራዊ የሆነው የኢኮኖሚ ፖሊሲ ኒዎ-ሊበራሊዝም ሳይሆን በዕውቅ ላይ የተመሰረተ የኢኮኖሚ ግንባታ ነው። ጀርመን ሁለት ሶስተኛው የሚሆነው ኢኮኖሚዋና ንብረቷ በጦርነቱ ምክንያት ከወደመና ከፈራረሰ በኋላ ከአስራ አምስት እስከ ሃያ ዐመት ባለው ጊዜ ውስጥ መልሳ የገነባችው በተዓምር ሳይሆን በመደራጀት፣ በዲሲፐሊንና በፍላጎት በመመራት ነው። እነዚህን መመሪያዎች ያላደረገ በፍጹም ጤናማና ጠንካራ አገር ሊገነባ አይችልም ማለት ነው። ይህ ማለት ምን ማለት ነው። የኢትዮጵያን ዕድገትና ስልጣኔ ከዛሬው አገዛዝ ባሻገር ማየት አለብን ማለት ነው። በምርጫ ተወዳድሬ ስልጣን ይዤ አገር እገነባለሁ ማለት ለአገዛዙ በጭቆናህ ግፋበት እንደማለት ይቆጠራል። የኢትዮጵያ ህዝብና አገር ወዳዱ ኃይል ለኢህአዴግ ህገ-መንግስት የሚዋደቅ ሳይሆን በህገ-መንግስቱ መቃብር ላይ አዲስ ህገ-መንግስት በመፍጠር ወደ አገር ግንባታ የሚሸጋገርበት መሆን አለበት። ስለሆነም ከምንጊዜውም በላይ ከውዥንብር በመላቀቅና ህዝብን ከማደናበር ታግዶ ወደ ተባበረና ለዕድገት ወደሚያመች ስራ መሰማራቱ የኢህአዴግን አገዛዝ ዕድሜ ያሳጥረዋል። የኢትየጵያ ህዝብ የሚሻውና የቀን ተሌት ህልሙ ከእንደዚህ ወደ ወሮበላነት የሚጢጋ አገዛዝ መላቀቅ ብቻ ነው።

# ከመቃብር ተመልሶ የመጣውን የሳንሱር መቀስ እንቃወመዋለን፤ ወደ መቃብሩ እንዲመለስም እንታገለዋለን!!

የአቶ መለስ ዜናዊ ልማታዊ መንግስት የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታን ህልማቸው ባደረጉና የገዥ መንግስቱ ህይለማያምን ስርዓት በብዙ መስዋዕትነት ባስወገዱ ኢትዮጵያውያን ደም ወደ ስልጣን ማማው ላይ ከወጣ ሃያ አንደኛ አመቱን ለመያዝ ጥቂት ቀናት ቀርተውታል:: ያለፉትን 20 አመታት ወደ ሃላ ሄደን ዴሞክራሲን ዓላማቸው አድርገው መተኪያ የሌለው ህይወታቸውን የገበሩ ታጋዮችንና ኢህአዴግ እየሄደ ያለበትን መንገድ ስንመረምር ግን እንሳቀቃለን:: ‹‹ኢህአዴግ ሀዲዱን ስቶአል›› በማለት ድርጅቱን ለቀው የወጡ የቀድሞ የህወሓት መስራቾች የትግሉ ብቸኛ ስኬት ደርግን ማስወገዱ ብቻ እንደሆነና ከዚያ ውጭ ምንም እንዳልተሳካለት የሚናገሩት ሀቅ እንደሆነ እንገነዘባለን:: ምክንያም ሞትኩለት የሚለውን ዓላማ ተግባራዊ ማድረግ የተሳነው መንግስት ሆንዋልና::

ህወሓት ያደረገው ትግል ድጋፍ እንዲያገኝ ምክንያት የሆነው ደርግ በአቁዋራጭ የነጠቀውን የተማሪዎችና የወቅቱ ልሂቃንን ጥያቄ በአጋጣሚ፤ በስልትና በሁዋላም በጉልበት ከነጠቀ በሁዋላ ለ17 ዓመታት በአምባገነንነት፤ ባለማዳመጥ፤ ባለማስተዋልና ዜጎችን በማሸማቀቅ ባለታሪኩዋን ሀገራችንን ተገቢ ያልሆነ ዋጋ እንድትከፍል አድርጎ ስለነበረ ይሄን አንባገነን የደርግ ስርዓት ለማስወገድ የተደረገው ትግል ክብር እንዲያገኝ ምክንያት ነበር::

የደርጉን አስከፊ ስርዓት ከማስወገድ ባሻገርም ህወሓት/ኢህአዴግ ከዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ጋር በትግሉ ወቅት የማይግባባና የማይተዋወቅ ቢሆንም የዓለማችን ነባራዊ ሁኔታ አስገድዶት (ማለትም የሶቬት ህብረት ጎራ መፈራረስና የምዕራባውያን ጎራ አሸናፊ ሆኖ መውጣት) የማይተገብረውን ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ፤ ነፃ ገበያና የመንግስት ተቋዋማትን ወደ ግል ማዞር የሚሉ አማላይ ‹ታፔላዎችን› በመለጠፍ የህዝቡን ልብ ለመያዝ ጥረት አድርጎ የገዥ መንግስቱን አምባገነን ስርዓት ለመጣል በቃ:: ሌላ ኢህአዴግ የሚባል አምባገነንም ተተካ::

‹‹ተጋዳላዮች›› እና ‹‹ዴሞክራሲ›› የሚል ጭምብል አጥልቀው ወደ ዙፋኑ የመጡት እነ አቶ መለስና ስርዓታቸውም ህገ-መንግስት አቆሙ:: በህገ-መንግስቱ ውስጥም ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለመገንባትና ሰብዓዊ መብት ለመጠበቅ የሚያስፈልጉ መሰረታዊ መብቶች ተካተቱበት:: ዴሞክራሲን ለመገንባት ያስፈልጋሉ የሚባሉት እንደ ምርጫ ቦርድ ያሉ ተቋዋማትም እንደሚመቹ ሆነው ተቁዋቁዋሙ:: ‹‹ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ መብትም ተረጋግጦአል›› ተባለ:: ‹‹የደርጉንም ሳንሱር ቀበርነው›› አሉን:: አሁን ላይ ቆመን ስናየው ግን ይሄ ሁሉ ድካም የተደከመው ከምር ሰብዓዊ መብትን ለመጠበቅና ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለመገንባት ሳይሆን የእርዳታ ምንጭ የሆኑት ምዕራባውያንን ቀልብ ለመያዝ፤ መስዋዕት የሆኑ የታጋዮች ቤተሰቦችን ላለማስከፋትና ህዝቡን ለማታለል እንደሆነ እንገነዘባለን::

ከዚህ በፊት የተፈፀሙትን በርካታ የገዥው ፓርቲ የህገ መንግስትና የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች መዘርዘር አድካሚ ይመስለናል:: በዚህ ሳያበቃም ስርዓቱ የቀድሞው የኮኔል መንግስቱ ሃይለማርያም አስተዳደር ተግባራዊ ያደርጋቸው የነበሩ ጉዳዮችን በመመለስም ላይ ይገኛል::

ለዛሬ ግን አንገብጋቢና አደገኛ የሆነውን አንድ ጥሰት ብቻ እንጥቀስ:: ይሄውም:- ‹‹ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት›› የተባለው የመንግስት የህትመት ተቋዋም ከሁለት ሳምንት በፊት ያወጣው ‹‹የህትመት ስራ ስታንዳርድ ውል›› ነው:: ይሄው 90ኛ ዓመት በዓሉን በቅርቡ ያከበረው አዛውንቱ የመንግስት ማተሚያ ቤት ህገ-መንግስቱን በይፋ የጣሰና የገዥ መንግቱን የቅድመ ምርመራ (ሳንሱር) መቀስ የመለሰ ውል አምጥቷል::

ፓርቲያችን ይህንን ብርሃንና ሰላም ራሱን ከተጠያቂነት ለማዳን በማስመሰል ካዘጋጀው ውል ጀርባ ሌላ እጅ እንዳለ ይጠረጥራል:: ይሄ እጅም የህጎች ሁሉ የበላይ ነው ተብሎ በሚታሰበው ህገ-መንግስት ላይ በአንቀፅ 29 ንዑስ አንቀጽ 3 (ሀ) ላይ ‹‹የቅድሚያ ምርመራ በማንኛውም መልኩ የተከለከለ መሆኑን›› የሚለው ድንጋጌ በአደባባይ ያውም አንድ ማተሚያ ቤት ባወጣው ህግ ሲጣስ ሰምቶ ዝም ያለው መንግስት ነው:: ከዚህ በፊት ‹‹ህገ-መንግስት ተጣሰብኝ፤ ተናደብኝ...›› የሚለው ገዥ ፓርቲ ዝምታ ከብርሃንና ሰላም የሳንሱር ህግ ጥሰት ጀርባ የቆመው አካል ማን እንደሆነ የሚያመላክት ነው::

ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ፤ ለነቃ ትውልድ ቀረፃ፤ ለልማትና ዕድገት አስፈላጊ ነው በሚባለው የነፃው ፕሬስ ላይ ከዚህ በፊት የተከፈተበት የተቀነባበረ የመቆጣጠርና የማጥፋት ዘመቻ አልበቃ ብሎ ጭራሽ ለታላቁዋ ኢትዮጵያ የሚመጥን ነፃ ፕሬስ በሌለበትና ሃላፊነት የሚሰማው መንግስት ካለ ድጋፍ መቸር በሚገባበት ወቅት በሃገራችን እየተደረገ ያለው ግን ያሉትን አንድና ሁለት ነጻ ጋዜጦች ማጥፋት ላይ ያነጣጠረ ዘመቻ አካል አድርገን እንቆጥረዋለን::

ለምን ማተሚያ ቤቱ ‹‹በአሳታሚው እንዲታተም የቀረበለት ጽሁፍ ስክሪፕት ሕግን የሚተላለፍ ስለመሆኑ በቂ ምክንያት ካለው አላትምም የማለት መብት አለው::›› የሚል አሳቃቂ ሕግ በማውጣት ብርሃንና ሰላም ለ20 ዓመት ተቀብሮ የኖረውን የሳንሱር መቀስ ቆፍሮ ማውጣት ለምን አስፈለገው**?** የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ መሞከር አስፈላጊ ይመስለናል::

የኢህአዴግ መንግስት በሚቆጣጠራቸው ሚዲያዎች እና በልማታዊ ጋዜጠኞች አማካኝነት ‹‹በለውጥና በእድገት ጎዳና እየዘለቅሁ ነው›› እያለ ዘወትር የሚናገረው ገዥው ፓርቲ እና ‹‹ለውጡና እድገቱ ካለ ለምን ይርበናል፤ ለምን በቤት እጦት እንንከራተታለን፤ ሀሳባችንን በነፃነት መግለፅ ለምን አልቻልንም፤ መስዋዕት ተከፍሎበታል የምትሉት ዴሞክራሲ የት አለ**?**...›› ከሚለው የህዝብ ይፋዊ ጥያቄ ጋር እያንገራገጫቸው ይገኛል:: ለዚህ መንገራገጭና ለልማታዊ ጋዜጠኞቻቸው የተሰሚነት እጦት እንዲሁም የሴራ ትንተናቸውን የሚያጋልጡት በጣም ጥቂት ደፋር የነፃ ጋዜጦች ናቸው:: ስለዚህ ስህተትን ለማስተካከል በመጣር ፈንታ ያሉትን ጥቂት ጋዜጦች እስከነጭራሹ ማጥፋት አስፈላጊ እንደሆነ ያመኑበት ነው ብለን ለመናገር እንደፍራለን:: ይሄን የማጥፋት ስራም አጥብቀን እንቃወማን፤ እንታገለዋለንም::

ለጥቂት ነፃ ጋዜጦች ማፈኛ ሲባል ከተዘጋጁት የፕሬስ ሕግ፤ የፀረ-ሽብርተኝነት ሕግና እንደ አዲስ ዘመን አይነት የመንግስት ሚዲያዎች ላይ ከሚሰነዘሩ ማስፈራሪያዎች በተጨማሪም በማተሚያ ቤት በኩል የሳንሱር ሕግ በማበጀት ለማጥፋት የተያዘው መንገድ አጥፊና ለሀገርም፤ ለሕዝብም፤ ለመንግስትም የሚጠቅም አይደለም እንላለን::

ስለዚህ የመንግስት ተቅዋም የሆነው ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ‹‹እንፈራረም›› በማለት ያወጣውን የሳንሱር ሕግ እንቃወማለን:: መቃወም ብቻ ሳይሆንም እንታገለዋለን:: የሚመለከተው ህገ-መንግስት አስከባሪ የሆነው የመንግስት አካል ድርጊቱ እንዲቆም ማድረግ ይገባዋል እንላለን:: አፈሩን አራግፎ ከመቃብር የተነሳውን የሳንሱር መቀስ የኢትዮጵያ ሕዝብ በመቃወም የሞት አፋፍ ላይ ያለውን ፕሬስ እንዲታደገው የሚል ጥሪም እናስተላልፋለን:: ከማተሚያ ቤቱ ጀርባ ያለው ድብቅ እጅም እንዲሰበሰብ እንጠይቃለን::

አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ
(አንድነት) ሕዝብ ግንኙነት ኮሜቴ
ግንንቦት 6 ቀን 2004 ዓ.ም

# ኢፍትሐዊነትንና አድሎን ...

ከ ገፅ 5 የዞረ....

ያለው የኢትዮጵያ መንግስት ብቻ ይመስለኛል:: አገር የሚያፈርሰው እንዲህ አይነት አመለካከት ነው:: እኔ ግን ይህን በመርህም ተቀብዬ በተግባርም ሞክሬ አላውቅም::

ነገር ግን ለሥርዓቱ ካለመመቸት ውጪ በሀገሬና በሕዝቤ ላይ አንዳች ጥፋት እንዳልፈፀምኩ ጠንቅቀው የሚያውቁት ከሳሾቹ በወህኒ ቤቶች አካባቢ “አዳፍኔ” በመባል የሚታወቁ የሀሰት ምስክሮችን አቅርበው አስመስክረውብኛል:: በመጽሐፍ ቅዱስ 1ኛ ነገሥት ምዕራፍ 21 ላይ አጽመርስቴን አልለቅም ስላለ “ንጉሡንና እግዚአብሔርን ሰድቧል” ብለው የሀሰት ምስክሮችን አስመስክረው ናቡቴን በድንጋይ አስወግረው እንዳስገደሉት የአክአብ ባለሥልጣኖች የሰው ልጆች መብት ይከበር ባልኩ ኢትዮጵያዊው ናቡቴ ሆኜ ቀርቤያለሁ:: ይህ ድርጊት ከዚህ መዘምር ከሳሾች እራሳቸው ሲኒማ ቤት ውስጥ የእጅ ቦምብ ወርውረው ብዙ ሰዎችን ካቆሰሉ በኋላ ይህን ያደረገው ማሞ ነው በማለት በሀሰት አስመስክረው ሞት ተፈርዶበት አለም በቃኝ እስር ቤት ውስጥ በስቃላት ተቀጥቷል::

በኔ ላይ የቀረቡት የአቃቤ ህግ ምስክሮች በቁጥር አራት ሲሆኑ ሁለቱ ቤቴ ሲፈተሽ ታዛቢ የነበሩ ናቸው:: ሁለቱም ያዩትን በመመስከራቸው በምስክርነት ቃላቸው ውስጥ ወንጀለኛ የሚያሰኘኝ ነገር ባለመኖሩ ሌሎች ሁለት ምስክሮች በሰጡት የሀሰት ምስክርነት ቃል ላይ አተኩራለሁ::

የአቃቤ ሕግ ምስክር ሆኖ የቀረበብኝ አንደኛው ሰው በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪዬ ሆኖ የተመደበ የክረምት ተማሪ ኢዮስያስ አበራ ማሞ ከሌሎች ተማሪዎች ተነጥሎ ቢሮዬ መጥቶ የገዥው ፓርቲ አባል እንደሆነ ይህን ያደረገውም የደህንነት አባል የሆነውን አባቱን በመፍራት እንደሆነ አሁን ግን በፓርቲው ውስጥ የሰፈነውን ኢፍትሐዊነት በመፀየፍ የአንድ ተቃዋሚ ፓርቲ አባል መሆን እንደሚፈልግ በተለይም ደግሞ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክን እንደሚያደንቅ ነግሮኝ እንድመለምለው ጠይቆኝ ነበረ:: እኔም እኔ ያለሁበት ፓርቲ የኦሮሞ ድርጅት እንደሆነና የመድረክ አባላት ከሆኑ ህብረብሔር ፓርቲዎች ውስጥ ወስኖ አንዱን መጠየቅ እንዲሚችል ነግሬው የአንድነት ለፍትህና ለዴሞክራሲ ፓርቲ አመራር አባል የሆነውን የአቶ አንዱአለም አራጌን ስልክ ቁጥር ሰጠሁት::

ግለሰቡ ክቡር ፍ/ቤቱ ፊት ቀርቦ ቃሉን ሲሰጥ ተማሪዬ እንደሆነ ኮርስ ሰጥቼው እንደማላውቅ ለመጀመሪያ ጊዜ የተገናኘነው ሐምሌ ወር 2003 ዓ/ም የመመረቂያ ጽሁፉን ሊያስረክብ ቢሮዬ በተገኘበት ዕለት መሆኑን በዚሁ የመጀመሪያ ግኑኝነታችን “መንግሥት የኦሮሞንና የደቡብን ህዝብ ስለሚጠላ ይጨቁናቸዋል፣ ስለዚህ ተነሳስተን በአመጽ እናስወግደው” እንዳልኩት ተናግሯል:: ሌሎችንም ተማሪዎች ጨምሮ እንደተወያየን አስመስሎ መስክሯል::

ይህ ግን ፈጽሞ ሀሰት ነው:: ግለሰቡ አግኝቶኝ የማያውቅ ከሆነ በሐምሌ 2003 ዓ/ም ሊያስረክበኝ የመጣው የመመረቂያ ጽሁፍ ማን ያማከረውን ነበር? ከአማካሪው ጋር አንዳች ግንኙነት ሳያደረግ ምንነቱ ያልታወቀ የመመረቂያ ጽሁፉን ይዞ ከመጣ ተማሪ ጋር ያውም በመጀመሪያው ግንኙነት ከአካዳሚ ነክ ጉዳዮች ወጥቶ ስለ መንግስት ግልበጣ ማውራት ይታሰባል ወይ? ለአንድ የዩኒቨርስቲ መምህር ተመካሪ ተማሪዎች የሚመደቡት በሚመለከተው ትምህርት ክፍል እንደመሆኑ የተለያየ ፖለቲካ ዝናባሌ እንዳላቸው እየታወቀ አንድን ወገን ብቻ በሚመለከት ፖለቲካ ውይይት መክፈት እንዴት ይታሰባል? የተከሰሰኩት በአሸባሪነት ከተፈረጀ የኦሮሞ ድርጅት ሆኖ ሳለ ግለሰቡ ደግሞ የዚህ ማህበረሰብ አባል አለመሆኑን በግልጽ እየተናገረ፤ ኦሮሞዎች ተበድለዋልና በመንግስት ግልበጣ ተባብረን ልል እንዴ እችላለሁ? ይህ ሰው ኦሮሞዎችን ከጭቆና ለመታደግ ከሰማየ ሰማያት የተላከ አዳኝ ነው ብዬ ልገምት አልችልም:: ይልቅ እሱስ ፍትህን ሲገድል የተመደበ የአክአብ ምስክር ኖሯል::

ሌላኛው ስሜን እንኳን በትክክል ያላስጠኑት የአቃቤ ሕግ ምስክር አመና አርኮ በክቡር ፍ/ቤቱ ፊት ቀርቦ ቃሉን ሲሰጥ “በጥር ወር 2002 ዓ/ም አቶ ጉቱ ሙሲሳ ቤት ተገናኝተን ለአመጽ አነሳስቶኛል” ሲል ተናግሯል::

እኔ ይህን ግለሰብ ለመጀመሪያ ጊዜ ያየሁት ከዚሁ ፍ/ቤት ውስጥ ነው:: ነገሩ የማይታመንና ዱብዕዳ ስለነበረ በዕለቱ ጥያቄም አላቀረብኩለትም፤ ስለማንነቱ ለማወቅ ባደረግሁት ጥረት በቂና ተጨባጭ መረጃዎችን ለማግኘት ችያለሁ:: ግለሰቡ እውነተኛ ማንነቱ ኢመና ኢርኮ ሳይሆን ሺፈራው ኤቢዳ ሲሆን የትውልድ ሥፍራው በምዕራብ ሸዋ ዞን ሸነን ወረዳ ሆኖ አድራሻዬና የሥራ ቦታዬ ነው ያለውን ነቀምቴ ከተማ 01 ቀበሌን ረግጦ እንኳን አያውቅም::

ይህ ግለሰብ የኦሮሞ ህዝብ ኮንግረስ /ኦ.ህ.ኮ /አባል የነበረ ሲሆን በ1997 ዓ/ም የምርጫ ታዛቢ ስነበር በ1998 ዓ.ም ታስሮ የተሠቃየ በ1999 ዓ.ም አጣሪ ኮሚሽን ፊት ቀርቦ ቃሉን የሠጠ በ2000 ዓ/ም ኦህኮን ወክሎ ለወረዳና ለቀበሌ ምርጫ የተወዳደረ:: በ2003 ዓ/ም እንደገና ታስሮ የነበረ ሲሆን ይህን ሁሉ ያደረገው በእውነተኛ ስሙ ነበር:: በመጨረሻም ከደረሰበት ስቃይ የተነሳ እንዲሁም የሚሉትን እሺ ካላለ መኖር እንደማይችል ስለተገለጸለት ያሉትን ሁሉ ለማድረግ ቃል ግብቶ በመፈታት በኔ ላይ በምስክርነት የቀረበ ነው:: ይህንን የመከላከያ ምስክሮች ያስረዱልኛል::

ከላይ እንደገለጽኩት ከግለሰቡ ጋር በአካልም ሆነ በማንኛውም የመገናኛ ዘዴ ተገናኝተን የማናውቅ ከመሆን አልፎ ቤቱ ተገናኘን ያለውን አቶ ጉታ ሙሊሳን እንኳን ለመጀመሪያ ጊዜ ያየሁት ማረሚያ ቤት ሁለታችንም እስረኞች ሆነን ነው:: ይህንንም ምስክሮቼ ያረጋገጡልኛል ለመሆኑ በ2002 ዓ.ም ህገ መንግሥቱን አምኜና አክብሬ በምርጫ ለመሳተፍ ዝግጅት ላይ የነበርኩ ሰው እንዴት ሆኖ ለአመጽ ቅስቀሳ ማካሄድ የምችለው?

ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው ግለሰቡ በኔ ላይ ስለመሰከረው ነገር ብቻ ሳይሆን ማንነቱንና አድራሻውን ጭምር እንዲዋሽ የተገደደ እንደመሆኑ መጠን ክቡር ፍ/ቤቱ ይህን ተመልክቶ የሰጠውን የምስክርነት ቃል ውድቅ እንዲያደርገልኝ እጠይቃለሁ::

አቃቤ ህግ ወንጀለኛ ለመሆኔ እንደአስረጂነት ያቀረበው ሌላው የሠነድ ማስረጃ በ1989 ዓ/ም መጀመሪያ ላይ የተነሳሁት የኦነግ አርማ ተሰቅሎ የሚታይበት ፎቶ ግራፍ ነው:: በ1983 ዓ.ም መጨረሻ ደረግ እሠራበት የነበረችውን ዓለም ተፈሪ ከተማ ለቆ ሲሄድ ብዙ ሰዎች አካባቢውን ለቀው ሲሰደዱ ሠላምና መረጋጋትን ለመፍጠር የተቋቋመውን ኮሚቴ እንድመራ በህዝብ ተመርጬ እስከ 1984 ዓ/ም መጨረሻ ድረስ ሰርቻለሁ:: በዚህ ወቅት በከተማው ፍ/ቤት ከፍተው በይፋ ይንቀሳቀሱ ለነበሩ ሁለት የኦሮሞ ድርጅቶች ኦህዴድና ኦነግ ስብሰባዎችን እየጠራሁና እየመራሁ በገለልተኝነት ሥሰራ ቆይቻለሁ:: በነዚህ ጊዜያት ውስጥ ለኦህዴድ በርካታ ስብሰባዎችን ለኦነግም ጥቂት ሰብሰባዎችን ከተማው መሃል በሚገኝ የወረዳው አስተዳደር ግቢ ሜዳ ላይ መጥራቴን አስታውሳለሁ:: ከነዚህ ስብሰባዎች በአንዱ የተወሰደ ነው የተጠቀሰው ፎትግራፍ ያ ወቅት ሁለት ድርጅቶች እንኳን በመሰብሰቢያ ቦታዎች ቀርቶ በየምሰሶዎቹና ዛፎቹ አርማቻቸውን ይሰቅሉ የነበረ የትኩሳት ጊዜ ነበር::

ወደ ገፅ 10 ይዞራል....

# ማስታወቂያ

## አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ (አንድነት)

## ታላቅ የስነ-ጥበብ ውይይት

ግንቦት 12 ቀን 2002 ዓ.ም ከጧቱ 3:00 ሰዓት እስከ 6:00 ሰዓት ድረስ ‹‹በሕብረተሰብ ውስጥ የሥነ-ጥበብ ሚና›› በሚል ርዕስ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ትያትር አዳራሽ ሕዝባዊ ውይይት ያካሂዳል፡፡ በሙያው እውቅ ግለሰቦች በሚከተሉት ጥያቄዎች ዙሪያ የውይይት መነሻ ሃሳቦችን ያቀርባሉ፡-

1. ሥነ-ጥበብ በሕብረተሰብ ውስጥ ያለው ሚና ምንድን ነው?
2. በሀገራችን ሥነ-ጥበብ ተገቢውን ሚና እየተጫወተ ነውን?
3. እየተጫወተ ከሆነ፣ እሰየው !እንዴት ይበልጥ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይችላል?
4. የማይጫወት ከሆነ ችግሮቹ ምንድን ናቸው?

ከላይ በተነሱት ጥያቄዎች ዙሪያ መነሻ ሃሳቦች ከቀረቡ በኋላ ቤቱ ለውይይት (ለጥያቄና ለመልስ ለአስተያየት) ክፍት ይሆናል፡፡

- በውይይቱ እንድትሳተፉ ሁላችሁም በአክብሮት ተጋብዛችኋል፡፡
- ቀደም ብላችሁ በመገኘት ቦታ ያዙ፡፡
- ሰዓት ይከበር፡፡

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ

የህዝብ ግንኙነት

# አራተኛው የሻማ ምሽት ተከበረ

## "ኢህአዴግ ጣሪያው እንደተበሳሳ አሮጌ ቤት ነው፡፡ አንዱን ሲደፍን በአንዱ ያፈስበታል" አቶ ገብሩ አስራት

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ የህዝብ ግንኙነት የሚያዘጋጀው እና በመላ ኢትዮጵያ የሚገኙ የህሊናና የፖለቲካ እስረኞች እንዲፈቱ የሚያሳስብበት አራተኛው የሻማ ምሽት ግንቦት 3 ቀን 2004 ዓ.ም በጽ/ቤቱ ግቢ ውስጥ በተለያዩ ዝግጅቶች ተከበረ፡፡

ይሄው በርካታ ታዳሚዎችና የታሳሪ ቤተሰቦች የተሳተፉበት የሻማ ምሽት "የፖለቲካና የህሊና እስረኞች በአፋጣኝ ይፈቱ!" የሚል ጠንካራ መልዕክት የሚተላለፍበት ሲሆን ታዋቂ ፖለቲከኞችና ሙሁራን እየተገኙ መልዕክት ያስተላልፋሉ፡፡

በአራተኛው የሻማ ምሽትም የመግቢያ ንግግር እንዲያደርጉ የተጋበዙት የአረና ፓርቲ ሊቀመንበርና የመድረክ ስራ አስፈፃሚ አባል አቶ ገብሩ አስራት ኢህአዴግን በደንብ እንደሚያውቁት ጠቁመው "አብዛኞች አምባገነን መሪዎች እንደሚያደርጉት ሁሉ ኢህአዴግም አምባገነን ከመሆኑ የተነሳ ከስጋት የሚገላገለው ተቃዋሚዎቹን በማሰርና በማሳደድ ነው፡፡ ኢህአዴግን ሳስበው አሮጌና ጣሪያው የተበሳሳ ቤት ሆኖ ይታየኛል፡፡ በአንድ በኩል ደፈንን ሲሉ በሌላ በኩል እየፈሰሰባቸው ተቸግረዋል፡፡ የመምህራን ጥያቄ የሀይማኖት ጥያቄና ሌሎችም የዚህ መገለጫዎች ናቸው፡፡ ህጋዊ ጥያቄዎችን ለማዳፈን ደግሞ የፀረ ሽብርተኝነት ህግ እየጠቀሱ ያስራሉ፡፡ የፀረ ሽብርተኝነት ህግ ተጠቅሶ የታሰሩት የመድረክ አባላት ሽብርተኞች አይደሉም" ብለዋል፡፡

ፖለቲካዊ ይዘት ያላቸው ግጥሞችም የቀረቡ ሲሆን የኦህኮ አባል የሆኑት መምህሩ የህግ ባለሙያ አቶ ወንድሙ ኢብሳ የሻማ ምሽቱን አስመልክቶ ንግግር አድርገዋል፡፡ በንግግራቸውም ፓርቲዎች በጋራና በአንድነት በመስራት ትግሉ ግቡን እንዲመታ ማድረግ አለብን ብለዋል፡፡

የዕለቱን ሻማ የለኮሰችው በሽብርተኝነት ተከሶ ማረሚያ ቤት የሚገኘው የአቶ አንዱዓለም አያሌው ባለቤትና በዚያው ግንቦት 3 ቀን 2004 ዓ.ም የአንደኛ አመት የልደት በዓሏን ያከበረችው ህፃን ክርስቲና መሆናቸው ታውቋል፡፡

ጧፍ እየበራም "የእነ አቶ መለስ ወኔ እኛም ውስጥ አለ! የህሊና እስረኞች ያለ አንዳች ቅድመ ሁኔታ በአስቸኳይ ይፈቱ" በሚል ርዕስ የመዝጊያ ንግግራቸውን በፅሁፍ አቅርበው የመርሀ ግብሩ ፍፃሜ ሆኗል፡፡

# የፕ/ር አስራት ወልደየስ 13ኛ ዓመት ሙት ዓመት ታስቦ ዋለ

« ሻማውን ለኩሰነዋል ከእንግዲህ ማንም አያጠፋውም» ፕ/ር አስራት ወልደየስ

የታዋቂው የቀዶ ጥገና ባለሙያና የመላው አማራ ሕዝብ ድርጅት/መአህድ/መስራችና ፕሬዚደንት የነበሩት የፕ/ር አስራት ወልደየስ 13ኛ ሙት ዓመት በልዩ ልዩ ዝግጅትና በሥርዓተ ፀሎት ታስቦ ዋለ፡፡ ዕለቱ በተለያዩ ዝግጅቶች ታስቦ የዋለው ባለፈው እሁድ በመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት/መኢአድ/ ጽ/ቤት ሲሆን ሥርዓተ ፀሎቱ የተከናወነው ደግሞ በትላንትናው እለት መካነ ቀብራቸው በሚገኝበት አራትኪሎ በሚገኘው እግዚአራብ ቤተክርስቲያን ነው፡፡

በመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት/መኢአድ ጽ/ቤት በተከናወነው ሥነ-ሥርዓት ላይ ታዋቂው ዓለም አቀፍ የህግ ምሁር ዶ/ር ያዕቆብ ኃ/ለማሪያምና የመኢአድ ማዕከላዊ ም/ቤት አባል ተዋቂው የባንክ ባለሞያ ዶ/ር ደንበል ባልቻ በጋራ 13ኛውን ዓመት ሻማ ለኩሰዋል፡፡ ዶ/ር ያዕቆብ ባደረጉት ንግግር «ፕ/ር አስራት ወ/የስ የመኢአድ መሪ ብቻ ሳይሆኑ የሁላችንም መሪ ነበሩ፡፡ የትግላችንም ፈር ቀዳጅ ናቸው፡፡ አንድ ቀን በመሀል አደባባይ ሐውልታቸው በክብር ይቆማል፡፡» ብለዋል፡፡ በዝግጅቱ ላይ በአቶ ስለሺ ያቀረበው ግጥም «አጽሙ ይፋረዳል» የሚለው ታዳሚውን ያስደመመ ነበር፡፡

የእለቱን ዝግጅት በንግግር የከፈቱት የመኢአድ ተ/ም/ፕ አቶ ወንድምአገኝ ደነቀ ናቸው፡፡ አቶ ወንድምአገኝ ባደረጉት ንግግር «ፕ/ር አስራት ወልደየስ መአህድን ለማቋቋም የተገደዱት ወያኔ አገሪቱን እንደተቆጣጠረ አማርኛ ተናጋሪው ህዝብ ላይ በከፈተው እልቂት ነበር፡፡ የአማርኛ ተናጋሪውን ህብረተሰብ በብሔራዊ ጨቋኝነት በመፈረጅ በበደኖ፣ በገለምሶ፣ በአርሲ፣ በወለጋ፣ በቤኒሻንጉል፣ መግደልን፣ ወደ ገደል፣ መወርወርን ህፃናትን፣ ነፍሰጡሮችን፣ አረጋዊያንን በቤት ውስጥ እንዳሉ በእሳት ማቃጠልን፣ በተደራጀ ወታደራዊ ኃይል በጥይት መፍጀትን ሥራዬ ብሎ በሚያካሂዱበት የግፍ ዘመቻ ወቅት ነበር፡፡» ብለዋል፡፡

አቶ ወንድምአገኝ በማያያዝም ባደረጉት ንግግረ «ወያኔ የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪውን ህዝብ ይፈጅ የነበረው በኦነግ እያሳበበ ነበር፡፡ አማራን በመጨፍጨፍ ሥልጣኑን ለብቻው ከተቆናጠጠ በኋላ የአገሪቱን ሀብት በመዝረፍ ዝናን እና ተራ ክብርን ለማግኘት አስቦ ነበር፡፡ ካለፈው የቀጠለ በቅርቡ በአማራው ህዝብ ላይ የጥቃት ዘመቻውን አጠናክሮ ቀጥሎአል፡፡ በደቡብ ጉራ ፈርዳ እና በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች አዲስ ጥቃት ቀጥሎአል፡፡ በታሪክ መቼም ጊዜ በኤርትራ ተዳድራ ያልነበረውን የአሰብን ወደብ ለኤርትራ በመስጠት አገር ያስገነጠለው ወያኔ ዛሬም የጥፋት ጉዞውን አጠናክሮ ቀጥሎአል፡፡» በማለት ሠፊ ንግግር አድርገዋል፡፡

በፓርቲው የድርጅት ጉዳይ ኃላፊ በአቶ አበባው መሀሪ የፕ/ር አስራት የህይዎት ታሪክ በንባብ ቀርቧል፡፡ የመኢአድ የስዊድን፣ የካናዳና ቶሮንቶና የእንግሊዝ ድጋፍ ሰጪ ተወካዮች ለታዳሚው የስልክ መልእክት አስተላልፈዋል፡፡ በተለይ ከለንደን የፓርቲው ድጋፍ ሰጪ ተወካይ አቶ ጌታቸው አለማየሁ ባሰሙት ንግግር የፕሮፌሰርን የትግል ታሪክና በእስር ዘመናቸው፣ የፍርድ ሂደትን፣ ታመው በነበረበት ወቅት የህክምናቸውን ሁኔታ በወቅቱ ከውጭ ሚዲያዎች ዘ-ጋርዲያንና ዘ-ዋሽንግተን ፖስት የተባሉት ጋዜጦች የፃፉትን በመጥቀስ ተናግረዋል፡፡ ፕ/ር አስራት ላይ የተሰጠውን ፍርድ "ተአማኒነት የሌለው ፍርድ ብለው በዘገባቸው እንዳጣጣሉት" ጠቅሰዋል፡፡

በትላንትናው እለት በእግዚአብሔራብ በተደረገው ሥርዓተ ፀሎት ላይ የትግል አጋሮቻቸውና ታዋቂ ግለሰቦች ተገኝተዋል፡፡ ከሥርዓተ ፀሎቱ በኋላ የፀሎቱን ማስረጊያ የሰጡት ካህን እንደተናገሩት « እኚህ ታላቅ ክቡር ሰው በህይወት ዘመናቸው ለአገራቸው ክብር ሥራ ሠራተው አልፈዋል፡፡ ለእውነት ሞተዋል፡፡ የክብር እረፍት አግኝተዋል፡፡ ሞተዋል ተብሎ ሊለቀስላቸው፣ ሊታዘንላቸው አይገባም» ብለዋል፡፡

በመካነ መቃብራቸው ላይ አበባ ተቀምጦላቸዋል፡፡ ከአበባው ማኖር በኋላ አቶ ማሙሸት አማረ አጭር ንግግር ያደረጉ ሲሆን ባደረጉት ንግግርም «ፕ/ር በህይወት በነበሩበት ወቅት ለእውነት ኖረዋል፡፡ ኤርትራ አትገነጠልም ብለው ስብሰባውን ረግጠው የወጡ ብቸኛ ኢትዮጵያዊ ናቸው፡፡ እሳቸው የመሠረቱት ድርጅት ዛሬ ታሟል፡፡ በርካታ ዜጎች የሞቱለት፣ የታሰሩበት የተደበደቡበት በደረቁ የተላጩለትና ለተሰደዱለት ዓላማ ዛሬም በጽናት ልንታገል ይገባል» ብለዋል፡፡ አቶ ያሬድ ግርማ በበኩላቸው እንደተናገሩት «ዛሬ እዚህ ቦታ ላይ የመኢአድ አባላት ሁለት ቦታ ተከፍለው መታየታቸው የሚያሳዝን ነው፡፡ ልዩነታችንን ሠብረን ጠንካራ አንድ የሆነ መኢአድን እንመስርት » ሲሉ አቶ ታጠቅ በበኩላቸው "በሚቀጥለው ዓመት አንድ ሆነን የምናከብር ሲሆን በአጭር ጊዜ ውስጥ መኢአድን መኢአድ እናደርገዋለን፡፡" ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ከሥርዓተ ፀሎቱ በኋላ ከመኢአድ ጽ/ቤት የመጡት ለብቻ የእነ አቶ ማሙሸት ቡድን ለየብቻ ተለየይተው ፀበል ፃዲቅ ሲቃመሱ ታይቷል፡፡

---

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ

(አንድነት)

## የገቢ ማሰባሰቢያ የራት ፕሮግራም

አንድነት ፓርቲ የኢትዮጵያ ህዝብ የስልጣኑ ባለቤት እንዲሆን ለማድረግ በቁርጠኝነት እየታገለ ይገኛል፡፡ ለትግሉ ስኬት የርሶ ድጋፍ ወሳኝ ነዉ፡፡

የአንድነት ፓርቲ የፋይናንስ ቋሚ ኮሚቴ የራት ዝግጅት ፕሮግራም አዘጋጅቷል፡፡ መግቢያ ባለ 1,000፣ 500ና 300 ብር መግቢያ ካርዶች ተዘጋጅተዋል፡፡

በራት ፕሮግራሙ ላይ ታዋቂ ግለሰቦች ንግግር ያደርጋሉ፡፡ የራት ግብዣዉ ግንቦት 25 ቀን 2004 ዓ.ም ይደረጋል፡፡ የሆቴሉ ስም ግንቦት 14 በሚወጣዉ ፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ላይ ይገለፃል፡፡

በዉጭ ሀገር የምትኖሩ ኢትዮጵያዉያን በሚኖሩ ቤተሰቦችና ጓደኞች ካርዱን መግዛት ትችላላችሁ፡፡

ለተጨማሪ መረጃና ካርድ ለመግዛት በሚከተለዉ አድራሻ ይጠቀሙ፡-

በቢሮ ስልክ ቁጥር፡- 01 18 40 08 11

ሞባይል 09 11 61 84 34

ኢ-ሜይል

andinetfinance@yahoo.com

andinet@ andinet.org

የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት)

ንብ ባንክ ዑራኤል ቅርንጫፍ

የሂሳብ ቁጥር 510

ለዴሞክራሲ ስርዓትና ለህግ የበላይነት ሁላችንም ካርዱን በመግዛት ድርሻችንን እንወጣ!